ፓትሪሺያ
ሴንት ጆን

# ጐረቤት ፈልጌ ነበር

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

የመጀመሪያው እትም 2002 ዓ.ም
First published 2010

የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡ አስቀድሞ ከቃለ እግዚአብሔር አንባቢያን ማኅበር ፈቃድ ካልተገኘ በስተቀር፣ የዚህን መጽሐፍ የቱንም ክፍል በኤሌክትሮኒክስ፣ ሜካኒካል፣ ፎቶ ኮፒ፣ በድምፅ መቅረጫ መሣሪያም ሆነ በሌላ በማንኛውም መንገድ ማባዛት፣ ማስቀመጥ፣ ወይም ማሰራጨት አይቻልም፡፡

ትርጉም ፡- ዳንኤል ተሾመ
እርማት፡- ኃይሌ ጀናይ
ዋና አርታዒ፡- ዘነበ ገብረሐና
የኮምፒውተር ጽሑፍና የገጽ አቀማመጥ፡- ጥሩወርቅ በቀለ

አሳታሚ / Publisher: የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል / SIM Publication
የፖ. ሣ. ቁ. / P.O. Box.: 127፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ / 127, Addis Ababa, ETHIOPIA
ኢ-ሜይል / E-mail: simmedia@ethionet.et

Copyright © Patricia M St John 1987. Revised 2007.
First published in English by Scripture Union,
207-209 Queensway, Bletchley, Milton Keynes
MK2 2EB, Buckinghamshire, United Kingdom

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING



# ጕረቤት ፈልጌ ነበር

## 1

ኤማ ከእንቅልፏ ነቅታ ክብ ወደ ሆነው ሰማያዊ ሰማይ ቀና ብላ የተመለከተችበት እንዲሁም ሌላ ቀንን ስለ መቀበል የተደነቀችበት ጊዜ የሚያዝያው ማለዳ አራት ሰዓት ተኩል ሆኖ ነበር፡፡

ለተጨማሪ አንድ ሰዓት ተኩል ወይም ፀሐይ ልክ እንደሚያቃጥል እውሬ ምድርን ለማቃጠል እና ለማጠውለግ ከመውጣትዋ እጅግ ቀደም ብሎ፣ ጊዜው ደስ የሚያሰኝ ቀዝቃዛ ነበር፡፡ ምንም እንኳ የቡድን መሪዋ፣ እን፣ የመታጠቢያ ቤቱን ወደ ከለለው የቆርቆሮ ከለላ ቀድሞውኑ በዓላማ የሄደች ቢሆንም፣ እሁንም ገና መሄድ አላስፈለጋትም፡፡ ነገር ግን፣ አን ሁልጊዜ ከማንኛውም ሰው ግማሽ ሰዓት ቀድማ ስለምትነሣ እንዲሁም በግማሽ ሰዓት ስለማትፈጥን፣ ያ ኤማን አላስጨነቃትም፡፡ በጊዜው በተሰነጣጠቀው መሬት ላይ ተበታትነው ያሉትን ቀሪዎቹን እምስት አልጋዎች የያዙ ሰዎች በእንቅልፍ ላይ ነበሩና ጊዜው ጸጥ ረጭ ያለ ነበር፡፡ በዚህ የማለዳ ጊዜ፣ የማለዳው ዝማሬ ይጀምራል፡፡ ነገር ግን በዚህ ደረቅና የተጠማ መሬት ወፎች የሉም፤ እንዲሁም የጸደይ ወቅት ምልክት የለም፡፡

በአሳብዋ እንድ የሆነ ነገር ነበር፤ ከአንድ ወይም ከሁለት ደቂቃ በኋላ፣ የምታስታውሰው ነገር አለ፣ እርሱም የልደትዋ በዓል ነበር፡፡ ከእንግሊዝ አገር ተነሥታ እዚህ ከደረሰች ገና አምስት ቀንዋ ነው፡፡ ደግሞም ስለ ልደትዋ ለማንም አልተናገረችም፣ አንድ ሰው ከዋና ከተማ ወደዚህ እስኪወርድ ድረስ ለአሥር ቀናት የምትቀበለው ደብዳቤ የያዘ ፖስታ አይኖርም፡፡ ያለፉት የልደት በዓላት በምትቈርሰው ኬክ ዙሪያ በሳቅ የሚፍነከነኩት ልጃገረዶች

የሚሰበሰቡበትን ክፍል፣ በዴቮን ያለ የካህን ቤት እንዲሁም በገበታው ላይ የሚቀርቡ ስጦታዎች፣ በአትክልት ስፍራው ያለው የአበባ ፍካት፣ በሚያንጥረው ሳር ላይ የሚወርደው ለስለስ ያለ ዝናብ ወይም ፀሐይ ያረፈችበት ታላቅ መዘርጋት፣ እናትዋን እያሰበች ሳለ፣ ታላቅ የናፍቆት ማዕበል በላይዋ ላይ አለፈ። ይተናነቃት የነበረውን እንባዋን ዋጠችው፣ ዓይኖችዋን ጠራረገች ደግሞም የተበታተኑትን አልጋዎች ቃኘቻቸው፤ የተጨናነቀው ጎጆ ቤት ሊተኙበት የማያስችል ሙቀት ነበረው፣ የገላ መታጠቢያ ውኃ ማፍሰሻውንና በመሬት ላይ ያለውን ቀዳዳ አካትቶ የያዙት የቆርቆሮ መጠለያዎቹ ራስዋን ወደ ኋላ እንዳትሰበስብ አደረጓት። እያንዳንዱ ሰው በጥቂት ቀናት ውስጥ ሙቀቱን ትላመደዋለች ይላል፤ ሌሎቹም ተላምደውታል፣ ደግሞም እርሷም እንደዚሁ እንደሚሆን ታስባለች። ያም ሆነ ይህ፣ ብዙ የሚሠራ ሥራ ስላለ ዛሬ የተሻለ ቀን ይሆናል። ምክንያቱም ዛሬ የመጀመሪያዎቹ 20,000 ስደተኞች ወደ አዲሱ የስደተኞች ጣቢያ ይደርሳሉ።

ሌሎች ሰዎች እየተበጣበጡ ነበር፤ ስለዚህ ከእንቅልፍዋ ተነሥታ ወደ መታጠቢያ ቤት ለመግባት ወረፋ ያዘች። የሚቀርበው ቁርስ ከሻይ፣ ከዳቦና ከሙዝ የሚዘጋጅ የችኮላ ምግብ ነበር፣ ነገር ግን ቀለብ ከዋናው ከተማ ሲመጣ ይህ ይሻሻላል። በአምስት ሰዓት ተኩል፣ አን፣ ልክ እንደ ፍየል - አውራ ቡድንዋን እየዞረች በመመልከት ከባድ መኪናዎቹ ፀሐይ ከመውጣትዋ በፊት እንደሚደርሱ በድጋሚ ለቡድንዋ አባላት ትነግራቸዋለች። ከአራት ወይም ከአምስት አፍሪካዊ ወታደራዊ ረዳቶች ጋር ዕቃዎቻቸውን በማዘጋጀት በአንድ ላይ ሆነው በጂፕ መኪና ተጫኑ። ከዚያም ጸጥ ረጭ ባለው መንደር እየተንገጫገጩ፣ ታላቁን ግድብ በሚመጥነው ድልድይ ላይ እንዲሁም ዱኳ– የለሽ በሆነው ደረቅ በረሃ፣ የፀሐይዋን መውጣት ወደ ኋላ ትተው ሄዱ። እንግዳ የሆኑትን አረንጓዴ ተክሎች ብቅ ብቅ ማለት እንዲሁም በአድማሱ ላይ የሚታዩ እና ጂፕ መኪናዋ እየቀረበች ስትመጣ የሚጠፉትን የውኃ ገንዳዎች ካልቈጠራችሁ በቀር፣ በመሬቱ ላይ የሚታየውን ተደጋጋሚና አሰልቺ ነገር



የሚገቱት እድገታቸው የተስተጓጎለ ዛፎች እና የሞቱ እንስሳት ቅሪተ አካላት ነበሩ።

መንገጫገጭ እና ጩኸት ሁሉንም ራሶቻቸውን ወደ አንድ አቅጣጫ እንዲመልሱ አደረጋቸው። እየተፍጨረጨሩ መደገፊያውን የተጠጉ ወይም በመሀል ያሉቱ እርስ በርሳቸው ተ ያይዘው ያሉ ወደ አርባ የሚሆኑ ሰዎች የያዘ ግልጽ የከብቶች መጫኛ መኪና አልፎአቸው ሄደ። አን፣ በዚያ ፍጥነት ለመንዳት እና የታመሙ ሰዎችን እንዲሁም የተራቡ ሰዎችን አጥንት ለማወዛወዝ ሹፌሩ ምንም መብት እንደሌለው የምልክት ማስጠንቀቂያ ሰጠችው። በፍጥነት እየተጓዘ ያለው እና በድንኳኖቹ መሥመር ላይ የሚጓዘው ጂፕ መኪና ወደ መታየቱ መጣ። ሁለቱ ተሽከርካሪዎች ከሞላ ጎደል ፊትና ኋላ ሆነው ደረሱና የቡድኑ አባላት ከመኪናዎቹ ወረዱ።

በአን በደንብ የሠለጠኑ ስለ ነበሩ፣ ምን ሊያደርጉ እንደሚገባቸው በትክክል ያውቁ ነበር። አንዳንዶቹ ወደ ትልቁ መጠለያ ሄዱ፤ ደግሞም በመመዝገቢያው ጠረጴዛ፣ በክብደት መመዘኛው ማሽን፣ በሕክምና ወይም በቴራፒ ማዕከላት በየደ ረጃቸው ቆዩ። ከአንድ ቡድን የወታደራዊ ረዳቶች ጋር በመሆን፣ አን እና ኤማ ወደ ጭነት መኪናው ይፈጥኑ ነበር። የኋላ መደገፊያዎቹን እያነሡ ሳሉ ተጓዦቹ ወረዱ፣ ደግሞም እጅግ በጣም ቀጫጭን የሆኑ ትናንሽ ልጆች በመድረሳቸው እየተደሰቱ ወደ ታች እየተመለከቱ ለሚያዩት ሁሉ በደስታ እጆቻቸውን ማወዛወዝ ጀመሩ። ሚስቶቻቸው የሚያቀብሉዋቸውን የታሸጉ ዕቃ ዎች እና የውኃ ማሰሮዎችን ለመቀበልና ደግሞም አዛውንቶች እና ሕሙማንን ረድተው ከዚያ ለማውጣት አባቶች ቀጣዩን እርምጃ አደረጉ። ከዚያም አንዲት ደንጋጣ ዓይኖች ያላት ሴት በፍየል ቆዳ የተጠቀለለ ቀለል ያለ ጥቅልል ለኤማ አቀበለቻት፣ ወርዳም ፊት ለፊትዋን እየተመለከተቻት ከእርስዋ ጎን ቆመች።

ሌሎች የጭነት መኪናዎችም እየደረሱ፣ መሥመራቸውን ይዘው እየቆሙና የሰው ጭነታቸውን እያራገፉ ነበሩ። በዚያ ማለዳ በግምት ወደ አንድ ሺህ ስድስት መቶ የሚሆኑ ተጓዦች እዚያው

ደረሰ፣ ነገር ግን ኤማ በእቅፏዋ ውስጥ ያለውን ያንን ብልጭ ድርግም የሚል አሳዛኝ ትንሽ ሕይወት በድንገት አሰበችው:: ለአን ስ(ዐ)ቻት::

«እየሞተ ነው፣» አለች:: «በቀጥታ ልውሰደው?»

«አዎን፣ ፍጠኚ፣» ስትል አን በአጭሩ መለሰች:: «ክሌር በመመገቢያው ጣቢያ ነው ያለችው፣ ሁሉንም ነገሮች አዘጋጅታለች:: በቦታሽ እንድትሆን ለካትሪን ንገሪያት፣ አንድ ሰው ወደ ቀይ መስቀል ክፍል ላኪ:: ምናልባት ዶክተር ሊያዘጋጁልሽ ይችሉ ይሆናል::»

ኤማ ፈጠነች:: ግራ ተጋብተው ያሉትን እና የወተት ማደያውን አጨናንቀውት ያሉትን አሁን የደረሱ ሰዎችን አቋርጣ በማለፍ፣ ክሌር በጣም የታመሙ ሰዎችን፣ በድርቀት የተጐዱ ልጆችን እየተጠባበቁ ያሉ ወታደራዊ ረዳቶችን እያሠለጠነች ወዳለችበት ወደ መመገቢያው ጣቢያ ደረሰች:: ነገር ግን ሕፃንዋን በኤማ እቅፍ ውስጥ ባየች ጊዜ ማስተማርዋን አቋረጠችና በአንድ ላይ በመሆን በአፍንጫ ውስጥ የሚገባ ቀጭን የፕላስቲክ ቱቦ በማስገባት ሕይወት ሰጭ ፈሳሹን ደቃቃ ወደ ሆነው የደከመ ሰውነት ለማስረጽ በፍጥነት ተንቀሳቀሱ::

«ቀዝቅዞአል፣» አለች ኤማ ተስፋ በመቍረጥ:: «እርሱን የምንጠቀልልበት አንድ ነገር በዚህ አይገኝምን?»

«አዎን፣ ጥቂት የሹራብ አልባሳት እና ብርድ ልብሶችን የያዘ ሳጥን እዚያ ማዶ አለ:: ልጁን ስጪኝና የምትፈልጊውን ውሰጂ::»

እርሱንም መሥመር ባለው የቀስተ ደመና ቀለም አለበሱት፤ ደግሞም ኅብረ ቀለማት ባሉት ብርድ ልብስ ጠቀለሉት:: ኤማ ፀሐይ ወደ ወጣችበት፣ አስገራሚ የቀለሞች ጠብታ በእነዚያ ደስ የማይሉ አካባቢዎች መካከል በተገኘበት፣ በቡናማ መሬት፣ በቡናማ ጨርቅ፣ በቡናማ ጥቅልሎች ወዳሉበት ዘግናኝ ቦታ ትንሹን ሸክም ወደ በሩ መሄጃ ተሸክማ ወሰደችው:: ነገር ግን የወተት ኩባያዎች ብሩህ የሆነ ቡርቱካናማ ቀለም ነበራቸው፤ እንዲሁም በዘንባባ ዛፍ የተሠራውን ጣራ ሰንጥቀው የሚያልፉት የብርሃን



ነጸብራቆች (ጨረሮች) በብርሃን ነጠብጣቦች ላይ እያብለጨለጩ በወለሉ ላይ ትንሽ የብሩህነት ኩሬዎችን አበጁ:: ስፍራው አሁን በሚያስገርም መልኩ ከመደበኛ ክብደት ዝቅተኛ በሆኑ ልጆች ተሞላ:: ትላልቅ ራሶች፣ ያበጡ ሆዶች እንዲሁም በትር መሳይ እጆችና እግሮች ያሉዋቸውን ሕፃናት በመሸከም የደከሙ እናቶች በመሬት ላይ ተዘርረዋል:: ወተቱ፣ አጥሚቱ እና ከፍተኛ ንጥረ ነገር (ማዕድን) ያለው ብስኩት በሚታደልበት ጊዜ፣ በደበዘዙ ተስፋ ቢስ ዓይኖች ውስጥ የነበሩት በተስፋ ፈነጠቁ:: ቀኑ ደግሞ እየሞቀ፣ እየሞቀ ሄደ::

ኤማ ልጅዋን በወታደራዊ ረዳት ክንዶች ላይ አስቀምጣ እንዲመገቡ ወይም ለመጥባት ወይም ለማኘክ እጅግ በደከሙቱ ሰዎች፣ አፍንጫ ውስጥ የፈሳሽ ምግብ ማስተላለፊያ ቱቦን ለማስገባት እያበረታታቻቸው፣ ከአንድ ቡድን ወደ ሌላ ቡድን ትንቀሳቀስ ነበር:: ከቋንቋቸው አንዱን ቃል አታውቅም፤ ነገር ግን ወላጆች መጠነኛ ፈገግታ ባለው ፊት በሚነጋገሩበት ጊዜ፣ ፈገግ ለማለት ሞከረች፣ ደግሞም ጥቂቶች ለፈገግታዋ ምላሽ ሰጡ:: አንዳንዶች ለመተባበር እጅግ ደክመው ስለ ነበር፣ ልጆቻቸውን በመጨረሻ ለአንድ ሰው ተንከባካቢነት ትተው በመሬት ላይ በተነጠፈው ምንጣፍ ላይ ዝም ብለው ተዘረጉ::

ብቸኛው ዶክተር እዚህም እዚያም በሥራ ተወጥሮአል:: ትናንሽ ቤተሰቦች መጥተዋል፣ በመምጣትም ላይ ናቸው፤ ነርሶችና ወታደራዊ ረዳቶች በትጋት እየሠሩ ናቸው፣ ነገር ግን የኤማ ልብ በበሩ አቅራቢያ ባለች ብሩህ የሆነ ልብስ በለበሰች፣ ትንፋሽዋን ውጣ ባለች፣ ትንሽ ፍጥረት ላይ እንዳረፈ ነው:: «እግዚአብሔር ሆይ፣ እባክህ፣ እንድትኖር አድርጋት፣» ብላ ጮኸች እርስዋን አሳልፋ ለሌላ ሰው እየሰጠች፣ ነገር ግን አሁን ከአንድ የተራበ፣ በረሃብ የተሰበረ ልጅ ወደ ሌላው እየተጓዘች ሳለ በድድብና እና በዓመፅ እንዲህ ባለ አኗኗር ውስጥ ምን ዓይነት ዓሳማ ሊሳካ ይችላል ስትል ተገረመች:: ለምን ሲባል ነው መኖራቸው የሚያስፈልገው? የሆነ ሆኖ፣ በበሩ መግቢያ ያለችውን ሕፃን ለመንከባከብ (ለመመገብ) በምትችልበት ጊዜ ሁሉ ተመልሳ በፍጥነት ወደዚያ ሄደች::

ተስፋ የሚያስቈርጥ ነበር፤ ብዙ ወደ ተጐዳው አካል በቻሉት ፍጥነት ሕይወት አድን ፈሳሽን እያስገቡ ሳለ፣ በዚያው ፍጥነት ተመልሶ ይወጣ ነበር። ሥርዓት ባለው መልኩ የሚከፋፈል የሽንት ጨርቅም ሆነ ውኃ አልነበረም። ኤማ የራሰውን የፍየል ቆዳ ወደ ውጭ ወስደችውና ፀሐይ ላይ አሰጣችው። የሙቀቱ መጠን ወደ 120 ዲግሪ በሚደርስበት ጊዜ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ይደርቃል።

እርሷ ወደ እርሱ እየተመለከተች፣ ሕፃኑን ያዛዋለች፤ ሕፃኑ አፉን በከፈተ ጊዜ ትንሽ የሚቈራረጥ ትንፋሽ እወጣ፣ ከዚያም ሞተ። ክሌር መጣች፣ ከዚያም አብረው መረመሩት፣ ነገር ግን የሞተ መሆኑን በተመለከተ ምንም ጥርጣሬ አልነበረም። ተቀምጣ እንቅስቃሴ-አልባ ሆና፣ በሰመመን እንቅልፍ ውስጥ ወደ ነበረችው ወደ እናቲቱ መሰሉት። ምልክቶችን ሰጧት፣ የውጭ አገር ልብሱን አወለቁለት። ከዚያም፣ በእርሷ ክንዶች ውስጥ አጋደሙት። እርሷም ሁኔታውን በአንዴ ተረዳችው፣ ዝቅ ባለ ድምፅም ማልቀስ ጀመረች። ከዚያም ማልቀስዋን አቆመች፣ ወደ ሞተው ልጅዋ እያመለከተች አንድ ነገር የምትለምን መሰለች።

ክሌር ወደ ወታደራዊ ረዳቶች ተመለሰች። «የምትፈልገውን ነገር ጠይቋት፣» አለቻቸው።

«ልጅዋን ለመቅበር የሚጠቀለልበትን ነጭ ልብስ ትፈልጋለች፣» ሲሉ ወታደራዊ ረዳቶች አብራሩ።

ክሌር የተጠየቀውን ለመፈለግ ሄደች፣ ነገር ግን ነጭ ልብስ አልነበረም፤ እንደ መሐረብ ወይም ሰፊ የቤት ውስጥ ልብስ ያለ እጅግም አልነበረም። ገሚስ አካልን የሚሸፍኑ አልባሳት፣ ጂንሶች እና ቲሸርቶች የጊዜው መገልገያ ልብሶች ነበሩ። እናትየው በቆሻሻ ጨርቅ ሕፃኑን ከጠቀለለችው በኋላ ወደ ድንኳንዋ በመሄድ ቀስ ባለ ድምፅ ማልቀስዋን ቀጠለች።

«ነጭ ልብስ!» ስትል ክሌር ጮኸች። «ከነገ በፊት ልንመለከተው የሚገባ ነገር ያ ነው።» ነገር ግን ኤማ እያዳመጠች አልነበረም፤ የምታሰቅስበትን ቦታ ፈልጋ ወደ ኋላ ተመልሳለች።



ክሌር እጅዋን ጭምቅ አድርጋ ያዘቻት። «አውቃለሁ፣» አለች። «በመጀመሪያ ልክ እንደዛ ተሰምቶኝ ነበር። ልትለምጂው የግድ ይሆናል. . . ለማንኛውስ ይህ ምን የሚሉት ዓይነት ሕይወት ነው? ከእነዚያ የብስኩት ካርቶኖች በኋላ ሂጂ ደግሞም ከእርሱ ውሰጂ፣ ከዚያም ሊያገግሙ ወዳሉቱ ሰዎች ተመለሺ።»

ኤማ ራስዋን ለመቆጣጠር እየሞከረች ከካርቶኖቹ በስተጀርባ ቁጢጥ አለች፣ ነገር ግን ክንዶችዋን በነካት እጅ ደነገጠች። በከፊል ተርባ ትታያለች፣ እንባዋን ከጠረገች በኋላ እጅግ ቀጭን እና እድገትዋ ከመገታቱ የተነሣ ዕድሜዋን ለመገመት የማይቻል እንዲት ልጃገረድን ተመለከተች። በጀርባዋ ላይ የተስተካከለ ዕድገት የሌለው የሚመስል ልጅ ተሸክማለች። አንድ የሆነ ነገር እየተናገረች ነበረች፣ ደግሞም የምትናገረው ነገር አስቸኳይ ይመስል ነበር።

ኤማ አፍንጫዋን ቀሰር አድርጋ ወታደራዊ ረዳቱን ጠራችው። «የምትፈልገው ምንድን ነው?» አለች።

«መረዳት እንዳለባት ነው የምትናገረው፣» ሲል ወታደራዊ ረዳቱ በኀዘን አብራራ።

«ልትረዳኝ? እንዳመሰገንኳት ንገርልኝ። ስምዋን ጠይቅልኝ።»

«ስምዋ ምሕረት ነው።»

«ደግሞስ በጀርባዋ ላይ ያለው ልጅ፣ የእርሷ ልጅ ነውን?»

«አይደለም፣ ወንድምዋ ነው። ወላጆች የሏቸውም።»

«ወላጆች የሉዋቸውም? ዕድሜዋስንት እንደ ሆነ ጠይቃት።»

«14 ዓመትዋ ነው፤ ልትረዳሽ ትፈልጋለች።»

አሥራ አራት ዓመት። ከታናሽ እኅትዋ፣ ከቤኪ ጋር ዕድሜያቸው እኩል ነው! ቤኪ፣ ከሰፊ ቤተሰብ ውስጥ የምትወደደዋ ታናሽ ልጅ፤ በፍቅረኞች ቀን በሚላክላት ካርዶች ትፈነድቅ የነበረችው እንዲሁም ስለ ክብደትዋ እጅግ ትጨነቅና ለመቀነስ ሙከራ ማድረግ እንዳለበት ግራ ትጋባ የነበረችው ቤኪ! በቤኪና በዚህች የጐደጐዱ፣ ሥቃይን የቀመሱና ሩኅሩኅ ዓይኖች ባሉዋት ኃላፊነት

የሚስማት አሳዛኝ ልጅ መካከል የሚገኝ የሚጋሩት ነገር ሊኖር ይችላልን?

«እንዳመሰገንኳት ንገራት፣ ደግሞም እኔን የምትረዳኝ ከሆነ በጣም ደስተኛ እሆናለሁ፣» አለች ኤማ። «ኩባያዎቹን አሁኑኑ መሰብሰብ ትችል እንደ ሆነ ንገራት።»

ምሕረት በቀጥታ ፊትዋን ተመለከተችና ከመሄድዋ በፊት ፈገግ አለች፤ ልክ እንደ አንድ የልመና ዓይነት፣ እንባዎችዋ ተረስተዋል ስትል ኤማ አሰበች። እርሷ እና ምሕረት አብረው ይሠራሉ፤ ደግሞም ሌላውን ቀን እንዴት አገኘዋለሁ ሲሉ መባዘን ከዚህ በኋላ የለም። ወደ አንገትዋ እየተንጠባጠበ ከሚወርደው ሳብና ሙቀት ባሻገር፣ በጣም ደስተኛ ነበረች፣ ትወጣ የነበረውም ለመስጠት፣ ለመፈወስና ለማጽናት ደስተኛ በመሆን ነበር፤ ምናልባትም በምሕ ረት ጀርባ ላይ የታዘለውን ሕፃን አስቂኝ ገጽታ ወደ ጤንነት ለመመለስ እንኳ ትረዳ ይሆናል። በቅጽበትም ይህ፣ የተጣበበ፣ የታጨቀ መጠለያ ለወጣት እጩ ነርሶች በዓለም ላይ እጅግ ምርጥ የሆነ ስፍራ ነው ስትል ወሰነች።

ነገር ግን ምሕረት ማን ናት ደግሞስ የመጣችው ከየት ነው? እነርሱን በሺህ ማይሎች ከሚለያይ ስፍራ በአንድ ላይ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ምን ዓይነት እንግዳ የሆነ የዕድል ነፋስ ነው? ቤትዋ የት ነበረ ደግሞስ በወላጆችዋ ላይ የተከሰተው ምንድን ነበር? ኤማ ታሪኳን ማወቅ ትችል ይሆን? አላወቀችውም። የምታውቀው ብቸኛ ነገር እርስዋ ልትቀበለው ከምትችለው በጣም ምርጥ የሆነው የልደት ስጦታ እርሷን የነካት የምሕረት እጅ እና በዓይኗ ውስጥ የነበረ የፍቅር እይታ ብቻ ነው።



# 2

ምሕረት መንገዱን እየቃኘች በቤትዋ በር ላይ ቆማለች። ፀሐይ ወደ ምዕራብ ቄጣ ባስ ቀይ ቀለምዋ ከቤቱ ጣሪያ ባሻገር እየጠለቀች ነበር፣ የምሕረት ትንሹ ወንድም ስለ እራቱ ያለቅስ ነበር። እስከ አሁን ድረስ የፍርሃት ስሜት አልተሰማትም፣ ምክንያቱም፣ ከሁሉም በላይ ለምግብ ማከፋፈል ያለው ወረፋ ብዙውን ጊዜ ረጅም ነበር፣ ደግሞም ወላጆችዋ ቀኑን ሙሉ እዚያ ውለው ይሆናል፤ ነገር ግን ልክ እንደዚህ አይዘገዩም ነበር! በውስጥዋ ትንሽ የፍርሃት ስሜት ተለኰሰ፤ ምክንያቱም፣ በእነዚህ ቀናት የቱም ነገር ሊከሰት ይችላል። አንድ ነገር ሁልጊዜ ይከሰታል፣ ስለ እርሱ ብቻ አትናገሩም - ረሃብ፣ ጥማት፣ ከእይታ መሰወር፣ ድንገተኛ ሞት እንዲሁም ማብቂያ የሌላቸው የነገሮች እጥረት፤ ሲነገሩ የማይገባ ነገሮች፣ የምታንሾካሹኳቸው ቃላት ብቻ፣ ከመጠን በላይ የምትሰማቸው ነገር ግን ከቶ የማታውቃቸው ቃላት የሕይወት ዘይቤ እየሆነ መጥቷል። ደግሞም በአንድ ላይ እስከ ጠበቃችኋቸው ድረስ ምንም ችግር አይኖርም። ነገር ግን ዛሬ እነርሱ ተለይተዋል፣ እንዲሁም ምሽቱ በፍጥነት መጥቷል፤ ይሁንና፣ ወላጆችዋ እቤት አልመጡም።

አሁን በልቅሶ እያላዘነና ወለሉን በእጆቹ እየደበደበ ወዳለው ወደ ወንድምዋ ተመልሳ መጣች፤ ነገር ግን ትንሽ ኃይል ያለው ያልጠነከረ ሕፃን ስለ ነበረ፣ የሚያደርገው ነገር በአብዛኛው የእዩኝ የእዩኝ ዓይነት አልነበረም። መንግሥት በሚቈጣጠራቸው ከተማ ዎች አሁንም የሚገዙ ምግቦች አሉ፤ ነገር ግን በሚያሳዝን መልኩ ውድ ሲሆኑ፣ ለእነርሱ መግዣ የሚሆን ብዙ ገንዘብ አልነበረም። ይሁንና፣ ዛሬ የጭነት መኪናዎች ምግብን ጭነው በመንገድ ላይ እየመጡ እንደ ሆነ ደግሞም በታጠቁ ሠራዊቶች በተጠናከ

ረ መልኩ ጥበቃ እየተደረገላቸው እንደ ሆነ፣ ዜና ተሰራጭቶአል:: ሰዎች ከክፍለ አገር ለማምጣት እየፈለጉ ነበር ደግሞም አባትዋ ወንድሙን ለማግኘት ሄዶ ነበር፣ ምክንያቱም ቤተሰቦቹን ለረጅም ጊዜ አላያቸውምና:: ከከተሞች ወደ የነፃነት ታጋዮች መኖሪያ ዱር የሆነ አገር ለማስፍ ቀላል አልነበረም፤ ነገር ግን ገቢያው የመገናኛ ስፍራ ነበር:: አያቷም እንደዚሁ ተጨማሪ ጆንያዎችን ለመሸከም ሄዳ ነበር::

ምሕረት ከተክሌ ጋር ሁሉም በበቅሎ አብረው እንዲጓዙ ፈልጋ ነበር፣ ነገር ግን ጉዞው ረጅም ስለ ነበረ፣ ተክሌ በቀላሉ ይደክማል:: እርሱን ለማየትና ለመንከባከብ፣ ጊዜውን የሚያሳልፉ አንድ የሚያስደስት ነገር ለማድረግ ወደ እርሱ ተመለሰች፣ ነገር ግን እጅግ ዘግይታ ስለ ነበረ፣ በሚያደክም እንቅልፍ ወድቆ ነበር:: እስከ እሁን ጠዋት ድረስ ስላልነቃ አንሥታ ወደ አልጋው ወሰደችው፣ ከዚያም እንጀራ ለመጋገር ዝግጅት ጀመረች:: ሊጡን ካዋሃደችው በኋላ በምድጃ ላይ እሳት አቀጣጠለች፣ ከዚያም እንደ ገና ለመመልከት ወደ በሩ ሄደች:: ነጭ በሆነው የጨረቃ ድምቀት ባለበት መንገድ ላይ ወላጆችዋ ሲመጡ በተመለከተች ጊዜ ትለኩሰዋለች::

ጥልቀት ወዳለው ሰማያዊ ሰማይ፣ እንዲሁም ከተራራዎቹ ጥላ በላይ ከዋክብት የወጡና የሚታዩበትን በአድናቆት ተመለከተች:: በተራራው ከፍታ ላይ በምሽት ይበርዳል፣ እርሷም ትንሽ ብርድ ብርድ አላትና በርኖሱን በተክሌ ላይ ለማድረግ ተመለሰች:: በዚህ ጊዜ ነበር የሚሮጡ እገሮች ድምፅ የሰማቸውና መጥፎ ዜና እንዳለ ያወቀችው::

ምክንያቱም ዜናው መልካም ቢሆን ኖሮ፣ በምሽት በዚያ አካባቢ ግዛት ሰዎች አይሮጡም ነበር:: በየቤታቸው ውስጥ ሆኑ - አንዳንዶቹም እጅግ ከመድከማቸው የተነሣ በምንም መልኩ ለመሮጥ አይችሉም ነበር:: ከዚህም ባሻገር፣ በመንገዶቹ ላይ ጠባቂ ዎች ነበሩና እነዚህ ጠባቂዎች የእያንዳንዱን ሰው ሥራ ለማወቅ ይፈልጉ ነበር:: ፍቅሬ ሁልጊዜ ጠባቂዎቹን ዘወር ብሎ ስለሚያሳልፋቸው እርሱን ከማየቷ በፊት እንኳ ይህ መልእክተኛ



ማን እንደ ሆነ አውቃ ነበር:: እርሱ ቀጫጫ እና ፈጣን ነበር፤ እርሱ ጨረቃ መቼ እንደምትወጣ ሁልጊዜ በትክክል ያውቃል፣ ደግሞም በግድግዳዎች ጥላ ውስጥ ሁልጊዜ ይሮጥ ነበር:: ሹልክ ብሎ እንዲገባ ለማድረግ በጣም በቂ አድርጋ በሩን ከፈተችው፣ ከዚያም እርሱ ከገባ በኋላ በሩን ከበስቲላው ፈጥና ዘጋችው:: ተ ቀመጠ፣ ለመናገርም ትንፋሹን ቊርጥ ቊርጥ ይል ነበር፣ እርሷም ጠበቀችው:: ልብዋ ፈጣን ምቱን እየመታ እንደ ሆነ ለማየት እጆቿን በልብዋ ላይ አደረገች:: ትንሽ ፀጥ ሲል፣ «ምንድን ነው?» አለች:: «ንገረኝ:: ወላጆቼ ናቸው፣ አይደል?» ነገር ግን እፍዋ እጅግ ደርቆ ስለ ነበር ታንሾኳሹክ ነበር::

እጆቹን ራሱ ላይ አድርጎ ተቀምጦ ነበር፣ ደግሞም ማድረግ የቻለው ራሱን መነቅነቅ ብቻ ነበር:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነገራት፣ ነገር ግን ራሱን ቀና ሳያደርግ ነበር የነገራት:: ቃላቱን ለመስማት በጸጥታ ጉንበስ እንድትል፣ «ለሰፈራ ተግባር ወስደዋቸዋል፣» አለ፣ ድምፁን በጣም ዝቅ አድርጎ:: «ብዙ ሰዎች እህል ለመግዛት ወደ ገበያ ስፍራ መጥተው ነበር:: ብዙ ወታደሮች፣ ብዙ ጠመንጃዎች እንዲሁም የጭነት መኪናዎቹን ለመጠበቅ ብረት ለበስ ተሽከሪካሪ ዎች ነበሩ:: በድንገትም ጩኸት እና ግራ መጋባት እንዲሁም ተ ኩስ ተነሣ፤ እንዲሁም ሰዎች እህሉን እያፈሰሱ በሁሉም አቅጣጫ ዎች ይሸሹ ነበር:: እየሮጡም ሳለ ተያዙና ጠመንጃ ተደቅኖባቸው ወደ ጭነት መኪናዎች እንዲወጡ ተደረገ፤ ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ፣ ብዙዎች ተወሰዱ:: ወላጆቻችሁ በቤት ልጆቻቸውን መተ ዋቸውን እየተናገሩ ሲጮኹ ተመለከትኋቸው፣ ነገር ግን ማንም ያዳመጣቸው አልነበረም:: በሮቻቸው ተዘግተው የጭነት መኪናዎ ቹ እያጓሩ ሄዱ::»

መናገሩን አቆመ ረጅም የጸጥታም ዝምታም ሆነ:: ምሕረት ራስዋን አልሳተችም ወይም አላለቀሰችም:: በዓመታት ውስጥ እርሷና ሕዝብዋ ትዕግሥትና ለመኖር የሚደረግ ጥረት ክህሎትን ተምረዋል:: ከትንሽ ጊዜ በኋላ እንዲህ አለች፣ «የት እንደ ሄዱ ታውቃለህ?»

«ወደ ቡና እርሻ የወሰዱዋቸው ይመስለኛል፣» ሲል መለሰ::

«መከር እና ዝናብ እዚያ ታች አለ፤ ጥቂት ሰዎች አሉ ደግሞም እነርሱ በረሃብ ምክንያት የሚሞቱ አይደሉም:: አንዳንዶቹ በገዛ ራሳቸው ነፃ ምርጫ የሄዱ ናቸው:: ምናልባት አንድ ቀን፣ እዚያ ሄዳችሁ ልታገኙዋቸው ትችሉ ይሆናል ይላሉ::»

«እንዲሁም አረንቋዎች እና የጼጼ ዝንብ እንዲሁም የወባ በሽታ አለ ብለው ይናገራሉ፣» አለች ምሕረት ፍዝዝ ብላ:: «ፍቅሬ፣ እኔ ብቻዬን እዚህ መቆየት አልችልም:: የተቀመጠ ጥቂት እህልና ትንሽ ገንዘብ አግኝተናል:: በመንደሩ ወዳሉት አያቶቻችን ተ ከሌን እወስደዋለሁ:: ነገ ማምሻው ላይ እንሄዳለን:: አዲስ ሙሉ ጨረቃ ገና አልወጣችም፣ በጣም ጨለማ ነው:: ወታደሮቹን አልፈን መሄድ ይኖርብናል:: በተራራዎቹ ላይ ያለውን መንገድ አውቀዋለሁ::»

በድንጋጤ ወደ ላይ እየተመለከተ፣ «አይሆንም፣ ምሕረት፣» አለ:: «ያንን ማድረግ አትችይም:: ከግዛቱ ወሰን ወጥተሽ ስትጓዢ ካዩሽ ይተኩሱብሻል:: አንቺ ማን እንደ ሆንሽ ወይም ወዴት እየሄድሽ እንደ ሆነ ለመጠየቅ አይታገሡም:: በዚያ ላይ፣ በመንደሮቹ ውስጥ ረሃብ አለ:: እነርሱ አሁንም ከከተማ ውጭ ወዳሉ መጠለያዎች እህል እያጋዙ ነው:: ከወታደሮቹ ብታመልጪ፣ በረሃብ ትሞቻለሽ:: ወደ እኔ ቤት ከእኔ ጋር ነይ፣ ምሕረት:: በመጋዘን የተቀመጠ እህል አሁንም አለን፣ ደግሞም ቤተሰቦቼ ሁለታችሁንም ይንከባከቡአችኋል::»

ራስዋን በቀስታ አወዛወዘችው:: በዚያን ቅጽበት ሞት ምሕረት የሞላበት መፍትሔ መሰለ፣ ነገር ግን በገዛ ሕዝብዋ አጃቢነት ብቻ ነው ይህ የሚሆነው:: አያቶችዋ አሁን በጣም የሸመገሉና ድኾች ናቸው፣ ነገር ግን የሥጋዋ ቊራጭ፣ የአጥንቷ ፍላጭ ነበሩ:: በዚያ ላይ፣ የወላጆችዋን መጥፋት ልትነግራቸው ይገባል:: ወደዚያ የሚሄድ ማንም የለም::

እጆችዋን ለፍቅሬ ዘረጋችለት:: አሥራ አራት ዓመትዋ ነበር፣ ደግሞም በሚቀጥለው ዓመት እንደ ሙሽራው አድርጎ ይወስዳት ይሆናል:: ስለዚህ ጉዳይ ወላጆችዋ እንደ ተነጋገሩበት እንዲሁም



በጥሎሹ ላይም እንደ ተወያዩበት ታውቃለች፣ ደግሞም ደስተኛ ነበ ረች:: ወደ ማንም ከመሄድ ይልቅ፣ ወደ ፍቅሬ መሄዱን ትመርጣለች:: ነገር ግን አሁን ስለ ጋብቻ ምንም ሊነጋገሩ አይችሉም:: ነገሩ የሕልውና ጉዳይ ነበር::

አንድ ነገር እንድታደርግ ሊያሳምናት አልጣረም፤ ነገር ግን የደፈረሱ ዓይኖቹ በጣም አዝነው ነበር:: «አንቺ ዕድለኛ ነሽ፣» አለ በጸጥታ:: «ትክክል ነሽ፤ ነገ አዲስ ጨረቃ ይታያል፣ ደግሞም በጣም ይጨልማል:: በዚያ ላይ፣ የእጎቴ ባል በጥበቃ ላይ ነው:: የመጀመሪያው መንደር ድረስ እወስድሻለሁ፣ ከዚያም ከመምሽቱ በፊት እመለሳለሁ:: ከዚያ በኋላ፣ ሊሻገሩት የሚቀር አንድ ተራራ ብቻ ነው፣ ደግሞም ቅኝት የሚያደርጉት ወታደሮች ከከተማ እጅግ ርቀው ጥበቃ ለማድረግ አይደፍሩም:: ቀን መጓዝ ትችያለሽ ደግሞም ምሽቱ ከመምጣቱ በፊት ትደርሺያለሽ::»

ለትንሽ ጊዜ አብረው ተቀመጡ፣ ነገር ግን በ14 ዓመት ዕድሜ ኀዘን እንቅልፍህን ሊሰርቅ አይችልም:: ምሕረት ግድግዳውን ተ ደግፋ ድክም እንዳላት ዓይኖቿን ጨፈነች:: ከደቂቃ በኋላ በጥልቀት ትተነፍስ ነበር:: እንድትነቃ ሳያደርጋት ፍቅሬ በምንጣፉ ላይ ጋደም አደረጋት:: ደግሞም ለአንድ ወይም ለሁለት ደቂቃ ወደ ታች እየተመለከታት ቆመ:: እርሷ በጣም ቆንጆ ናት ደግሞም እርሷን ረጅም ጊዜ ጠብቋታል፤ አሁን ደግሞ ተስፋ የለም:: በሺህ ዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እንደ ሞቱት ሁሉ በመንደሩ ውስጥ ትሞታለች:: በኃይል ተነፈሰና በምሽቱ ጨለማ ውስጥ ሄደ::

ምሕረት ተከሌ ወደ እርሷ እስኪመጣና እስኪቀሰቅሳት እስከ ማለዳ ድረስ ተኛች:: በመጀመሪያም ምንድን ነው የተፈጠረው መጥፎ ነገር በሚል ተገረመች፤ ምክንያቱም እንደ ተለመደው በትንሽዋ መስኮት በኩል ዘልቃ ገብታ፣ የአቧራ ብናኞችን እየገለጠች፣ ተነሥታ ቤቱን እንድታጸዳ እያደረገቻት ፀሐይዋ በጣም ደምቃ ወጥታለች:: ከዚያም እናትዋ በአካባቢው እየተንቀሳቀሰች አለመሆኗን ተገነዘበች፣ እውነታ ደግሞ ልክ እንደሚጨፈልቅ ሸክም መታት:: ተነሥታ ከመሄድ ይልቅ፣ በጀርባ ተኝቶ መጋደሙ ቀልሎ ታያት፣ ነገር ግን አሁንም ተከሌ

በዚያ ነበር:: ተነሥታ ቍርሳቸውን ለማዘጋጀት ትንሽ ማገዶ አቀጣጠለች:: ከፍ ባለ ዋጋ የሚገዛ እህል በከተማው ውስጥ ነበረና የምሕረት አባት፣ የሞተር ሜካኒክ እና የጭነት መኪና ሹፌር እንደ መሆኑ መጠን፣ መግዛት ስለሚችሉ ገዙ:: ትንሿን የገንዘብ ማጠራቀሚያቸውን የት እንደሚያስቀምጧት ታውቃለች፣ ደግሞም አንድ ጆንያ ሙሉ ማሽላ በዚያ ነበር:: ለረጅም ጊዜ ግን ሊቆይ የሚችል አይደለም:: በአንዴ ነቅለው መንዝ ይኖርባቸዋል::

ተክሌ፣ በፀሐይ ብርሃን ነጣ ያለና የደበዘዘውን ነበልባል እየተመለከተ፣ እግሮቹን አጠላልፎ በመቀመጥ ቍርሱን እየተጠባበቀ ስለ እናቱ ጠየቀ:: ነገር ግን እርሷ ብቅ ባትልም ኀዘን አልተሰማውም:: በአሥር ዓመት የምትበልጠው ምሕረት፣ እንደ እናቱ አድርጋ ምግብ ትሠራለች:: እየተመገበ ሳለ ዕቅፍዋ ላይ አደረገችውና እናታቸው ርቃ እንደ ሄደችና ነገር ግን ቀኑ ከተገባደደ በኋላ ወደ ቤት አያታቸው እንደሚሄዱና በዚያ እንደሚቀመጡ አብራራችለት:: በደስታ ራሱን ነቀነቀ፣ ምግቡን ጨረሰና በደረጃ ላይ ባለ የፀሐይ መሞቂያ ለመቀመጥ ሄደ፤ ፊቱን ወደ ሙቀቱ በማድረግ በጠጠር ቦርሳ መጫወትን ጀመረ:: ምሕረት እዚያ ረዥም ጊዜ እንደሚቆይ ታውቃለች:: እርሷም ለጉዞ ዝግጅት ጀመረች::

ብዙ መሸከም አትችልም በእርግጥ፣ ብዙ ነገር ቤት ውስጥ መተው ደግሞ መልካም አይደለም:: እንዲህ ዓይነቱ ነገር ከዚህ ቀደም ስለ ተከሰተ፣ ወላጆችዋ ተመልሰው የመምጣታቸው ነገር በአብዛኛው ከቶ የማይቻል እንደ ሆነ እውቃለች:: አንድ ቀን፣ ምናልባት፣ እርሷ ወደ እነርሱ ትሄድ ይሆናል፤ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ወደ ደቡብ በፈቃደኝነት ይጓዛሉ:: ነገር ግን የሚሄዱት በሕመም የተጠቃ ሕፃን በጀርባቸው ላይ ያደርጉ ልጃገረዶች ሳይሆኑ፣ የተመረጡ ጠንካራ ወጣት ወንዶች ናቸው::

የእናቷን ልብሶች በአንድ ላይ ጠቀለለች፤ ብዙም አልነበሩም:: እንዲሁም ምግብ ለመግዛት ሲባል ጌጣጌጦችዋ ከተሸጡ ብዙ ጊዜ አልፎአል:: አንድ ረጅም፣ ለቀቅ ያለ ልብስ፣ የእርሷን ቀሚስ፣ ለእሮጊት አያቷ ትወስዳለች:: ወደ ሙሉ ሰውነት ስላላደገች፣



በወገብዋ ዙሪያ ጠቅልላ ትለብሰዋለች - ደግሞም ለሽማግሌው ሰውዬ የአባቷን ሸሚዝ ጭምር ትወስዳለች:: የጥር ምሽቶች በከፍታማ ቦታዎች ላይ በሚያስመርር መልኩ ቀዝቃዛ ናቸውና ብዙ ልብሶችን መልበስ በቻለች መጠን የበለጠ ጥሩ ነው የሚሆነው:: ቀሪውን እህል፣ አንድ ማሰሮ ውኃ እና ጥቂት እንጀራ ለጉዞው መሸከም ይኖርባታል:: በመጨረሻም ተክሌንም እንደዚሁ መሸከም ይኖርባት ይሆናል::

ቀሪዎቹን አልባሳት ጠቀለለቻቸውና በቤታቸው አጠገብ ወዳሉት ጐረቤቶችዋ ሄደች:: ማኒላ ባልዋ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ይሠራ በነበረበት ጊዜ በመከራ ወቅት አንዳንድ ጊዜ ትረዳቸው የነበረች ደግ ሴት ናት:: ምሕረት ወደ ውስጥ እየገባች ሳለች፣ ሴቲቱ ወደ ላይ ቀና ብላ ፈገግ አለች::

«እሺ፣» ስትል ጀመረች፣ «ወላጆችሽ ባለፈው ምሽት ዘግይተው ነበር የመጡት:: እህሉን አመጡ?» ብላ ጠየቀች:: የልጃገረዷን (የልጂቱን) የተጨነቀ ፊት ልብ ማለትን እንደ ጀመረች ንግግሯን አቋረጠች:: «ወይስ አልመጡም? ምን ሆነሽ ነው፣ ምሕረት? ልጅት፣ እስቲ ቁጭ በይና ንገሪኝ!»

«ሄደዋል፣» አለች ምሕረት:: አሁንም ማልቀስ አልቻለችም:: «ወደ ሰፈራ ጣቢያዎች ተወስደዋል:: ሲሄዱ ፍቅሬ አይቶአቸዋል:: ተመልሰው አይመጡም:: በመንደሩ ወዳሉ አያቶቻችን ተክሌን እየወሰድሁት ነው:: እነዚህን ለአንቺ አመጣሁልሽ::»

ድምፅዋ ሙትት ያለ ነበር፣ ደግሞም የምታስበው ምንም ስሜት አልነበረም:: የምታለቅሰውና በዚያ እንድትቆይ የምትለምናት ማኔላ ነበረች:: «እዚያ ረሃብ አለ፣» ስትል ጮኸች:: «ከከተማው ውጭ ስላሉት መጠለያዎች አስቢ! አሁንም ሰዎች ከየመንደሮቹ እየጐረፉባቸው ነው:: ለአያቶችሽ ሊመግቡት የሚጠበቅባቸው ሁለት ተጨማሪ አፍ ትሆኚባቸዋለሽ:: እዚህ ቆዩ፣ ምሕረት፣ ከእኛ ጋር ልትሆኚ ትችያለሽ::»

ምሕረት ራስዋን ነቀነቀች:: «የአያቶቼ ቤት ከወንዝ አጠገብ

ስለሆነ ድርቅ ሊያገኘው አይችልም፣» ስትል መለሰች። «ምናልባት እስከ አሁን አልተራቡ ይሆናል። ጊዜው ጥር ነው፣ ደግሞም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የበልግ ዝናብ በቅርቡ ይመጣል። ከሞትን፣ እንሞታለን፣ ነገር ግን ቢያንስ ቢያንስ ከዘመዶቻችን ጋር እንሙት።»

ማኒላ ተነሥታ ከክፍሉ በስተጀርባ ወዳለው መጋዘን ሄደች። እህል የያዘ ከረጢት፣ አንድ ጠርሙስ ዘይት እና ትንሽ ገንዘብ ይዛ መጣች። «ይህን መውሰድ ትችያለሽ፣» አለቻት። «ልጄን መሸከም ሳይኖርብሽ አይቀርም፣ ነገር ግን፣ ይህን በአንገትሽ ዙሪያ ልታንጠለጥይው ትችያለሽ። አሁንም በቂ የሆነ ነገር ስላለን እግዚአብሔር ይመስገን። ጀንበርዋ ልትጠልቅ ስትል፣ ከመሄድሽ በፊት እዚህ ነይና ብዪ፣ ደግሞም ንብረቶችሽን ሁሉ ይዘሽ ነይ። ተመልሰሽ እስክትመጪ ድረስ እንጠብቅልሻለን።»

ምሕረት በማኒላ ደረት ላይ ለአንድ ወይም ለሁለት ደቂቃ ልጥፍ አለች፣ እጆችዋንም ያዘች፣ በጉሮሮዋ እና በደረትዋ ላይ ያለው ሕመም እያፈናት ነበር። ደግነትዋ እንባዎችዋን በፊትዋ ላይ አመጡት፣ ነገር ግን እሁንም ገና ልታለቅስ አይገባትም፤ ገና የሚሠራ እጅግ ብዙ ነገር አለ፤ ብዙ የምታቅድና በድፍረት ጎላፊነት የሚወስድበት ነገር አለ። በተከፈተው በር በኩል ተክሌ እየባዘነ (እየተቁነጠነጠ) እርስዋን ሲፈልግ ልትመለከተው ትችል ነበር። «አመሰግናለሁ፣» ብላ፣ የማኒላን እጅ ስማ ወጣች። ቀሪውን የዕለቱን ክፍል ቤቱን በማጽዳት፣ ልብሶችን በማጠብ እንዲሁም ለጉዞው በመዘጋጀት ማሳለፍ ይኖርባታል።

ስለ ደረሰባት ነገር ከእርሷ ጋር የኀዘን ተካፋይ ለመሆን ቀኑን ሙሉ ጐረቤቶች ይመጡ ነበር። ነገር ግን ለስለስ ባለ መልኩ ነበር ይናገሩ የነበሩት፣ ምክንያቱም እነዚህ ክስተቶች እንዲታወቁ አይፈለግም። ደግሞም፣ ቶሎ ሊረሱ ይገባ ነበር። ከዚያ በላይ፣ ከደቡብ የሆነው ቡናው የሚለማበት ስፍራ፦ ግሩም፣ ቀዝቃዛ አየር፣ የተትረፈረፈ ዝናብ እንዲሁም የመከር እህልና ቤቶችና ምግብ የለበት ገነት ነው ተብለው ተነግሮአቸዋል። አንዳንዶች ይህን፣ ምንነው በምርጫቸው ሄደዋል። አንድ ሰው ወደ



ባለሥልጣናት ሄዳ፣ እነርሱም ወደዚያ እንዲወስዱ እንድትጠይቅ ምሕረትን ነግሮአታል፣ ነገር ግን በአካል ትንሽና ደካማ የሆነች፣ የ4 ዓመት ዕድሜ ያለው ሕፃን የያዘች ልጅ፣ ተቀባይነት የማግኘት ዕድል እንደ ሌላት ሁሉም ተስማምተውበታል። በዚህ ላይ፣ የደቡቡ የአገሪቱ ክፍል ብዙ አውራጃዎች ያሉት ስለሆነ፣ የሚገናኙ ስለ መሆናቸው ማወቂያ ምንም መንገድ የለም። ጐረቤቶቹ እዚያ እንድትቆይ፣ እንደሚረዱዋቸውና እንደሚንከባከቡዋቸው በመንገር ለመኑዋት። እውነተኛው ችግር በሚመጣበት ጊዜ፣ ዓይኖቻችሁ ይከፈታሉ ደግሞም መሆን ያለበትን ታውቃላችሁ። መሞት ወይም መኖር፣ የገዛ ወገናችሁን ለማግኘት ትጮኻላችሁ በማለት አሰበች። ጥላዎች እየረዘሙ ያሉበትን ስፍራ በመስታወቱ በኩል ቃኘት አደረገች፣ ደግሞም ፀሐይዋ በቅርቡ ከከተማዋ በስቲያ ትጠልቃለች። ለመሄድ ዝግጁ ነበረች።

# 3

ምሕረት ፀሐይ ከመጥለቅዋ በፊት ቤቱን ቈለፈች፣ ደግሞም ለእነርሱ ምግብ ወደ ተዘጋጀላቸው ወደ እነ ማኒላ ቀሪዎቹን ንብረቶችዋን ተሸክማ ሄደች። እየተመገቡ ሳለ፣ የፍቅሬን መምጣት ጸጥ ብለው ተቀምጠው ይጠብቁ ነበር። ጨለማ በሆነ ጊዜ፣ አዲስዋ ጨረቃ ከመውጣትዋ በፊት ይመጣል።

እርሱ የመጣው በጣም ጨለማ በሆነው የመንገዱ በኩል ነበር፣ እንደ ሌባ ቀስ ብሎ በገባ ጊዜ ምሕረት በድንጋጤ ወደ ላይ ዘለለች። ማንም አልተናገረም። ያንቀላፋውን ተክሌን አነሣውና በፍጥነት መንዝ ስለሚኖርበት ጀርባው ላይ አድርጎ በማዘያ አዘለው። ምሕረት ወደ ማኒላ መለስ አለችና አሻቅባ ተመለከተቻት፤ ለአንድ አፍታም ተቃቀፉ። ከዚያም ወደ መንገዱ ተያይዘው ወጡ።

«ሁሉም ነገር መልካም ነው፣» ሲል ፍቅሬ አንሾካሾከ። «የእኅቴን ባል አግኝቼዋለሁ፣ እርሱ ሁሉንም ነገር ያውቃል። እኔ ከእንቺ ጋር ብዙ ርቄ መሄድ አይኖርብኝ ይሆናል። ጎሕ ሳይቀድ መመለስ እንዳለብኝ ነግሮኛል፣ ነገር ግን በዚያ ጊዜ የጭነት መኪናው ቀጥ ብሎ ወደፊት ይጓዛል።»

«በእግዚአብሔር እርዳታ እንደርሳለን፣» ስትል ምሕረት አጉተመተች። በወላጆችዋ ልብስ እንዲሁም ከበላይ በደረበችው የራስዋ ባርኖስ የበለጠ ወፍራም መሰለች፣ ነገር ግን ሌላው ቢቀር ሞቆአታል። ምግቡንና ውኃውን በጀርባዋ ተሸክማለች፤ የገንዘብዋንም ቦርሳ በወገብዋ ታጥቃዋለች። እስከ አሁን እጅግ መልካም ነው፣ ነገር ግን ተክሌንም ጨምራ የማዘሉ አሳብ እያስፈራት ነበር።



ከከተማው ክልል ውጭ ስለምትኖር፣ ብዙም ሳይዘገዩ በገላጣው ሰፍራ ላይ ነበሩ። ስለዚህም ፍቅሬ የት እንደሚሄድ በትክክል ያውቅ ነበረና በኮረኮንቹ ደረቅ መሬት ላይ ተደናቅፋ እንዳትወድቅ ክንዷን ያዛት። ከመንግሥት ግዛት ምግብ የሚያመላልሱ የጭነት መኪናዎች በፍጹም ወደማይዘልቁበት፣ ረሃብ ወዳለበት የነፃነት ታጋዮች ክልል የሚሄድ ማንኛውም ሰው እንዳይሻገር ለመከልከል የእኅቱ ባል ጠመንጃ ይዞ በሆነ ጉብታ ላይ ይጠብቃል። በጸጥታ ተጓዙ፣ ደግሞም ተክሌ በእንቅልፍ ላይ ነበረ። ራቅ ብሎ ከበስተ ግራቸው፣ አሁንም በደበዘዘ መልኩ ብርሃን ከሚታይበት ምዕራባዊ ሰማይ በተቃራኒ የስደተኞች መጠለያዎች ጥቁር ቀለምን እንደ ተላበሱ ከምችት ብለዋል። ነገሮች አሁን የተሻሉ ሆነዋል፤ ከዋናው ከተማ የሆኑት ተሳቢ ያላቸው የጭነት መኪናዎች ምን እንደ ተከሰተ ገና እየተገለጠላቸው ካሉት ከመላው ዓለም አገሮች የምግብ አቅርቦትን እያመጡ ነበር። ነገር ግን በግራጫማው መቃብር ውስጥ ያሉ ማብቂያ የሌላቸው ቁልሎች የመሰከሩትን፣ ደግሞም ምሕረት የዘገነናት ክስተትን ሰማወቅ፣ ዓለም የነቃችው እጅግ ዘግይታ ነበር።

የረሃቡ ታላቅ ወረራ የጀመረው የመጨረሻው ዝናብ በነሐሴ ወር ላይ ሙሉ በሙሉ መዝነብ ባልቻለበት ጊዜ ነበር። ሰዎቹ ማሽላቸውንና ገብሳቸውን እንዲሁም ባቄላቸውን፣ ከሞላ ጐደል በደረቅ መሬት ላይ ማለት ይቻላል፣ ዘርተው ነበር፤ ነገር ግን ምንም መከር አይኖርም። ከሚያዝያ የበልግ ዝናብ ጀምሮ ምንም መከር አልነበረም። በቆሎው ከመብቀሉ በፊት አቧራማ በሆነው መሬት ውስጥ በሰብሶ ቀረ። በሬዎቻቸውን ሸጠዋል ወይም አርደው በልተዋቸዋል፣ እንዲሁም ዘራቸውን እንኳ ተመግበውታል፣ አሁን ምንም የሚታይ የወደፊት ተስፋ የለም፣ ስለዚህም የምግብ አቅርቦት አሁንም ወደሚገኝባቸው ወደ ከተማዎች በሺህዎች የሚቈጠሩ ሆነው መጥተዋል። ከምሥራቅ ተራሮች የሆኑቱ ኵሩ የሆኑቱ ጐሳዎች ሳይቀሩ እንኳ መጥተዋል፣ ምክንያቱም ከብቶቻቸው፣ በጎቻቸው እና ፍየሎቻቸው እንዲሁም ግመሎቻቸው ከረሃብና ከውኃ ጥማት የተነሣ አልቀውባቸዋል። በእነዚያ ቀናት ትርፍ የሆነ እህል አልነበረምና የሚሰጧቸው ምንም ነገር አልነበ

ረም፣ ነገር ግን እነርሱ ገና ይመጡ ነበር። ምሕረት አይታቻቸው ከነበሩ ነገሮች መካከል ላለማስታወስ ከአእምሮዋ ለማስወጣት ሞከራ ነበር፣ ነገር ግን አልቻለችም፤ በአእምሮዋ ውስጥ ታትመው ለዘላለም እንደሚኖሩ ታውቅ ነበር።

በመጡበት ወደ አገራቸው ተመልሰው እንዲሄዱ የተነገራቸውንና ሲመጡ የጣሏቸው ዱካቸው ላይ በአቧሯው ሞተው የቀሩትን ወይም ወገኖቻቸው ትተው ወደፊት የገሰገሱትን ታስታውሳለች። በትውስታዋ ውስጥ ዘግይቶ የመጣው ዝናብ አቧራማውን መንገድ ወደ ጭቃማነት እንዲሁም የተሸረሸሩ ቦታዎችን ወደ ትልቅ ቦይነት እንደ ለወጣቸው ልትመለከት ትችላለች። በዚያ ጭቃ ውስጥ ለማረስ ሰዎቹ እጅግ ደካሞች ነበሩ፤ ውኃ በቋጠሩ መሬቶች ውስጥ እየወደቁ ይሞቱ ነበር። የምግብ አቅርቦቱ በሚገኝበት ጊዜ ለመኖር የመረጡ 150 ሰዎች በጉሮኖ ውስጥ የምግብና የውኃ ቀለባቸውን እየወሰዱ ራሳቸውን ማጉራቸውን ከቶ ልትረሳው አትችልም። ነገር ግን ከዚያ ጉሮኖ ውጭ ሦስት ሺህ የሚሆኑ ሰዎች ቆመው ይመለከቱ ነበር፤ ዓይኖቻቸው ወደ ውስጥ ተሰርጉደው ነበር። ይሁንና፣ ማንም የተዋጋ ወይም ሲቃ የያዘው አልነበረም። የተጨቈነ ሕዝብ በዕድሜ ጠገብ ትዕግሥት የልጆቻቸውን የደከመ ማቃሰት እያባበሉ፣ አይቀሬ የሆነውን እየተቀበሉ፣ ለመቋቋም እጅግ ደክሞአቸው ዝም ብለው ቆመው ይመለከቱ ነበር።

በከተማ አቅራቢያ ሲሽሎኮለኩ ትመለከታቸው ነበር። ጠጕራቸው እየተሰባበረ ረገፈ ወይም ወደ ቀይነት ተለወጠ፣ ቆዳቸው ገረጣ እና ተሸበሸበ፣ ዓይኖቻቸው ደግሞ ፈዘዙ። አሳዛኝ ዕድሜ ጠገብ የሆኑት የተጨማደዱ ፊቶች ያሏቸው ከመደበኛው ክብደት በታች በሆኑ ልጆቻቸው እጅግ ልባቸው አዝኖአል። ከፍ ያሉ ልጆችም ይህንኑ ተከትለዋል - ትልቅ የተነፋ ሆድ እና እንዲሁም እንደ ክብሪት እንጨት የቀጠኑ እጆችና እግሮች ነበሩዋቸው። እያቃሠቱ በአፍንጫቸው ይምጉ ነበር፣ ነገር ግን እያለቅሱም ነበር። የሚያስለቅስ ነገር አልነበረም፣ ደግሞም ያንን ማድረግ ብዙ ጥረትን የሚጠይቅ ነበር።



አንዳንዶች በመንገድ ዳር ባሉ በአቧራ የተሸፈኑ ድንኳኖች ውስጥ ተጠልለው ነበር፣ ሌሎች ደግሞ በችኮላ በተሠሩ ዳሶች ውስጥ ተጠልለው ነበር። ሌሎች የድንጋይ ግድግዳ በሚመስሉ ጉድጓዶች ውስጥ ራሳቸውን አገሩ። ዋሾቹ በሚያስመርር መልኩ ስለሚቀዘቅዙ ከመንጋቱ በፊት ብዙዎች ይሞቱ ነበር። ምሕረት ምን ያህል ሰዎች እንደ ሞቱ አታውቅም። በምድር ላያ ያሉ የመቃብር ቁልሎች ማብቂያ የሌላቸው ይመስላሉ፣ ደግሞም እነርሱን ተርበው እየጠበቁ ያሉ ጥንብ አንሣዎችና ጅቦች ባሉበት በመንገድ ላይ የሞቱትን አይጨምሩም፤ ያ ሕግ የሆነበት ምክንያት አሁንም በሕይወት ያሉት ሰዎች የተሰነጣጠቀውን ስፍራ ጫር ጫር ከማድረግ በላይ ስለ ደከሙ ምንም ሊያደርጉ አይችሉም ነበር።

አዎን፣ ምግቡ አሁን እየመጣ ነበር፣ ነገር ግን ከከተማ ውጭ ያሉ ሰዎች ወጥተው ለመውሰድ ተመልሰን ከቶ አንመጣም ሲሉ በመፍራት ተስፋ ቈርጠው ነበር። ስለዚህ ብዙዎቹ ልክ እንደ ወላጆችዋ በጭነት መኪናዎች ተጭነው መሣሪያ ተደግኖባቸው ተወሰዱ። እርሱ ወጣት እና ጠንካራ ስለ ነበረ፣ አጐትዋም እንደዚሁ እንደ ተወሰደ ታስባለች። ምናልባት አዛውንት የሆኑ አያቶቿ ካልሆኑ በቀር በዚያ ማንም አልነበረም። ሽክሟን አነሣችና መጓዝ ጀመረች።

እጆችዋን ጠበቅ አድርጎ እየያዘ፣ «ፈጠን ብለሽ ነይ፣» ሲል ፍቅሬ አንሾካሾከ። ምንም እንኳ ድቅድቅ ጨለማ ቢሆንም ለመፍጠን ሞከረች፣ ነገር ግን ፍቅሬ የድመት ዓይኖች ያሉት ይመስል ነበር፤ ትናንሾቹን የእግር መረማመጃ መንገዶችን እንኳ ሳይቀር ያውቅ ነበር። በድንገትም ጕዞውን አቆመ። «አሁን፣» ሲል ተነፈሰ፣ «ጸጥ ብለሽ ወደፊት ሂጂ» አለ።

ከጥቁሩ ለማይ ፊት ለፊት የጥበቃ ቅርጽ ያለው ነገር ጥቁር መስሎ ይታያል። ፍቅሬ ወደ አጠገቡ ዓይኑን ጣለ ደግሞ ጥቂት ቃሎችን ተለዋወጠ። ከዚያም ወደ ፊት እንድትጓዝ እየጠየቃት ተመለሰ። «ሁሉም ነገር ደኅና ነው፣» ሲል አንሾካሾከ፣ «ነገር ግን መፍጠን አለብን። የቀኑ ብርሃን ከመውጣቱ በፊት መመለስ

ይኖርብኛል::»

በጸጥታ እየፈጠኑ ተጓዙ፣ ከዚያም አዲስዋ ጨረቃ በተራራው አናት ላይ ወጣች:: ብሩህ የሆነ ቀዝቃዛማ ምሽት ነበር፣ ደግሞም ከዋክብቶቹ በድምቀት ያንጸባርቁ ጀመር:: ጥልቀት ያለውን ቦይ እየተሻገሩ ነበር ደግሞም ፍቅሬ ፋኖሱን አበራው:: «እኛ አሁን በተዋጊዎቹ ግዛት ውስጥ በደኅንነት አለን» አለ:: «ወታደሮቹ እዚህ አይመጡም፤ አሁን በመጠኑ ቀስ ብለሽ መሄድ ትችያለሽ:: ትንሽ ብርሃን በሻካራው መረማመጃ መንገድ ላይ ስታንጸባርቅ ማየት መልካም ነበር:: ምሕረት የበለጠ ጸጥ ብላ ትተነፍሳለች፣ ደግሞም የልብዋ ምት ግልቢያውን አቊሟል:: ከዚያም ፍቅሬ መናገሩን ጀመረ::

«አብሬሽ ብመጣ ብዬ እመኛለሁ፣ ምሕረት፣» አላት፤ «ነገር ግን ያ ማለት ሊመግቡት የሚገባ አንድ ተጨማሪ አፍ ማምጣት ነው፤ ከዚህም ባሻገር፣ የአንድ ዓመት ትምህርት ይጠብቀኛል፣ ደግሞም ስለ ወደፊት ኑሮአችን ማሰብ ይኖርብኛል:: ትምህርቴን እጨርሳለሁ፤ ከዚያም አንድ ምሽት እመጣና በተራራው ላይ ከተዋጊዎቹ ጋር እቀላቀላለሁ:: ከጥቂት ወራት በኋላ እመጣና አገኝሻለሁ:: በዚያን ጊዜ፣ እባክህ እግዚአብሔር ሆይ፣ ዝናብ ይዝነብ፣ የገዛ ራሳችንን መሬት እና በሬዎች ገዝተን እናርሳለን፤ ከሚከፈቱት ትምህርት ቤቶች በአንዱ አስተምራለሁ፣ ደግሞ ተክሌም ይማራል:: ምሕረት፣ ሕይወት አንድ ቀን እንደገና መልካም ይሆናል:: ተስፋ በማድረግም እንጠብቃለን::»

ሊደረግ የሚገባው ነገር የሚደረግበት መንገድ ይህ አልነበረምና ፊትዋ ከሰለ:: ወላጆች ጋብቻን ያዘጋጃሉ፣ ደግሞም ያደገችው ይህን ባህል እያከበረች ነበር:: ከዚያም አሁን ወላጆች በዚያ እንዳልነበሩ፣ አልፎ አልፎ በሚሰማ የጅብ ጩኸት እና የወፎች ጫጫታ በሚቋረጥ በሰፊው ጸጥ ያለ ደን እና በከዋክበት ብርሃን የደመቀ ጨለማ ውስጥ እርሷና ፍቅሬ እንዲሁም ተክሌ እንደ ነበሩ አስታወሰች:: እዚህ ለወግና ለደንብ ስፍራ አልነበረም:: አጨባበጥዋን በክንዱ ላይ ጠበቅ አደረገች፣ መፍራትዋንም አቆመች::



«እጠብቅሃለሁ፣» አለችው:: «ነገር ግን ወደ ምዕራብ መሄድ ግድ የሆነብንስ እንደሁ? ብዙዎች ድንበሩን ሁሉ አልፈው እንኳ ተጉዘዋል:: እንደገና የማገኝህ እንዴት ነው?»

«አንድ ቀን ዝናቡ ይዘንባል፣» ሲል መለሰ:: «አንድ ቀን ሕያው የሆኑት ወደ መሬታቸው ተመልሰው ይመጣሉ:: አንድ ቀን ተራራዎቹ (ጋራዎቹ) እንደገና አረንጓዴ ይሆናሉ፣ ደግሞም መከሩ ይሰበሰባል:: መንደሮችሽን እጐበኛለሁ፣ ደግሞም እግዚአብሔር ለከፋ ነገር አሳልፎ አይሰጠንም::»

ስለ ቤተሰብዎችዋና ስለ ኀዘናቸው አሰበች፣ ደግሞም እግዚአብሔር ቀድሞውኑ ለከፋ ነገር አሳልፎ ሰጥቶአቸዋል ለማለት አፍዋን ከፈተች፤ ነገር ግን ፍቅሬ ከልቡ የተለጠ አማኝ ስለ ነበረ፣ ደግሞም ከታወቀ ካህን የተማረ ሰው ስለ ነበረ፣ ቃሎችዋን መልሳ ዋጠቻቸው:: ከዚህም ባሻገር፣ እርሷ እንደ ተሠቃየችው እርሱ ገና አልተሠቃየም::

ጥልቀት ወዳለው ቦይ ደረሱ:: መጓዝ አቆሙና ተክሌን ተኝቶ ሳለ ከፍ አደረገውና ከጀርባው አወረደው፣ በአንቀልባው አድርጎ በምሕረት ጀርባ ላይ አደረገው፤ ከዚያም እህሉን እና አልባሳቱን እንዲሁም የውኃ መያዣውን በማስተካከሉ ረገድ ረዳትና በትከሻዋ ወይም በወገብዋ ላይ አደረገላት:: በክብደቱ ብዛት ለትንሽ ጊዜ ያህል ተንገዳገደች፣ ነገር ግን ራስዋን አስተካከለች:: ከዚያም ሁለተኛውን ፋኖስ አበራውና አቀበላት:: እራሷም ከፍ አድርጋ ያዘችው ደግሞም መንገዱ በቀላሉ የምትሮጥበት እና ከፊት ለፊትዋም ልትወርደው ያለ ቁልቁለት መሆኑን ተመለከተች::

«ተመልሼ መሄድ አለብኝ» አለ፣ «አለበለዚያ ቀኑ ከመጀመሩ በፊት ከተማ መድረስ ከቶ አልችልም፣ ደግሞም ካዩኝ ይተኩሳሉ:: መንገዴን ሁሉ እየሮጥሁ መሄድ ይኖርብኛል:: አሁን መንገድሽ ቀጥ ያለ ነው:: እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ይሁን:: ምሽቱ ከመጀመሩ በፊት እዚያ ትደርሺያለሽ::»

ጐንበስ አለና እጆችዋን ሳመ፣ ደግሞም ዓይኖቹ በዕንባ እርሰው ተመለከተች:: ነገር ግን ምስጋናዋን እንኳ በሹክሹታ

ከመናገርዋ በፊት፣ በፍርሃት ተመልሶ ሄዶአል፣ ደግሞም እርሱ በፍጥነት እየሮጠ ስለ ነበረ ትንሿን የማትንቀሳቀስ ብርሃንን ስመመልከት ቆመች:: ልታየው የምትችልበት ሁኔታ እስኪያበቃ ድረስ ተመለከተችው፣ ከዚያም ወደ ትልቁ የምሽቱ ብቸኝነት ተመለሰች::

በጊዜ ለመድረስ ታገለች፤ ነገር ግን፣ ተክሴን ረጅም መንገድ ማዘል እንደማትችል ታውቃለች:: የልጁ፣ የውኃው እና የእህሉ ጣምራ ክብደት ለእርሷ ከባድ ነበሩ:: የመጀመሪያዋ ብርሃን እንደ ወጣች ተክሌ በእግሩ መጓዝ ይኖርበታል፣ ደግሞም ያ በጣም ያንቀረፍፋቸዋል:: ከተራራው ጥላ ወደ አቀበታማ ጉብታ ወጣች:: ደግሞም ከአፍታ በኋላ ዕረፍት ለማድረግ በዐለቱ ላይ ተቀመጠች፤ ጥቂት ውኃ ጠጣች ደግሞም ሰፊ ወደ ሆነው የምሽቱ ሰማይ ተመለከተች:: ከዋክብቱ በጽናትና በድምቀት ይንቀሰቀሳሉ (ያንጸባርቃሉ)፣ ደግሞም እንዳሰበችው በጣም ጨለማ አልነበረም:: በከፊል እንቅልፍ ላይ ሆና ትውስታዋ በሕይወትዋ እጅግ መጥፎ ወደ ሆነው ወደ ትናንቱ ምሽት ይጐትታት ነበር:: ይሁንና . . . እርሷ የማኪላን ደግነት፣ ጐረቤቶቿ ያመጡላትን ትንሽ ስጦታ፣ እምነት የተሞሉ ጥብቅ አድርገው የሚያቅፉ የተክሴን እጆች እንዲሁም የፍቅሬን ጽኑ ድፍረትና ፍቅር ታስታውስ ነበር:: ወዲያውም ማንንም ማግባት እንደ ሌለባት፣ ደግሞም እርሱ ፈልጎ እንደሚመጣ ቃል የገባላት መሆኑን ተገነዘበች:: ምናልባት እርስዋ የገጠሙትውን ያህል አልጨለመም ነበር፣ ምሽቱ እየጨለመ በሄደ ቁጥር፣ ከዋክብቶቹ ብሩህ እየሆኑ ሄዱ:: ተክሴን ወደ እቅፍዋ ሳበችው፣ በዐለቱ መጠለያ ውስጥ ተዘረጋች እና እንቅልፍ ወሰዳት::

ወዲያም፣ በከፊል በቅዝቃዜው ምክንያት ደግሞም በከፊል በብርሃኑ ምክንያት፣ ከእንቅልፍ ነቃች:: በእንቅልፍ የከበዱ ዓይኖችዋ ከሞላ ጐደል ብሩህ በሆነው የምሥራቅ ብርሃን አንጸባርቋል:: እነዚያ በዙሪያዋ የነበሩ እንግዳ ጠመዝማዛማ የሆኑና ወጣ ገባ የሆኑ የዓለቶች እናቶች እና ገደሎች፣ በዚያ አስደናቂ በሩህነት ውስጥ ያሉ ቀይ እሸዋና ጥቁር ድንጋይም ጭላንጭል



ብርሃን እየሰጡ በታላቅ የወንዝ ሸለቆና የወንዝ ውኃ መፍሰሻ ተቈራርጠው የፀሐይዋ ብርሃንን ተጋፍጠዋል:: ነገር ግን ከፊትዋ ትልቁ ጉብታ ወደ አባጣ ጐርባጣው፣ ጠፍጣፋ ጣሪያ ወዳለው ዓቀበት እና አረንጓዴ ሊሆኑ የተገባቸው ነገር ግን አሁን ግራጫማ የሆነ አቧራ ተነባብሮበት እና የተጋገረ ጓል ሆኖ ወደ ሸለቆዎች በቀስታ ይወርዳል::

ባዕድ ከሆነው የማይታይ ነገር በፊትዋ ወዳለው ቀን ወቅታዊ ችግሮች ተመለሰች:: ተክሌ፣ ቢያንስ ለተወሰነ ጊዜ፣ መራመድ አለበት፣ ምክንያቱም ለረጅም ጉዞ ልትሸከመው አትችልም:: ቀሰቀሰችውና የሚጠጣ ውኃ እና የተጠቀለለ እንጀራ ሰጠችው:: ነገር ግን እርሱ ያንቀላፋ፣ ይጨነቅና ቅዝቅዝ ያለ እንዲሁም ራሱን ለመርዳት በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ነበር:: በመጨረሻም ሸክሞችዋን አነሣችና ሄደች፣ እርሱም እየተነጫነጨ ተከተላት:: እርስዋ ልብ አላለችውም፣ ጉዞዋን ቀጠለች፣ እርሱም እያነፈነፈ በበስተኋላዋ ተከተለ እያለቀሰና እየተንሰቀሰቀ ነበር፣ ምክንያቱም ምንም አማራጭ አልነበረውምና:: በዚያ ሰፊ እንግዳ ስፍራ ብቻውን ለመቆየት አልፈለገም::

ፀሐይዋ በከፍታ ወጣች ደግሞም ቀኑ ሞቀ፣ ነገር ግን የተራራው አየር ጸጥ ረጭ ያለና ቀዝቃዛ ነበረ ደግሞም የእግር መተላለፊያው መንገድ የተያያዙ እርከኖች ወደ ታች የሚወርድበት ነበር:: ባለፉት ዓመታት ጐራ ተብሎባቸው መስተንግዶ የሚገኝባቸው የነበሩ የተበታተኑ መኖሪያዎችንና ትናንሽ መንደሮችን አልፈው ሄዱ:: ነገር ግን መንደሮቹ በረሃማ ሆነው ነበር፣ እርሻው አቧራማ እና ቀምቀሞ ሆኖአል:: በመካነ መቃብሮች ያሉ ማብቂያ የሌላቸው ጉብታዎች፣ እና እልፎ እልፎ የሚገኙት የፍየሎች እና የከብቶች ዓጽሞች ብቻ ታሪኩን ይናገራሉ::

ምሕረት መንገዱን ታውቀዋለች፤ ትንሽ ልጅ ሆና ሳለ የሰንበሌጥ ቍጥቋጦ ቅጠል በሚያወጣበት እና ወንዞች በውኃ በሚሞሉበት ጊዜ፣ ዓቀበቶቹ በሰብሎች አረንጓዴ በሚሆኑበት ጊዜ፣ ደግሞም እርግቦችና ብሩህ የፍቅር ወፎች በባሕር ዛፍ ውስጥ ሆነው በሚዘምሩበት ጊዜ እዚህ ብዙ ጊዜ ኖራለች:: አንድ ጊዜ ታላላቅ

ዛፎች በጉርፍ ውኃ ከሥራቸው የተነቀሉበት ደረቁን የወንዝ መውረጃ መሻገር ነበረባቸው፤ እዚያ ከአንድ ጥልቀት ያለው ቧንባ-አልባ ምንጭ እንክብካቤን የሚያገኙ ትናንሽዬ የአረንጓዴ መስክ ደሴቶች ነበሩ:: እዚሁ ዐረፉ፣ ውኃ ጠጡ፣ ደግሞም ጥቂት ተጨማሪ እንጀራ ተመገቡ::

«በቅርቡ እዚያ እንደርሳለን፣» አለች ምሕረት:: «አንተ አሁን ትልቅ ሰው ነህ:: ትንሽ ተጨማሪ መንገድ መጓዝ ትችላለህ::»

በስተዚያ ያለው ኮረብታ ቀጥ ያለ ዓቀበት ሆኖአል:: ተክሌ ትንሿን ለንቦጩን አንጀላጀለና፣ «እዘይኝ፣» ሲል ተነጫነጨ:: «እግሮቼ እጅግ ደክመዋል» አለ::

«አይሆንም፣» ስትል ምሕረት መለሰች:: «ዓቀበቱን እራስህ መውጣት አለብህ:: እላይ ስንደርስ፣ አዝልሃለሁ፣» አለችው::

ፀሐይዋ ወደ ምዕራብ ማሽቆልቆል ጀምራለች፣ ጨለማም ቶሎ ይመጣል:: ቀኑን ሙሉ በምሕረት ልብ ውስጥ የነበረው ፍርሃት እያደገ መጥቷል፣ ምክንያቱም ማንንም አላገኙም - እያንዳንዱ መንደር ተራቁቶአል፤ እያንዳንዱ የወንዝ ውኃ መውረጃ ደረቅ ሆኖአል:: ሴት አያትዋ ሄደውስ ከሆነ! ባዶ የሆነ መንደር እና እጅግ የተንሠራፋ መቃብር ቢያገኙስ! አሁኑን ሄደው ማየት ብቻ ነው የሚችሉት:: የውስጥ መረበሽዋን እየተዋጋች፣ ላላ ባሉ ድንጋዮች እየተወላከፈችና ተክሌን እየጎተተች ይህን የቀን ቅዠት ማሰቡን ለማስወገድ እየጣረች ዓቀበቱ ላይ ወጣች:: አያትዋ ከቶ ከማይደርቅ በረዶ ከሚተኛበት ደግሞም ደኖች ከሚያድጉበት ከከፍታ የሚፈስስ ውኃ ካለበት ወንዝ አጠገብ ነበር የሚኖሩት:: በእርግጠኝነት እሁንም እዚያ ይገኛሉ!

በኮረብታው አናት ላይ ተክሌን በጀርባዋ አዘለችውና ወዲያው እንቅልፍ ወሰደው፤ በደከመ ሰውነትዋ ላይ የሙት ያህል ክብደት ተጨመረበት:: የመጨረሻውን ግራጫማ ያጋደለ ስፍራ እየወጣች ሳለ ደግሞም መንደሩን በጕጕት በምትመለከትበት ጊዜ ከሞላ ጐደል ፀሐይ እየጠለቀች ነበር::

መኖሪያዎቹ እንዳሉ ቆመዋል:: እርሻዎቹም በደንብ አርረዋል፤



ነገር ግን በጐጆዎቹ ዙሪያ ትናንሽ አረንጓዴ ተክሎች ነበሩ፣ ደግሞም ገና በምሽቱ አየር ላይ ጢስ ይወጣ ነበር:: ራቅ ብሎ በሸለቆው ውስጥ እየደረቀ ያለው ወንዝ ጭላንጭል ይታያል:: ገና የምትጓዘው ጥቂት መንገድ ነበራት፤ ነገር ግን፣ በዚህ ሸለቆ ውስጥ ሰዎች ይኖራሉን:: ምናልባት ይረዱዋት ይሆናል:: እየተንገዳገደች ወደ መጀመሪያው እሾሃማ ጉረኖ ሄደች:: ደግሞም በዚያ በአቧራማው መሬት ላይ፣ የምሽት ምግባቸውን ለማብሰል የጐደጐዱ ዓይኖች ያሏቸው ልጆች የነበሯቸው የጐደጐዱ ዓይኖች ያሏቸው ቀጫጭን ሴቶች ትንሽ እሳት እያነደዱ ነበሩ፣ ነገር ግን ደጎች ነበሩ:: አንዳንዶቹ ከሁለት ማይል ርቀት ከወንዝ በአቁማዳ ውኃ ይዘው የመጡ ናቸው፤ ሌሎቹ ሴቶች ደግሞ እጅ ሙሉ የሚሆኑ ሥሮችን፣ ደረቅ ዘሮችን ወይም ሳሮችን ይዘው የመጡ ናቸው:: ታሪኳን አዳመጡ፣ አዘኑ ነገር ግን አልተገረሙም::

«ብዙዎቹ ወንዶቻችን ወደ ተራራ ወጥተዋል፣» አሏት:: «ብዙዎቹም፣ እንደዚሁ ልክ እንደ ወላጆችሽ ተወስደዋል:: አያቶችሽ አሁንም በሕይወት አሉ:: ከልጆቻችን አንዱ ልጁን ዓቀበቱን ያሻግርልሻል:: ሩቅ አይደለም::»

ፀሐይዋ ከኮረብታው አናት ወደ ኋላ እየሸሸች ሄደች፣ ደግሞም ጨለማ በፍጥነት መጣ:: ወደሚቀጥለው እጅብ ያሉ ጐጆዎች በመጨረሻው ብልጭ ድርግም የሚል ብርሃን ደረሱ:: ደግሞም ስማቸውን በምትጠራበት ጊዜ አያቶችዋ እየሮጡ መጡ:: መሬታቸው ባዶ እንደ ሆነና ፊታቸው የከሳ እንደ ነበረ ልብ አላለችውም:: እጆቻቸው በዙሪያዋ እንዳሉና እቤት እንደ ደረሰች ብቻ ነው የተሰማት::

ከዚያም፣ ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ምሕረት አለቀሰች::

# 4

ተስፋዬ እና ሙና በመሬት ላይ በጣም ተቀራርበው ተቀምጠዋል:: ሌሎች በዙሪያቸው ተቀምጠዋል፣ ነገር ግን ማንም የሚናገር አልነበረም፤ ምክንያቱም ምንም የሚያናግር ነገር አልነበረም፣ ወቅቱ ረፋዱ የከሰዓት በኋላ ነበር፣ ደግሞም በአቅራቢያው ባለ የአየር ማረፊያ ላይ በሄሊኮፕተር ድምፅ ጸጥታው ተገፈፈ:: ምናልባትም ለዘላለም ስለ ተዉአቸው ትናንሽ ቤቶች እና ቤተሰቦች ካልሆነ በቀር፣ ሰምንም ነገር ፍላጎትና አሳብ የሌላቸው በመሆናቸው፣ እዚህ ግባ በማይባል መልኩ ያዩትን እየቀረጹ በፈዘዘ ሁኔታ ተመለከቱ::

የሄሊኮፕተሩ በሮች ሲከፈቱ እና መንገደኞች ሲወጡ፣ ለጥበቃ ወታደሮች ጠመንጃቸውን አቀባበሉ:: ከዚያም፣ የቱም ሄሊኮፕተር እጅግ ብዙ ተንገኞችን ከዚህ በፊት ይዞ አያውቅምና፤ ደግሞም እነዚህ ሰዎች ተስፋ የቈረጡ እና የታመሙ ስለ ነበሩ፣ ተመልካቾቹ ዓይኖቻቸውን ከፀሐይ ብርሃን እየሸፈኑ በእውነተኛ ጉጉት ፈዝዘው ያዩ ነበር:: ወንዶች ሴቶችንና የሚያለቅሱ ደግሞም የተረበሹ ጥቂት ልጆችን ይረዱ ነበር፤ አንዳንድ ሰዎች ገና መሬት ላይ እንዳረፉ ያስታውካሉ:: አንዳንዶች ይበርሩ ይመስል በስፋት ዙሪያውን ይመለከታሉ፣ ነገር ግን ጠመንጃዎቹን እየተመለከቱ፣ መስመራቸውን ይዘው ይተኛሉ ደግሞም በመሬት ካሉ ቡድኖቻች ጋር ለመቀላቀል ይታገላሉ፣ እንዲሁም ከአጠገባቸው ቁጢጥ ወይም ጋደም ይላሉ::

«ምግብና ውኃ፣» ሲል ጮኸ አንደኛው ሰውዬ፣ ደግሞም በሜዳው ሁሉ በጥር እንኳ ፀሐይ ታቃጥል ነበርና ጩኸቱን በዚያ የተሰበሰበው ሁሉ ሰው ተቀበለው፣ ደግሞም ምንም ጥላ አልነበረም::



አንድ ጠባቂ ወደ ፊት መጣና አንድ ከባድ መኪና መጥቶ ከኋላው ቆመ:: ከኋላው በተከፈተ ጊዜ፣ በዚያ የተሰበሰቡት ሰዎች በብርድ ልብስ የተሞላ እንደ ነበረ ተመለከቱ፤ ደግሞም ሁለት ፈረንጆች ወንዶች ካሜራ ይዘው ታዩ፣ እንዲሁም ፎቶ ማንሣት ጀመሩ:: ጠባቂው ለሕዝቡ ንግግር ማድረግ ጀመረ::

«ምግብና ልብስ በሌላ አካባቢ ትቀበላላችሁ፣» ሲል ተናገራቸው፣ «በዚያም ምሽቱን ሁሉ ታሳልፋላችሁ:: ነገር ግን፣ ምቾት ተሰምቶአችሁ መተኛት እንድትችሉ እያንዳንዳችሁ ብርድ ልብስ ትቀበላላችሁ:: ብርድ ልብሶቻችሁን ከያዛችሁ በኋላ ተሰለፉና ከኋላችሁ እየጠበቃችሁ ወዳለ የጭነት መኪና ውጡ:: አትፍሩ፤ ጥሩ የሆነ እንክብካቤ ይደረግላችኋል::»

ሙና እያመነታች ተስፋዬን ትመለከተው ነበር፣ ነገር ግን በፊቱ ላይ ምንም ዓይነት የተስፋ ብልጭታ አልተመለከተችም:: ፊቱ ጭር ያለና በአንደበት የሚገለጥ አልነበረም፣ ደግሞም ዓይኖቹ በኀዘን ደንዝዘው ነበር፤ ብርድ ልብሱን ተቀብሎ ከሌሎች ጋር ተመለሰ:: በዚያን ጊዜ በመሣሪያዎች የተከበቡ በመሆናቸው ዕንግዳ የሆነው የማምለጥ ተስፋዋ የማይቻል እንደ ሆነ ተገነዘበች፤ ስለዚህም ከምሕረት እና ከትንሹ ተክሌ እንኳ እጅግ ርቃ ከእርሱ ጋር ወደ ጭነት መኪናው በእግር እየተራመደች አመራች:: በስተጀርባ ያሉ ሰዎች ከመደገፊያዎቹ ተጣብቀው ሳሉ ብዙ ብዙ ሰዎች በጠመንጃና በሰደፍ ይዘው እየገፈተሩ ሲገቡ ሳለ ተንገኞቹ «በቃ፣ በቃ!» ብለው ጮኹ:: ለመተንፈስ አስቸጋሪ ነበረ፣ ነገር ግን መልካሙ ነገር የጭነት መኪናዎቹ ክፍት ነበሩ:: ጥላዎቹ እየረዘሙ ሄዱ፣ ደግሞም ወደማይታወቀው ፍጻሚያቸው እየተንገጫገጩ ሲሄዱ አየሩ ቀዝቅዞ ነበር::

ርቀው የሚሄዱበት አልነበረም:: የጭነት መኪናዎቹ ከአየር ማረፊያው ሳይርቁ ከፍ ወዳለ ተጋላጭ አምባ ላይ ቆሙ:: አሁንም በድጋሚ በመሣሪያዎች ተከብበዋል ደግሞም በአንድ ላይ ታፍነዋል፣ አሁንም በድጋሚ ለምግብና ለውኃ፣ ከጕሮሮነውም ለመውጣት እንዲሁም ራሳቸውን ዘና ለማድረግ ለመኑ:: መልሱም ጮኽ ባለና ግልጽ በሆነ ቃል መጣ፣ «ማንም እዚህ እንዲቆይ

አይገደድም። መሄድ የምትፈልጉ ከሆነ፣ ወደዚህ ኑና ብርድ ልብሳችሁን አስረክቡ።»

ሰዎች ወደ ስፍራው ጭንቅንቅ ብለው መጡና ብርድ ልብሳቸውን በተባለው ስፍራ ሰመወርወር (ለማስቀመጥ) ወደ ፊት እየተመሙ መጡ። ብዙዎች ከሰሜን እንዲመጡ የተደረጉ ነበሩ፣ ደግሞም የሚሄዱበት ስፍራ አልነበረም፣ ነገር ግን በሆነ መልኩ ቤ ት ማግኘት ይኖርባቸዋል። ተስፋዬ ሰሚስቱ ፈገግ አለላት፣ ደግሞም ሙና በደስታ ከሞላ ጉደል ራስዋ ሲዞር ተሰምቶአታል። ከከተማው የጥቂት ሰዓታት የእግር ጉዞ ብቻ ነበር ያስፈልጋቸው የነበረው፤ ከመንጋቱም በፊት ወደ ምሕረትና ወደ ተክሌ ተ መልሰው ይመጣሉ።

ነገር ግን እየሆነ ያለው ምንድን ነው? እስደሳቹ ሩጫ ቆመ። ከፊት ለፊት ያሉት ሰዎች ይከራከራሉ፣ ይለምናሉ፣ ያለቅሳሉ። በደረቱ ላይ በጠመንጃ ሰደፍ በደንብ ተመትቶ የነበረው ሰውዬ እየጮኸ በጀርባው ወደቀ። አሁንም በድጋሚ፣ ጠመንጃዎቹ በእነርሱ ላይ እነጣጠሩ ደግሞም የታጠቁ ሰዎች ከበባ በደከመው ብርሃን ውስጥ በጥቁርነት ቆመ። ያ ቅጽበታዊ የተስፋ ብልጭታ ሞተ፤ የተሰበሰበው ሕዝብ ነገሩ የጭካኔ ቀልድ መሆኑን በተገነዘበ ጊዜ ወደ ተስፋ መቊረጡ ተመለሱ።

ፀሐይዋ በምዕራባዊ ኮረብታ ከፍታ ጫፍ ላይ እያሽቈለቈለች ጠፋች፣ ደግሞም ከበላያቸው ያለው ሰማይ ልክ እንደ የእግዚአብሔ ር ፍርድ በእሳት ተያያዘ ስትል ሙና አሰበች። ወደ ምሥራቅ ዓለታማ በሆነው ኸው ያለ ገደል ውስጥ መሬቱ ወደ ጥላማ በርሃማነት ተቀየረ። ሙና ከማየት ታቀበች፣ ስለ አካላዊ ፍላጎትዋ ኢምንት ያህል ነበር ንቁ የነበረችው፣ ይህም በተስፋ መቊረጥዋ ላይ የሚጨመር ሆነ።

ከዚያም ትንሽ ድምፅ ወደ መንቃት አመጣት፣ ደግሞም ልትመለከት ወደ ኋላ መለስ አለች። ከእርሷ አጠገብ ከምሕረት ብዙም የማትበልጥ ልጃገረድ በተሸበሩ ዓይኖችዋ ውስጥ የመጨ ረሻው ብርሃን እየተንጸባረቀ በሥቃይ ጣር ላይ ነበረች። አንድ



ወጣት ከበላይዋ ተጐንብሶ፣ አስጠሊታ በሆነ መንገድ ይዞአት ነበር፣ እርሱም እንደዚሁ ተሸብሮ ነበር።

ነገሩ ምን እንደ ሆነ ለሙና ሊነገራት አያስፈልጋትም ነበር። በአንድ ጊዜ አወቀችው ደግሞም በቅጽበት በሙላት ተሳተፈችበት፤ ምክንያቱም ለእርስዋ ባዶ እና የታመመ ልብ ይህች ልጅ በዓመት ጊዜ ውስጥ ፍቅሬን ማግባት የነበረባት ምሕረት ናት፡ ደግሞም መንገዱን ወደ ሕይወት ለማድረግ የሚታገለው ሕፃን የገዛ ራስዋ የልጅ ልጅ ነው። በጭንቀትና በኀዘን ግራ ተጋብታ፣ ወደ ወጣቱ በፍጥነት ተመለሰች።

«ምን ያህል ጊዜ ሆነ?» ስትል ጠየቀችው።

ትከሻዎቹን ነቀነቀ። «ሕመሙ ገና አሁን መጀመሩ ነው፣» አላት። «እርሷ ወጣት እና ትንሽ ልጅ ናት፤ ረጅም ጊዜ ሊወስድ እንደሚችል አስባለሁ።»

የእናት የእጅ መንካት የተሰማት ልጃገረድ፣ ወደ እርስዋ ተ መልሳ ተጠጋቻት። ጊዜው ጨለማ እና በሚያስመርር መልኩ የሚቀዘቅዝ ነበር፤ ጠባቂዎቹ ከካባቸው በታች ተሸጉጠዋል፤ መሣሪያዎች ተደግነዋል፤ በእያንዳንዱ ጊዜ ንቁ ናቸው። ከዋክብቶቹ ጠፉ፣ ደግሞም ጨለማው ዘላለማዊ መሰለ፤ ነገር ግን ከልጅዋ ከምሕረት ጋር ስለ ነበረች፣ ደግሞም ምሽቱ እየለቀቀ ሲሄድ፣ ሥቃዩ እየቀነሰ ደግሞም ልጅትዋ በክንዶችዋ ላይ ደክሞአት እንቀላፍታ ስለ ነበረ ለሙና የዕረፍት ጊዜ ነበር።

በበረሃው ላይ፣ በምሥራቁ ባሕር ዳርቻ ላይ እንዲሁም ድንዙዝና ተስፋ ቢስ በሆኑት ምርኮኞች ፊት ላይ ቀስ በቀስ እየነጋ መጣ። እየሩ ትኩስና የሚያበረታታ ሊሆን ይገባዋል። ነገር ግን ማንም ጉረኖውን ለመተው ስለማይፈቀድለትም ይከረፋል። ልጆቹ በደረቁ ከናፍሮቻቸው ከእንቅልፋቸው ነቁ፣ ውኃ እንዲሰጣቸውም አለቀሱ፣ ነገር ግን ሌሎቹ፣ ፀሐይዋ ልትወጣ ነበርና፣ ራሶች በደ ረት ላይ እንደ ሆኑ በጸጥታና እየተንቀጠቀጡ ጠበቁ። ወዲያውም በአድማስ ላይ ዝቅ ብላና በድምቀት ወጣች፣ ነገር ግን ለአዲሱ ቀን ምንም ተስፋ የለም። ልጅቱ ከእንቅልፍዋ በሕመም ውስጥ ሆና

ነቃች፣ ደግሞም በተፋፋመ ምጥ ጮኸች:: ነገር ግን ምጡ አለፈ፣ ደግሞም በጀርባዋ ጋለል አለች፣ እንዲሁም ዓይኖችዋን ከደነች:: ከዚያም በጠባቂዎቹ መካከል ድንገተኛ የሆነ ትርምስ ነበረ:: ደግሞም ሰዎቹ ምግብና ውኃ ለመቀበል እንዲሰለፉ ታዘዙ:: እየከበዳቸው በእግራቸው ተነሡ፣ ደግሞም በባልዋ እና በሙና እየታገዘች ልጅቱም ጭምር መጣች:: ውኃ ጠጣች፣ ነገር ግን ዳቦውን ከቀሚሷ በታች ሻጥ አደረገችው::

የጭነት መኪናዎቹ እየተንገጫገጩ ሲወጡ ሳለ፣ «በመደዳ ተስለፉ፣» የሚለው ትእዛዝ ከፍ ባለ ድምፅ ተሰማ፣ አሁንም በድጋሚ ወደ አየር መንገድ በሚወስድ መኪና ላይ በአንድ ላይ ተደርገው ተጫኑ:: ከፊታቸው ያለውን እንደ ተመለከቱ ፍርሃታቸው በድንገት ወደ የኀዘን ጩኸትነት ተቀየረ:: ወደ አየር ማረፊያው እየተጓዙ ነበር፣ ደግሞም ሁለት ጄት አውሮፕላኖች በራቸውን ክፍት አድርገው እየጠበቁዋቸው ቆመዋል:: የጭነት መኪናዎቹ ቆሙ፤ ጥበቃዎቹ የጥበቃ ሥራቸውን ለማከናወን ቆሙ፤ ሰዎቹ ልክ እንደ በግ መንጋ ወደ አውሮፕላን ተጫኑ፣ ይህም ሁኔታ ቀጠለ:: የመጀመሪያዎቹ ቡድኖች ከአውሮፕላኑ ጋቢና ፊት ለፊት ተጫኑ፣ ሁለተኛዎቹ ቡድኖች በጐን ካሉ መደገፊያዎች ጋር ራሳቸውን እንዲያስጠጉ ተነገራቸው፣ ደግሞም በመሃል ወዳለው ስፍራ ብዙዎች ሰዎች ተደራርበው ታጨቁ:: ሴቶች ልጆቻቸው እየተረገጡ ስለሆኑ ጮኹ፣ ነገር ግን አሁንም ሌሎች ሰዎች ወደ አውሮፕላኑ ገቡ፣ እምቢ ካሉ ደግሞ በዱላ ይመቱ ነበር:: ሦስት መቶ የሚሆኑ ሰዎች ብቻ ሲቀሩ በሩ በላያቸው ተዘጋ ደግሞም አውሮፕላኑ ወደ ደቡብ ተጓዘ::

በረራው አንድ ሰዓት ወሰደ፣ ደግሞም በረራው የቀን ቅዠት ግልቢያ ነበረ:: የአየር ማስተካከያው መሣሪያ አይሠራም ነበር፣ ደግሞም ሰዎች በነፃነት ያስታውኩና ራሳቸውን ይስቱ ነበር:: ልጅቱ አሁንም በሙና እና በባልዋ ተደግፋ ነበር፣ ምጡ የበለጠ እየጨመረ ሲመጣ ትጮኽና ፊትዋ ግራጫማ ይሆን ነበር:: ወዲያውም በታላቅ ድምፅ ጮኸችና በዚያ የሆነ ክፍል እስ ከተባለ በመሬቱ ላይ ተዘረረች:: በሕዝቡ እግሮች ሥር በሆነ ስፍራ ላይ



አዲስ ሕይወት እንደ ተኛ ሙና አውቃለች:: አንድ ጊዜ በሩ ከተከፈተ ሩጫው ወዲያው ስለሚጀመር ወዲያውኑ ይረጋገጥና ይጨፈለቃልና በሆነ መንገድ ልትታደገው እንደሚገባትም ጭምር አውቃለች::

በሆነ መንገድ፣ በሆነ መንገድ! «ወደ ላይ እንሣኝ፣» ስትል ሙና ጮኸች፣ ደግሞ ባልዋ ይህንኑ አደረገ:: እርስዋ ትንሽ ሴት ናት፣ ነገር ግን ሌሎች ወደ ኋላ ሲገፉ፣ በቂ ስፍራ ተገኘ:: ወጣቱ ባል ቁጢጥ ብሎ ሕፃኑን አነሣው:: ደግሞም ሙና ሕፃኑን ለመለየት አስፈላጊ የነበረውን ሁሉ አድርጋለች:: ልጅቷ ወደ ታች ተንሸራተተች፣ ነገር ግን ሕፃኑ ጤናማ ነበር:: አፉን ከፈተና ጮኸ፣ ሙና ደግሞ የአሸናፊነትን ጊዜ ተለማመደች:: እርሱ የምሕረት ሕፃን ልጅ ነው፣ ስለዚህም መኖር ይኖርበታል::

አውሮፕላኑ መሬት ላይ ዐረፈ እና በሮቹ ተከፈቱ:: በትልቁ ድርቅ ላይ ትኩስ የሆነ ተራራማ አየር ነፈሰ:: ፈዝዞና ታምሞ የነበረው ሕዝብ ወደፊት ለመሄድ ታገለ፣ ሙና ሕፃኑን ከራስዋ በላይ አድርጋ ያዘችው:: ነገር ግን እናቲቱና ሌሎች አንድ ወይም ሁለት ሰዎች አሁንም ከታፈገው ሕዝብ እግሮች ሥር ተጋድመው ነበር፣ ደግሞም በተሸፈኑ ቃሬዛዎች ተወሰዱ::

አውጭም፣ ተንገዋች በተሰለፉ ወታደሮች መካከል ወደሚጠብቋቸው አውቶብሶች ተመሙ:: ሌሎች ሰባ አራት የሚሆኑት ቆመው ሳለ ሰባ አራቱ በመቀመጫዎቹ ላይ ተዋጡ:: በኋላም፣ ስፍራ ይቀያየራሉ:: ወጣቱ ባል ተስፋዬን ጠበቅ አድርጎ ይዞ በማልቀስ፣ በሙና ክንዶች ውስጥ ያለችውን ትንሿን ሴት ልጅ ለመመልከት ፈቃደኛ ያልሆነ መሰለ:: ሙና በንጽሕና እየጠራረገች ከገዛ ራስዋ ቀሚስ በተቦጨቀ ጨርቅ በተቀደደ ቁራጭ ጠቅልላ ልትይዛት ጣረች:: ዙሪያዋን ተመለከተች፣ በአንገትዋ ዙሪያ የተንጠለጠለውን መስቀል በጣቶችዋ ይዛ እርስዋን የተዋት ወደሚመስላት ወደ እግዚአብሔር ጸለየች::

አውቶብሱ፣ ትልቁን ዋና ከተማ ከበስተኋላቸው ትቶ፣ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ጉዞውን ጀምሮአል:: ከፊታቸው ካሉ ሁለት

መቀመጫዎች ላይ ሁለት ጥንዶች ተቀምጠዋል፣ ከፊት ለፊትዋ ወደ እርስዋ ዓይን በምሬት ፊዝዛ እየተመለከተች ልጅቱ ታለቅሳለች። ሙና ወደ ፊት ዘንበል አለች እና፣ «ከየት ነው የመጣሽው?» ስትል ጠየቀቻት።

«ከአንቺ ጋር በገበያ ስፍራ ሳለሁ ነው የተወሰድኩት፣» አለች ልጅቱ፣። በግዴለሽነት። ወደ ሙና እንኳ አትመለከትም ነበር፤ ነገር ግን ከፊት ለፊትዋ ፊዝዛ መመልከቷን ቀጠለችበት።

«ልጆች ነበሩሽ?» ስትል ሙና በጨዋነት መረመረቻት።

«አንድ ሕፃን ልጅ አለኝ፤ በተወሰድኩበት ጊዜ ከእናቴ ጋር ነበር።» ለመናገር እንዳልፈለገ ሰው ወደ ኋላ ዞረች። ወዲያውም ወደ ታች አዘነበለች ደግሞም እንባዎች ወደ ታች በነፃነት ወረዱ።

ሙና በቀጥታ ወደፊት ዘንበል አለች እና በጭንዋ ላይ የቆሸሸውን ትንሽ ጥቅል አስቀመጠች። ፍዝዝ ብላ ስትመለከተው እያለመች የነበረች መስላት፣ ከዚያም አንሥታ ወደ ጡቶችዋ ወሰደችው፣ ማልቀስዋንም አቆመች።



# 5

ምሕረት እና ተክሴ ቆዳ ለብሰው ተኝተዋል፣ ደግሞም አያቶቻቸው፣ ስለ ሴት ልጃቸው እያዘኑ፣ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለመወሰን ከአጠገባቸው ቁጢጥ ብለዋል።

«ተመልሰው መሄድ ይኖርባቸዋል፣» አሉ ወንድ አያታቸው። እርሳቸው መላጣ የሆነ ጭንቅላት እና ጭራሮ መሳይ እግሮች ያሉዋቸው ሽማግሌ ሰው ነበሩ። ጕበዝ ገበሬ ነበሩ። ነገር ግን የመጨረሻውን በግምጃ ቤት ያለ እህል ለመግዛት በሬዎቻቸውን ሸጠው ነበር፣ ደግሞም መጨረሻው ሩቅ እንዳልሆነ ያውቁ ነበር።

«ወደ የት ነው የሚሄዱት?» ሲሉ ጠየቁ ሴት አያታቸው። «ለብቻቸው መኖር አይችሉም።»

«በከተማ ምግብ አለ፣ ደግሞም ጐረቤቶቻቸው ደጎች ናቸው። እዚህ የሚቆዩ ከሆነ ይሞታሉ። እኛ ልንመግባቸው አንችልም።»

«እዚህ መቆየት አያስፈልጋቸውም። መንደርተኛው ጥሎ እየሄደ እንደ ሆነ አልነገርሽኝምን? ወደ ምዕራብ መንዝን በተመለከተ ለመነጋገር ነገ ይሰበሰባሉ። ከእኛ ጋር ይጓዙ፣ ከዚያም ጥቂት እልፍ ብለን በአንድነት አዲስ ቤት እንሠራለን።»

ቃኘት አድርጓቸው፣ አሳባቸውን በቃላት ለማስቀመጥ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ። ታውቃለች ብሎ አስቦ ነበርና። «እኛ ሽማሌዎች ነን፣» አለ በጨዋ አናጋገር። «እጅግ ፈጥነን እና እሩቅ ስፍራ እንዴት መሄድ እንችላለን? በመንደሩ ውስጥ አሁንም በመጋዘኑ ያለ ትንሽ በቆሎ አለ። ደግሞም ወደ ወንዝ መድረስ አሁንም እንችላለን። ሽማግሌ ለው መቆየት ይችላል ብዬ አስባለሁ።»

ሴት አያታቸው ራሳቸውን አወዛወዙ። «ልጆቹ እንግዶች

ስለሆኑ፣ ከመንደሩ መጋዘን እህል መመገብ አይችሉም:: እኔ አሁንም ጠንካራ ነኝ ደግሞም በካምፖቹ ውስጥ ያለውን መንገድ መከተል ይኖርብናል:: ሁላችንም በአንድነት እንንገዝ::»

የጉበጠ አሮጊ ጀርባቸውን እየዘረጉ ፈገግ አሉላቸው:: «ፍላጎትሽ ያ ከሆነ፣ እንግዲያውስ እንሄዳለን፣» አሉ:: ምክንያቱም ምንም እንኳ ሴትዮዋ ያረጁና ጥርስ-አልባ ቢሆኑም፣ አሁንም እርሳቸው በጣም ይወድዷቸዋል:: በዚያ በምዕራብ አገር ምግብ ነበረ ይባላል፣ ነገር ግን ጦርነት እና የመንገድ ላይ ዘረፋም ጭምር ነበሩ:: እሻ፣ በጀ! ከድርቅ እና ረሃብ ጋር፣ በተለይ አሁን ሴት ልጃቸው ተወስዳ ሳለ በመንደሮች ውስጥ የሚያጡት ነገር ትንሽ ነበር:: ከዚያም ትኩረታቸው በተኙት ልጆች ላይ ዐረፈ፣ ደግሞም የደከሙ አሳቦቻቸውን ፈተሹ:: ለእነርሱ ሲባል፣ ለተወሰነ ጊዜ መኖር እና ጠንካራ መሆን ይኖርባቸዋል:: እርሳቸው ገበሬ ነበሩ፣ ደግሞም አሮጌ አገዳዎች ዘሩ ከተበታተነና ካደገ ብቻ እንደሚጠወልጉና እንደሚሞቱ ያውቃሉ፤ ነገር ግን ሲሞቱ ሞገስ አላቸው፣ በክብርና ያለ ዐመፅ ነው የሚሞቱት:: በእርግጥ፣ በመጨረሻዎቹ ወርቃማ ቅጠሎች እንኳ ውስጥ ውበት እንዳለ ያውቁ ነበር፣ ነገር ግን ከአዲሱ ብቃይ በቀር ፋይዳ ያለው ነገር የለም:: እርሳቸው እና ሚስታቸው በጠፍር አልጋ ላይ በአንድነት በሰላም ጋደም ይላሉ፣ አእምሮአቸውም ይታደሳል::

ልጆቹ ታድሰውና ርቦአቸው ነቁ:: ምሕረት አሁንም ወዳልደረቀው የወንዝ ፈሳሽ ማለሮዋን አንሥታ ሄደች:: በስብርባሪውና በዓለቱ ላይ በሽሚያ እየወረዱ የሚወስደው በጥሩ እርምጃ ሁለት ሰዓት ነበር፤ ነገር ግን ሌሎች ሴቶችና ልጆች ከእርስዋ ጋር አብረው ሄዱ፣ ደግሞም የተራራው አየር ትኩስ እና ቀዝቃዛ ነበር:: ከፍታ ያላቸው የበረዶ ግግሮች ወደ ወንዙ ውኃ መፍሰሻ ስፍራ የሚገቡ በመሆናቸው ምክንያት፣ እንደ ሌሎች መንደሮች መንደራቸው አልጠፋም ነበር:: ለማረስ ወይም ለመዝራት አልቻሉም ነበር፣ ነገር ግን ወደፊት እና ወደ ኋላ ውኃን በመርጨት በቤታቸው ጥላ ሥር ማሽላ ለማሳደግ (ለማብቀል) ችለው ነበር:: ነገር ግን በዚያን ጊዜ ትልቁ በጭራሮ የተሠራ ገንዳ ባዶ ወደ መሆኑ



ቀርቦ ነበር:: ደግሞም ዝናቡ መዝነብ ካቆመ አምስት ዓመታት ስለሆነው፣ ምንም መከር አይኖርም:: በየካቲት የበልግ ዝናብ የሚመጣ ቢሆን እንኳ ሰብሉ እስኪሰበሰብ ድረስ መኖር አይችሉም:: ምሕረት እና ተክሴ በጊዜው ነበር የደረሱት:: ለቅቆ ለመሄድ ፈቃድ በገሃድ ተሰጥቶአል፣ ስብሰባ ተጠርቷል፣ ደግሞም በዚያ መንደር ያለ እያንዳንዱ ሰው ስብሰባውን ይከታተላል::

ምሕረት ከከተማ ይዛው ከመጣችው ማሽላ በትንሽ እሳት እንጀራን ለመጋገር ቁጢጥ ያሉትን ሴት አያትዋን ለማግኘት ተመልሳ ዓቀበቱን ትወጣለች፤ ደግሞም ወታደር የሆነ ልጅዋ ከአጠገብዋ ባለ የጭቃ መደብ ላይ ጋደም ብሏል:: በተራራው ካሉ ዓማፂ ኃይላት ዘንድ ነበር የመጣው፣ ደግሞም ሌሊቱን ሁሉ ተጉዟል:: ነገር ግን የእኅቱን ልጅ በተመለከተ ጊዜ ተነሥቶ በትሕትና ሰላምታ ሰጣት:: ተክሌ በጭኑ ላይ ሆኖ ክምላ ጉደል ጠመንጃውን በትኩረትና በአድናቆት ይመለከታል::

ሴት አያታቸው እሳቱን አጠፉ፣ ምክንያቱም እያንዳንዱ የእሳቱ ትንታግ ውድ ነበር፤ ደግሞም ትንሿን ቍራሽ ለራሳቸው አስቀርተው እንጀራውን በጥንቃቄ አካፈሏቸው:: እየተመገቡም ሳሉ፣ ይነጋገሩ ነበር:: ልጃቸው፣ ገበሬ፣ የመጣው ጉዞውን ለማቀናጀት እና በሚሄዱበትም ጊዜ ወደ መጀመሪያው ካምፕ ሊመራቸው ነው፣ ምክንያቱም በመንደሩ ውስጥ የቀሩት ወጣቶች ጥቂት ነበሩ:: እርሱ ረጅምና ጠንካራ ነበር፤ ነገር ግን የፊቱ አጥንቶች ገጥጠው ይታያሉ፤ በጣም ቀጭን ነበር:: በእኅቱና በባልዋ ላይ የተከሰተውን ነገር በሚሰማበት ጊዜ ጥቋቁር ዓይኖቹ በቍጣ እበሩ፣ ነገር ግን ልጆቹን ለማጽናናት ሞከረ:: «ሁሉም አይጠፉም፣ ትናንሾች ናቸው የሚጠፉት፣» አለ:: «አንዳንዶቹ በጠረፍ አልፈው ተመልሰው መጥተዋል:: እናንተም እንደዚሁ ጠረፉን አልፋችሁ ማምለጥ ይኖርባችኋል፣ ደግሞስ ማን ያውቃል? አንድ ቀን፣ በአንድ ስፍራ፣ እንደገና ትገናኙ ይሆናል::» ከዚያም ፈጠን አድርጎ፣ «ምግብ ወደሚታደልበት የሚሄዱት ሞኞች ናቸው:: ወጣትነትና ጥንካሬ የሚለማቸው ማናቸውም ቢሆኑ ከዚህ በኋላ ወደዚያ አይሄዱም:: ልጆቹን ሊልካቸው ይገባል:: እነርሱ ሊወስዱዋቸው አይገባም፣»

አለ::

በትንሿ መንደር ውስጥ ብጥብጥ ነበረ:: ሰዎች፣ በአብዛኛው ሽማግሌዎች፣ ሴቶችና ልጆች፣ ከየቤቶቹ እየመጡ ነበር:: የደካከሙ ብዙዎች ነበሩ፣ ደግሞም ልጆቹ ጸጥ ያሉና ከቁጥር የሚገቡ አልነበሩም:: አንዳንዶቹ በጡጉራቸው ላይ እራፊ ጨርቅ የተደረገላቸው ነበሩ፤ ደግሞም ብዙዎቹ ራሳቸውን ይዘው ነበር፣ ምክንያቱም ዓይኖቻቸው የቀሉባቸውና ብርሃንን ለማየት የሚቸገሩ ነበሩ:: ነገር ግን ሁሉም መጥተዋል፣ ክብ ከሆኑ የድንጋይ ቤቶች እየወጡ፣ የተሰነጠቀውን ደወል የሚደውለው ካህን ወዳለበት ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ለመሰብሰብ መጡ::

ቀጭንና መቋሚያቸውን የተመረኰዙት ሽማግሌ የሆኑት ካህን ነበሩ በመጀመሪያ ጉዳዩን የሚያቀርቡላቸው:: ቀድሞውኑ የሚያውቁትን ነገር፣ ይህም ዝናብን እየጠበቁ በረሃብ መሞት እንደ ሌለባቸው፣ ነገሯቸው፤ መንግሥታዊው ትእዛዝ የተላለፈበት ሕጋዊ ደብዳቤ መጥቶአል፤ ስለዚህ ያላቸውን ንብረት ሁሉ ሰብስበውና አሽገው ተሸክመው ሁላቸውም በአንድነት መሄድ ይኖርባቸዋል:: ወደ ምሥራቅ በመታጠፍ ቅርብ ወደ ሆኑትና ምግብ ወደሚገኝባቸው በመንግሥት ወደ ተያዙ ከተሞች ማምራት ይችላሉ፣ ወይም የምግብ አቅርቦት እርግጠኛ ወዳልሆነበት ሩቅ ወደ ሆነው ምዕራብ ጉዞ መጀመር ይችላሉ:: መወሰን ይኖርባቸዋል::

በምርጫቸው ላይ ምንም ማመንታት አልነበረም:: ምዕራባዊው መንገድ ረጅምና አደገኛ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ወደ ምሥራቅ ከሄዱ፣ ሰዎች ይጠፋሉ እንዲሁም ወላጆች በከባድ መኪናዎች ላይ ይጫናሉ፣ ደግሞም ልጆች ወደ ኋላ ይተዋሉ:: ወደ ምዕራብ መሄድ ይኖርባቸዋል:: ሴቶችና ሽማግሌዎች ትናንሾቹን ልጆች ይሸከማሉ እንዲሁም ትላልቆች ወንዶች ሸክሞችን ይሸከማሉ፣ ደግሞም ፀሐይ ከመጥለቅዋ በፊት ጉዞውን ይጀምሩታል:: ከዚያም ገብሬ መሪነቱን ተረክበና በምሽት መጓዝ ተመራጭ እንደ ሆነ አብራራ:: ደጋማ በሆነ ስፍራ የሚኖሩ፣ የቆላን ሙቀት ያልለመዱ ሰዎች ነበሩ፤ ደግሞም በየትኛውም መልኩ መንገዶቹ በቀን አመቺ



አልነበሩም፣ ምክንያቱም የጠላት ወገን ድንገተኛ አደጋ ለመጣል በተርታ የሚሄዱ ተጓዦችን ላይ ለመተኰስ አውሮፕላኖችን ይልካል:: ብዙዎች - ወንዶች፣ ሴቶች እና ሕፃናት-ሞተዋል ብሉ ነገራቸው:: ነገር ግን አርሱ እነርሱን ሲመራቸው እንደ መጣ ነገራቸው:: በተራራዎቹ ላይ ያለውን መንገድ ያውቀዋል፣ ደግሞም ወደ መጀመሪያው መጠለያ ካምፕ ለመድረስ እጅግ ሩቅ አልነበ ረም::

ሁልጊዜ መኖር ያለባቸው ልጆች በመሆናቸው፣ ጥቂቶች ቀድሞውኑ በረሃብና በትክክለኛው ራስን መካድ ደክመው ወደ ነበሩ ያረጁ ወላጆቻቸው እና አያቶቻቸው እየተመለሱ ሳለ የሞት ዝምታ ሰፍኖ ነበር:: አንዳንዶች በድካም ይንቀጠቀጣሉ፣ አንዳንዶች በመቋሚያዎች ላይ ደገፍ ብለዋል:: ነገር ግን በመንደሩ ውስጥ አሁንም ትንሽ እህል አለ፤ ደግሞም በመጋዘኑ ውስጥ የተቀመጠ ዘር አለ፤ እንዲሁም በእርግጠኝነት ዝናቡ ይመጣል:: ረጅም መንገድ መሄድ የማይችሉት ሰዎች አሁንም ውኃ ለመቅዳት መሄድ ይችላሉ:: ምሕረት ወደ ሴት አያትዋ ደገፍ አለች::

«ተክሉ እና እኔ ከእናንተ ጋር እንሆናለን፣» ስትል አንሾካሾከች:: «እናንተን ልንተዋችሁ ወይም ብቻችንን ልንሄድ አንችልም:: ውኃ እንቀዳላችኋለን::»

«ወንድ አያትሽ እና እኔ እየመጣን ነን፣» ሲሉ መለሱ አሮጊትዋ ሴትዮ፣ በታላቅ የመንፈስ ጥንካሬ:: «እግዚአብሔር ብርታቱን ይሰጠናል:: በአንድ ላይ እንሆናለን::»

ጊዜው አሳዛኝ የሆነ፣ በጣም አሳዛኝ የፀሐይ ጥልቀት ነበር:: እያንዳንዱ ሰው በቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ብርድ ልብስ፣ ምንጣፍ፣ ማብሰያ ድስት እና የውኃ ማሰሮ ተሸክሞአል፣ ደግሞም ምግቡ ቅዱስ ምሥጢር እስኪመስል ጸጥ ብለው በአንድ ላይ በሉና ጠጡ:: እያንዳንዳቸው ለጉዞ የሚሆን ቋጥረው የያዙት ትንሽ እህል አላቸው፣ ደግሞም ወደ ምዕራብ እየተጓዙ ሳለ፣ የሚበሉ ሥራ ሥሮችንና ሣር ያገኙ ይሆናል:: የተሰባሰበ ምግብ ወይም እሳት ሁሉ ባለማጉረምረም እና በአሳብ ባለመለየት ለቆሙት ጥቂት

አዛውንቶች ተተወ፣ ምክንያቱም ከዚህ ቀደም በረሃብ ውስጥ ኖረዋልና ያውቃሉ። ልጆቻቸው እያለቀሱ አቀፏዋቸው፤ ካህኑ ባረኳቸው፤ ደግሞም ታጋይ የሆነው ተጓዥ ሄደ። ምሕረት ዘወር ብላ ከዓቀበቱ በታች ስትመለከት፣ ለብቻቸው ቆመው እጃቸውን እያውለበለቡ ሲሰናበቱ፣ የፀሐይዋ የመጨረሻዋ ጨረሮች በእነርሱ ላይ ነበሩ።

በእርግጥም በዚያ ምሽት በዓቀበቶቹ ላይ የተከተሉት የእግር መንገድ በጣም ለሸመገሉት ሰዎች ወይም በጣም ትናንሽ ለሆኑት የሚሆን አልነበረም። ዓይኖቻቸውን ጭልጭል በምትለው በገብሬ ፋኖስ ላይ አደረጉ፣ ደግሞም አዲስዋ ጨረቃ ፈዘዝ ያለ ብርሃን ሰጠች፣ ነገር ግን ብዙዎች ካለባቸው የዓይን ሕመም የተነሣ ተሠቃዩ፣ ደግሞም በዐለቶች ተሰናከሉ ወይም አዳላጭ በሆነው ጭቃ ላይ ተንሸራተቱ።

ከዐለቶች ሥር ተጠልለው፣ ገንዳዎቹ ከደፈረሱበትና ጭቃማ ከሆኑበት፣ ከሞላ ጐደል እየደረቁ ካሉ ወንዞች፣ ውኃን እየቀዱ ቀኑን በዕረፍት አሳለፉት። በፍጥነት የሚያልቀውን ማሽላ ለማብሰል ወንዶች ልጆች ማገዶ ሰበሰቡ። ከሌሎች መንደሮች ሌሎች ተጓዦች ከእነርሱ ጋር ተቀላቀሉ፤ ነገር ግን ማንም ብዙ የተነጋገረ ወይም ዜናዎችን የተለዋወጠ አልነበረም፣ ደግሞም ልጆች መጫወቱን ወይም መሯሯጡን ፈጥነው ይተዋሉ። አንዳንድ ጊዜ ሁለት ሰዎች መነጋገር ይጀምራሉ፣ ነገር ግን በዓረፍተ ነገር ልውውጡ መሀል እንቅልፍ የሚወስዳቸው ይመስላል። ይሁንና፣ ምሽቱ በሚመጣበት ጊዜ፣ በቆራጥነት ተነሥተው በእግር መንገዱ ላይ ይሄዳሉ።

ተክሌን በምትመለከትበት ጊዜ ሁሉ የምሕረት ልብ በአሳብ ይሰጥማል። ከበፊቱ በተሻለ የወፈረ ይመስላል፣ ነገር ግን ውፍረቱ ጤናማ ውፍረት አልነበረም። ሆዱ እያበጠ መታየት ጀምሮአል፣ ነገር ግን ዓይኖቹ በትንሿ ፊቱ ወደ ውስጥ ሰጥመዋል። በአብዛኛው ገብሬ ይሸከመዋል፤ ነገር ግን ለዕረፍት ጕዞ በሚያቆሙበት ጊዜ፣ በሴት አያቱ ጭን ላይ ሲያደርገው ምግብ እንዲሰጠው ይነጫነጫል። ከዚያም ሴት አያታቸው ትንሽ ጭራሮ ይወስዱና



ትንሽ እሳት ያቀጣጥላሉ። በማሰሮው ውስጥ ትንሽ ጠብታ ውኃ ያደርጉና በተክሌ ፊት ለፊት በድንጋዮች ወይም ዐለቶች ላይ ያስቀምጡታል። «ምግቡ እየበሰለ ሳለ የማብስያውን ማሰሮ መዝሙር እንዘምራለን፣» ይሉታል፤ ከዚያም ይዘምራሉ ደግሞም ዛሩ አረንጓዴ ስለ ነበረበት፣ ደግሞም በሬዎች ያርሱ ስለ ነበረበት፤ የቆሎና የማሽላ ሰብል በሚሰበሰቡበት ጊዜ ደግሞም የንቦች መንጋ ስለሚመጣበት እና ወፎች ስለሚዘምሩበት፤ ጠላ ጠምቀው ስለሚጠጡበት፣ የደስታ ጊዜ ስለሚያሳልፉበት እና ስለሚጨፍሩበት ጊዜ እያወራችለት ሳለ . . . በአጭር ጊዜ ውስጥ የተክሌ ዓይኖች ይጨፈናሉ፣ ደግሞም ጥልቀት ያለው እንቅልፍ ይወስደዋል፣ የድካም እንቅልፍ ይወስደዋል፤ ደግሞም በማብስያው ማሰሮ ውስጥ ምግብ እንዳልነበረበት ከቶ አያውቅም።

ይሁንና፣ የመጀመሪያዎቹ ተጓዦች የረሃብ ሰለባዎቹ አልነበሩም፣ ምክንያቱም በትናንሽ ከተሞች ዳር በሚሄዱበት ጊዜ በሕይወት እንዲኖሩ ምግብ ይሰጣቸዋል፣ ነገር ግን እነርሱን ለማርካት ከቶ በቂ አይደለም። ሥሉስ ጐበዝ የሆነ፣ ከእናቱ ተለይቶ በኃይል መጓዝ የሚችል፣ ከማጕረምረም የተለየ ትንሽ ወንድ ልጅ ነበር። የእናቱ ባል ከመንግሥት ጓዶች ጋር በተፈጠረ ቀላል ግጭት ተገድሎ ነበር፤ ደግሞም ሕፃን ልጅዋ ሞቶአል። የቀራት ሥሉስ ብቻ ነበር፤ ደግሞም ለእርሱ ስትል በሕይወት መኖርን መረጠች።

ጊዜው እኩለ ሌሊት ነበር፤ ደግሞም የደረቀውን ቍጥቋጦ ፈጠን ብለው እያለፉት፣ አንዳንድ ጊዜ የደከሙ ልጆችን በሹክሹክታ ቃላት እያጽናኑ ከተራራው ግርጌ ባለ ኮረብታማ ስፍራ ላይ ይጓዙ ነበር። ወዲያውም ቀጭን የሆነ ድምፅ ጩኸት ነበር፣ ደግሞም የተጓዦቹ ሰልፍ ቀጥ አለ፤ ከዚያም በቍጥቋጦው ውስጥ ዘራፊው እንደ እባብ እንኰሻኰሸ። ጊዜው የደመና ምሽትና በጣም ጨለማ የሆነ ነበር፤ ደግሞም ጩኸቱን ማን አደረገው የሚለውን ለመወሰን ከገብሬ ጋርም ሆኖ ለመያዝ እንዲሁም ፋኖሱን እንዲመልስ ለመለመን ጥቂት ጊዜ ወስዶ ነበር። እርሱ በደረሰበት ጊዜ፣ የሥሉስ እግሮች አብጠው እና ለማያዊ ሆነው፣ ደግሞም

ምንም እንኳ ገብሬ በሴንጢው ቍስሉን ቀርጦ ደሙን ወደ ውጭ እንዲወጣ ቢያደርግለትም፣ እጅግ ዘግይቶ ነበር።

መቆየት አይችሉም። ዝም ብለው የሚንቀዋለሉ ከሆኑ በአደጋ ውስጥ ያሉ ብዙ ሌሎች ልጆች ነበሩ። አንድ ሰው ሥሉስን በክንዶቹ አድርጎ፣ በፊታቸው ያለ ሰማይ እስኪበራ ድረስ ከበላያቸው ባለው የተጠቀለለ የገጠር ሰማይ ላይ እርድ መስሎ እስኪታይ ድረስ ይለናከሉ ነበር። ለውየው አቆመ፤ ደግሞም እርሱና እናትየው የሥሉስን ፊት ወደ ታች ተመለከቱት። አስቀድሞ በሕመም ተጨራምቶ ነበር፤ ነገር ግን በዚህ ጊዜ በቅጽበት ሰላም ለፍኖአል፤ ደግሞም በመንጋቱ ብርሃን በርቶአል።

እንደ መገረም ብሎ ሰውዬው፣ «እርሱ አርፏል፣» አለ። ባጠገቡ የነበሩት ሽማግሌው ቄስ ደግሞ ወርቃማውን መስቀላቸውን ይዘው ቆመው ነበር።



# 6

«የሁለት ሰዓት ተጨማሪ ጊዜ ብቻ ነው የቀረን፣» አለ ገብሬ። «ከዚያም ወደ መጠለያ ካምፑ እንደርሳለን። መንዛቻችሁን ቀጥሉ።»

ጊዜው ማለዳ ነበር፤ ደግሞም ያንን ትንሽ፣ ጥልቀት የሌለው ቊልል እያስታወሱ ቀስ እያሉ ተጓዙ። የሥሉስ እናት፣ ባህላዊውን የኀዘን እንጉርጉሮ እያለማች፣ በቀስታ አለቀሰች፣ ደግሞም ሽማግሌው ካህን ከአጠገቧ ተጓዙ። ሌሎች እናቶች በጊዜው ከተራራው ግርጌ ባለ በዝቅተኛው ኮረብታማ ስፍራ ላይ ነበሩና በስጋት ልጆቻቸውን ቃኙት አደረጉ፣ ደግሞም ሙቀቱ በፍጥነት እየጨመረ ነበር። ጥቂት ውኃ ቀርቶ ነበር፣ ደግሞም ምንም እንኳ ልጆች የሆኑት ለብቻቸው በጉብዝና የሚሄዱ ቢሆኑም፣ ሰውነታቸው በድርቀት እየተጐዳ ነበር። ገብሬ በድጋሚ ተክሌን አነሣና ወደ ፊት እልፍ አሉ። ማንም አያወራም ነበር፣ ነገር ግን ራሶች ትንሽ ቀና አሉ። ቢያንስ ቢያንስ ወዴት እንደሚሄዱና መጠለያ ሩቅ እንዳልሆነ ለማየት ችለው ነበር።

ስፍራው ሙሉ በሙሉ የተራቆተ አሁን አቋርጠውት ሊሻገሩ ያለ የሚያስር አገር ነበር። በማለዳው ፀሐይ የሚያብለጨልጨ የጠንካራ እብነ በረድ ቀለም ያላቸው ዐለቶች ከበስተኋላቸው አሉ፣ ጥርት ባለው ሰማይ ላይ ቀይ ሸንተረር ያለው አፈር ከፊት አለ። ቀጭን፣ ቅጠል-አልባ ደን በእነዚህ ኮረብታዎች ላይ አድጓል፣ ቅርንጫፎቻቸው ለማገዶነት ተሰብሮ ተወስዶአል፤ ደግሞም ቀኑ እየሞቀ እየሞቀ ሄዶአል።

ከዚያም ተመለከቱት፣ ደግሞም የደከመ ደስታ ሆነ - ትንሽ ከተማ አሸዋማ በሆነ ገደል ሥር ክጥቁር ድንጋይ ወይም ከአሸዋ በተሠራ ድንጋይ ተመቻችታ ተበጃጅታለች። በዚያም ከዐለት ተፈልፍሎ የተሠራ ቤተ ክርስቲያንና አረንጓዴ መስጊድ ነበሩ። እዚህ

በእርግጠኝነት ምግብ እና ውኃ መኖር አለበት:: ነገር ግን ወደ ከተማው አልሄዱም ነበር፤ በዚህ ፈንታ ደረቅ፣ ቡናማ ቅጠል የባሕር ዛፍ ወዳለበት ጥሻ ታጠፉ:: በቍጥቋጦ የተሸፈነ የመሬት መታጠፊያ ወደ ታች ይወርዳል:: ደግሞም ገብሬ ወደ ተበሳጨው ሕዝብ ዞረ::

«ተከተሉኝ፣» አለ::

በመንገዱ ማዕዘን ታጠፈ፣ ወዲያውም ደረሉ:: ተጓዦች ጕንዳንና ተባይ በማይደርስበት መተኛት ይችሉ ዘንድ ከውጪ የማይታይ ከፍ ያለ ጣሪያዎቹ በፕላስቲክ የተሸፈኑ ሰፊ የሆነ የምድር ለምድር መጠለያ ነበር:: ሌሎች ቡድኖች ቀድሞውኑ በዚያ ዓርፈዋል፤ ደግሞም ንብረቶቻቸው በዙሪያቸው ተበታትነዋል:: ደግሞም ምግብ እየበሉና ውኃ እየጠጡ ነበሩ:: የታመሙ፣ የደከሙ ልጆች በጥንቃቄ እና በደግነት ይያዙ ነበር:: እግሮቻቸው ለቈሰሉባቸው ረሃብተኛ ተጓዦች፣ ገነት እንደ ደረሉ ያህል ነበር:: በዛፎቹ ጥላ ሥር ቁጢጥ ብለው ተራቸውን ይጠብቁ ጀመር::

ወዲያውም ተራቸው ደረሰ:: ደክመው ነበር፣ ደግሞም ውኃ ጠጡ እና አመስግነው ለመተኛት ጋደም አሉ፣ የደከማቸው ልጆች በእናቶቻቸው ላይ ልጥፍ አሉ:: የሥሉስ እናት ብቻ ጥግ ላይ ብቻዋን ሆና ራስዋን እያወዛወዘች ታቃስታለች::

እነርሱም ተኙ ወይም ቀኑን ሙሉ ጋደም ብለው አሳለፉ፤ ደግሞም ምሽቱን ሁሉ በዚህ ሁኔታ አሳለፉ፤ በሚቀጥለው ቀን በማለዳም በድጋሚ አንድ ጊዜ ተመገቡ፤ ደግሞም የውኃ ጠርሙሶቻቸውን እንዲሞሉ እና የምግብ ቀለባቸውን እንዲሰበስቡ ተነገራቸው:: «በዚህ ጠዋት እስከ እኩለ ቀን እንጓዛለን፣» አለ ገብሬ:: «ከዚያም እናርፍና ሌሊቱን ሙሉ እንጓዛለን::»

ሴት አያቱ ተነሡና ነቅንቀው ተክሌን አስነሡት:: ከዚያም አሁንም ተኝተው ወዳሉት ወደ ወንድ አያትየው ሄዱ:: ከድንጋይ ጋር ዕንቅፋት ተመትተው እግራቸው ላይ የወጣ ትልቅ ያመረቀዘ ቍስል ነበር፣ በዝንቦች ተሸፍኖ ነበር፣ ደግሞም በጣም በፍጥነት



ይተነፍስ ነበር:: ዓይኖቻቸው ብሩህ ነበሩ፣ ደግሞም ብሩህ መሆናቸውን ለረጅም ጊዜ አልተመለከቷቸውም ነበር:: ለብዙ ሳምንታት በረሃብ ደንዝዘው ነበር::

«ትኩሳት አለብህ፣» አሏቸው:: «መራመድ አትችልም:: እንቆያለን:: በኋላም መሄድ ትችላለህ::»

ራሳቸውን በፍጥነት አወዛወዙ:: «ገብሬ ከመንደርተኛው ጋር መጓዝ አለበት፣» ሲሉ አንሾካሾኩ፣ «ደግሞም አንቺ ከእርሱ ጋር መሄድ ይኖርብሻል. . . ልጆቹ . . . ልጆቹን መውሰድ ይኖርብሻል:: እኔ እዚህ እቆያለሁ፤ ከዚህ በኋላ አልጓዝም::»

ምን እየተናገሩ እንደ ነበሩ አውቀዋል፤ የእርሳቸው ተግባር ምን ላይ እንደሚያርፍም አውቀዋል:: ይሁንና፣ ብዙ ነገር ያጡ ነበሩና ጕዳዩ ከባድ ነበር:: ትልቋ ሴት ልጃቸው ወደ ደቡብ ተወስዳለች፤ ደግሞም ትንሿ ሴት ልጃቸው ከተራራዎቹ ባሻገር ሩቅ ስፍራ ላይ የሚኖር ባል አግብታ ሄዳለች፤ እርሳቸው እስከሚያውቁት ድረስ፣ ከዚያ መንደርተኛ አብዛኛው ክፍል ረሃቡ ገና በጀመረባቸው ወራት ነበር የጠፋችው:: አሁን ተራው እርሳቸው የ12 ዓመት ልጅ ሳሉ ያገቧቸው እና ለአንዲት ምሽት እንኳ ያልተለዩዋቸው ባላቸው ነበሩ:: አንድ በአንድ ከትግሉ እና ከረሃቡ እንዲሁም ከሽካራዎቹ መንገዶች ተገላገሉ፤ ደግሞም ሞት ከሞላ ጐደል በጣም የሚታወቅ ጓደኛ መስሎ ነበር:: ይሁንና፣ መለያየቱ አሁንም ከባድ ነበር:: እርሻዎቹ አረንጓዴ በነበሩበት እና መሬቱ ለስላሳ በነበረበት ጊዜ ወድደዋቸዋል፣ ነገር ግን ባዶ በሆኑት በድርቅ ዓመታት እጅግ የበለጠ ውድደዋቸዋል ምክንያቱም ከፍቅር፣ እንዲሁም በጨለማ ብሩህ ሆኖ ከሚበራው ነበልባል በስተቀር የቀረ ምንም ነገር አልነበረምና::

ገብሬ አጠገባቸው ቆመ፤ ደግሞም በዓይኖቹ ውስጥ እንባዎች ነበሩ:: «እማማ፣ መሄድ አለብን፣» አለ:: «ምግባችንን ለጥተውናል፤ ወደሚቀጥለው ካምፕ መጓዝ አሁን ካልጀመርን ምግቡ የሚቆይ አይሆንም:: እዚህ ያሉ ሰዎች ደጎች ናቸው፣ ደግሞም ለአባባ እንክብካቤ ያደርጉለታል:: አንቺ ልትመጪ ይገባል፤ ምሕ

ረት ትፈልግሻለች::»

በወንድ አያትየው ላይ ደገፍ አሉ፤ ደግሞም የፍቅር የሆነ ትንሽ የልቅሶ ጨኸትና ኀዘን አሰሙ፣ ምክንያቱም ይህ መለየት ገሚስ የሆነ ራሳቸውን እንደ መቅደድ ነበረ:: ዓይናቸውን ለመግለጥ እጅግ ደክሞአቸው ነበር፤ ነገር ግን እንደ ምንም ሁኔታውን ተቈጣጥረው «ልጆቹ፣» ሲሉ አንሾካሾኩ:: «ከልጆቹ ጋር ሂጂ፣» አሉና ወደ ነበሩበት አቅጣጫ ፊታቸውን መለሱ፣ ዓይኖቻቸውን ጨፈኑ እና ትግሉን እቆሙ:: እሁን ሊኖሩለት የሚገባ ምንም የቀረ ነገር ስለሌለ ሁሉም ነገር በቅርቡ እንደሚያከትም አውቀዋል::

ወጣት የሆነ ደግ ሠራተኛ መንገዳቸውን መራቸው:: «ከእርሳቸው ጋር እንቆያለን፣» አላቸው:: «ጊዜው ሩቅ አይሆንም፣ ደግሞም በካምፑ ውስጥ ካህን አሉ::» አሮጊትዋን ሴት ይህ አጽናናቸው፣ ምንም እንኳ በቤተ ክርስቲያን ለእርሳቸው የሚነበበው ቅዱስ የሆነውን መጽሐፍ ቋንቋ ሊረዱት ከቶ ባይችሉም፣ ይህ የሥቃይና የረሃብ ዓለም የመጨረሻው እንዳልሆነ ካህኑ ነግረዋቸዋል:: በሆነ ስፍራ፣ አንድ ቀን፣ እርሻዎቹ አረንጓዴ በሆኑበት፣ ደግሞም ውኖች ምድርን በሚያርሱበት አንድ ቀን ባላቸውን ያዩዋቸው ይሆናል፤ ምናልባትም በጣም በቅርቡ ይሆናል፣ ምክንያቱም አብዛኛው ሕይወታቸውና ጥንካሬአቸው ከእርሳቸው ጋር እንደ ሞተ ይሰማቸዋልና መኖር አይፈልጉም:: ነገር ግን ለልጆቹ ሲባል በዕድሜ መቀጠል ይኖርባቸዋል:: የማርያምንና የሚያውቋቸውን ቅዱሳን ሁሉ ስም በመጥራት አጕተመተሙና ጕዞአቸውን ቀጠሉ::

ለጥቂት ሰዓታት በእውነተኛው በገዛ ራሳቸው ሰዎች ለምግብ ማመላለሻነት በተገነባ መንገድ ለመጓዝ የድፍረት እርምጃን ተራመዱ፣ ነገር ግን በቀኑ ሙቀት ምክንያት ወደ ትንሽ ሸለቆ ሄዱ እና በሚወዛወዘው የባሕር ዛፍ ጥላ ሥር ዐረፉ:: በዚህ ስፍራ በምቾት መሸሸግ ይችላሉ፤ የሚገማው ሽታ የሚጫጫን ስሜት እንዲሰማቸው አደረገ፣ ደግሞም ብዙዎቹ አንቀላፉ:: በሚነቁበት ጊዜ፣ ጥላዎቹ እየረዘሙ ደግሞም ዓለታማ የሆነው የተቃጠለው መሬት ገላጣ ቀለሞች፣ በመጨረሻዎቹ የፀሐይ ጨረሮች የቀይ እና



የግራጫማ እንዲሁም የጥቁር ቀለማትን ማንጸባረቅ ጀመሩ:: ትላልቆቹ ልጆች ዘሮችንና ሥራ ሥሮችን ለመፈለግ ሸለቆውን በሚፈትሹበት ጊዜ፣ የቀሩቱ ትንሽ እሳት አንድደው ዳቦአቸውን ጋገሩ:: ነገር ግን ትልልቆቹ ልጆች ርቀው አልሄዱም ወይም ብዙም አላገኙም፣ ምክንያቱም ደክመው ነበርና፣ ማረፍን ብቻ የሚፈልጉ ልጆች ነበሩ::

በድጋሚ ለመሄድ በተዘጋጁ ጊዜ እየጨለመ ነበር፤ ደግሞም ምንም እንኳ መሬቱ ደረቅ እና በረሃማ ቢሆንም፣ እሁን እጅግ የከፋውን ረሃብ በስተኋላቸው ጥለውታል፣ ደግሞም ካምፖቹም ተቀራራቢ ነበሩ:: ቀኖቹ አድካሚ በሆነ የቀን ዕረፍት እና ረጅሙን ጕዞ በቀዝቃዛው ምሽት አካሄድ ስልት እያለፉ ሄዱ:: ነገር ግን አንዳንዶቹ ልጆች ጭራሮ በሚመስል እግሮቻቸው ቀስ ቀስ እያሉ እጅግ ብዙ ተጓዙ፣ ደግሞም ምንም እንኳ ትናንሾቹ የታዘሉ ቢሆንም፣ ሁሉንም ለማዘል የሚቻል አልነበረም:: እናት ወይም አባት፣ ቀድሞውኑ ድክ ድክ የሚል ሕፃን ልጅ፣ ብርድ ልብሶች እና ማብሰያ፣ ከዚህ በላይ ርቃ መሄድ የማትችል ታዳጊ ሴት ልጅን ከእነርሱ ጋር እንድትራመድ ሲደግፏት ማየት አሳዛኝ ነገር ነበር::

ሽማግሌዎቹና የደከሙቱ እየሞቱ ስለ ነበር፣ የተጓዦች ቁጥር እየቀነሰ ሄደ:: አንዳንዶቹ በደም ማነስ ወይም ስከርቪ በሚባል በሽታ ሞቱ፤ እንዳንዶች በዳፍንት ወይም በትራኮማ በሽታ በመያዛቸው መንገዶችን ማየት ስላልቻሉ በዓለቶች ላይ ወደ ወንዞች ውኃ መውረጃ ይወድቁ ነበር:: ትናንሽ ልጆችና ሕፃናት በተቅማጥ በሽታና በድርቀት ሞቱ፤ ደግሞም በመንገዱ ዳር የነበሩ መተላለፊያዎች የሟቾቹን ሬሳ ለመቅበር ሲባል ስለ ተቈፋፈሩ የቁልሎቹ ብዛት እያደገ ሄደ:: ነገር ግን በእያንዳንዱ ጊዜ ወደ መጠለያ ካምፖች ሲደርሱ ደግነት፣ ምግብ እና ውኃ እንዲሁም መሠረታዊ የሕክምና እርዳታ ነበሩ::

ሁሉም ወንዞች ወዳልደረቁበት የአገሩ ምዕራባዊው ክፍል ደረሱ፣ ደግሞም ምንም እንኳ ጊዜው የካቲት ቢሆንም፣ ጥቂት መጠን ያለው ዝናብ ቀድሞውኑ ዘንቦአል፤ እንዲሁም በተሰነጣጠቀው መሬት ላይ ቀጫጭን የአረንጓዴ ተክሎች ግርዶሽ ልክ

እንደ ጭጋግ ስፍራውን የሚሸፍኑት ይመስላል:: ነገር ግን የመንደሩ ነዋሪዎች ቀድሞውኑ ስፍራውን በሺህዎች የሚቈጠሩ ሆነው ሰፍረውበታል፣ ስለዚህ እዚያ ሊቆሙ አልቻሉም ነበር:: ስለዚህ ጉዞአቸውን ቀጠሉ::

ወንዞቹን መሻገር አንድ ችግር ነበር:: ውኃው በአብዛኛው ዝቅተ ኛ መጠን ያለው ነበር፤ ደግሞም ወንዶቹ ጥልቅ በሆነው ክፍል ላይ ይቆሙና ቀሪዎቹን አግድም ጠልቀው እየተንቀጠቀጡ ወደ ዋናው መታጠፊያ የሚሄዱትን ይረዳሉ:: በመንገዱ ላይ ድልድዮች የተሠሩባቸው ስፍራዎች ነበሩ፣ ነገር ግን የጠላት አውሮፕላኖች ቀዳሚ ዒላማዎች ስለሆኑ፣ እነርሱን ለመጠቀም አልደፈሩም::

ምሕረት በጉብዝና ታዘግማለች፤ ደግሞም ሴት አያትዋ ከእርስዋ አጠገብ ይንገዳገዳሉ (ይፍገመገማሉ):: ተክሌ በአብዛኛው በገብሬ ትከሻ ላይ በምቾት ይሄድ ነበር፤ ነገር ግን ሆዱ እያደገ እያደገ ሄደ፣ ደግሞም እጆቹና እግሮቹ እየሰለሉ ሄደዋል:: ወዲያውም በአንድ ማለዳ፣ ጠፍጣፋ በሆነ ዝርግ መሬት ላይ፣ ገብሬ መሄድ አቁሞ ወደ ታች ተመለከተ፣ ደግሞም መላው ተጓዥ እርሱ ወዳለበት መጡ እና ከእርሱ ጋር ተመለከቱ:: ከእግራቸው በታች ባሉት መታጠፊያዎች መካከል አንድ ሰፊ የሆነ ወንዝ ይፈስስ ነበር፣ እንዲሁም በአፋፉ ላይ ያሉ ዛፎች አረንጓዴ ነበሩ::

«እዚህ ልናርፍ፣ ውኃ ልንጠጣና ልንታጠብ ያስፈልጋል፣» አለ ገብሬ:: «ከዚያም ልንሻገረው ይገባል:: የውኃው ፍሰሰት ፈጣን ነው፤ ነገር ግን መሻገሪያ መሳይ ነገር አለ::»

ገብሬ ለመሻገር ወደ ውስጥ በገባ ጊዜ፣ ውኃው ደረቱ ላይ ደ ረሰ፣ እርሱ ረጅም ሰው ነበር:: ይሁንና፣ በሚቀጥለው ማለዳ ወደ ቀጣዩ ካምፕ ሊደርሱ ካስፈለገ ይህንን ወንዝ ሊሻገሩት ግድ ነበር:: ትልልቆች ንብረታቸውን ሰብስበው በጀርባቸው እንዲሸከሙ፣ ደግሞም ሕፃናቶቻቸውን ከራሳቸው በላይ እንዲይዙ ወንዶች አንድ በአንድ ልጆችን እየተሸከሙ አሻገሩ:: ምሕረት እና ተክሌ በገብሬ ወገብ ላይ ታዝለው ተሻግረው በርቀት አሉ፤ ደግሞም ገብሬ አሁን በወንዙ መካከል እናቱን ለማሻገር እየረዳቸው ነበር::



ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ከመንደራቸው የሆነች ጐረቤታቸው ማርያም ተንሸራተተችና በውኃው ውስጥ ገብታ ጠፋች:: እያቃሰተችና እየጮኸች በውኃው ተከደነች፣ ነገር ግን፣ ልክ ጉዞ ከመጀመራቸው ጥቂት ቀናት ቀድሞ የተወለደው ደግሞም ከራስዋ በላይ ተደርጎ የነበረው ሕፃን ልጅዋ በውኃ ተወሰደ:: ትንሹ አካሉ ብቅ ብሎ ሲታይና መልሶ ጥልቅ ሲልና ሲጠፋ ሳለ፣ ሰዎች አንድ በአንድ በጉርፉ ላይ ተረባረቡ:: የሕፃኑ አባት ያዘውና ወደ ዳር በመዋኘት ዳር በመድረሱ ታላቅ የደስታ ጩኸት ሆነ::

እጅግ ቆይቶበታልን? ሕፃኑ ሰማያዊ መስሎአል፣ ዓይኖቹ ግጥም ብለው ተዘግተዋል፤ ደግሞም አፉ ልክ እንደ ትንሽ ዓሣ በሰፊው ተከፍቶአል:: ነገር ግን ወደ ታች ገልብጠው ያዙት እና ውኃው ከሳንባው እንዲወጣ አወዛወዙት፤ እንዲሁም በአንድ ወቅት በሕክምና ሙያ ውስጥ የነበረ ሽማግሌ ሰውዬ ትንፋሽ ሰጠው:: የሕፃኑ እናት በፊትዋ ተደፍታ በንዴት እየተነጫነጨች ስትነፋረቅ ሳለ፣ መስቀሎቻቸውን በጣቶቻቸው እየነኩ የጨቀየው ሕዝብ እንቅስቃሴ -አልባ ሆኖ ዙሪያውን ቆሞአል::

ከዚያም ተአምር ተፈጠረ:: ሕፃኑ ማቃሰት እና መትፋት ጀመ ረ፣ ጥቂት የወንዝ ውኃዎችን አስታወከ፣ ደግሞም በድጋሚ አቃሰተ:: በአጠገቡ የነበረችው፣ ምሕረት ከጥቁሩ ቆዳው ሥር ሐምራዊ የሆነ ነገር ሲፈስስ ተመለከተች፤ ደግሞም ሕፃኑ ዓይኖቹን እየከፈተ ሳለ ከተሰበሰበው ሕዝብ ታላቅ ጩኸት ተሰማ:: በዚያ ትዕግሥት የሚጠይቅ ጉዞ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በጋራ ተ ደሰቱ:: «ሕፃኑ በሕይወት ኖረ! በሕይወትም ይኖራል!» የሚለውን አንዳቸው ለሌላው እየደጋገሙ ተናገሩ፣ ወዲያውም ምሕረት በወንዙ አጠገብ ያሉ ዛፎች አረንጓዴ እና ውብ እንደ ነበሩ፣ እንዲሁም በወንዙ መታጠፊያው ስፍራ ላይ ጥቂት አበቦች እንደ ነበሩ ልብ አለች:: ኩርምት ብሎ የተቀመጠው ተክሌ እንኳ ምንም እንኳ የሆነውን ነገር የማያውቀው ቢሆንም፣ ፈገግ ብሎ አጨበጨበ:: ለአንድ ደቂቃም ቢሆን ሕይወት ሞትን፣ ደስታ ደግሞ ኀዘንን እንዳሸነፉ ያህል ነበር::

ነገር ግን በደመናት መካከል ትንሽ ክፍተት ብቻ ነው የነበረው::

እየተጓዙ ሳለ፣ አገሪቱ የበለጠ የሕዝብ ብዛት እየኖራት ደግሞም ብዙ የጦርነት ጠባሳዎችን እያሳየች ነበር:: አንዳንድ ጊዜ እያንዳንዱ ቤት እየጠፋ ባለበት መንደር ደግሞም ትምህርት ቤቶች፣ ክሊኒኮች፣ እና የወላጅ አልባ ልጆች ማሳደጊያዎች እንኳ ከላይ በማይታይ መልኩ ሰው ሠራሽ በሆኑ ዋሻዎች ውስጥ አገልግሎት በሚሰጡበት በኩል አልፈው መጓዝ የበለጠ አደገኛ እየሆነ ጭምር ሄደ:: በዚህ ምድረ በዳ፣ አባጣ ጉባጣ በሆነ አገር፣ በማያባራ መልኩ የሚያዘግሙትን ቡትቶ የለበሱ ሰዎች ለመደበቅ የማይቻል ነበር::

አሁን የበለጠ በምሽት ይጓዙ ነበር፣ ደግሞም እርምጃው የበለጠ እየቀነሰ እየቀነሰ ሄደ:: ምሽቱ በቆላማ መሬቶች እየሞቀ ይሄድ ነበር፣ ደግሞም በከፍተኛ ቦታዎች ላይ ላደጉት ልጆች ያስቸግራቸው ነበር:: ሴት አያታቸው መናገር አቆሙ፣ ደግሞም በደከሙ መጠን ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ ይላል::

ፀሐይዋ ከበስተኋላቸው ወጥታለች፣ ደግሞም ደፋ ቀና እያሉ የሚሄዱት ተጓዦች ካምፑ ይታይ እንደ ሆነ ለመመልከት ዓይኖቻቸውን አደከሙ፣ ነገር ግን ብርሃኑ እጅግ ደማቅ ከመሆኑ የተነሣ አስፋልቱን ተመለከቱ:: ዕረፍት ሩቅ አልነበረም፤ ደግሞም ገብሬ መንገዱን የሙጥኝ ብሎ ለመያዝ ወስኖአል::

በመጀመሪያ ስምተውት እርስ በርሳቸው እየታያዩ በመንገዳቸው ላይ የሞተ ያህል የቆሙት አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ነበሩ:: ከዚያም ያ ራሱን የሳተ ጉርምርምታ ወደ ቍጡ ጩኸት ከፍ አለ፤ ደግሞም ወላጆች ልጆቻቸውን ይዘው መጠለያ ለማግኘት ሮጡ:: ነገር ግን ምንም መጠለያ አልነበረም፤ ስለዚህም የትናንሾቹን ልጆች ለውነት በራሳቸው ለውነት ራሳቸውን አፍነው በመንገዱ አጠገብ በነበሩት ከሸሽላዎች እና ዐለቶች ውስጥ ወሸቁ:: ደግሞም ትልቁ አውሮፕላን ከሞላ ጐደል ወደ መሬት ሽው ብሎ በመውረድ በመተኰሻ መሣሪያው መንገዱ ላይ ጥቃት አደረሰ፣ ከዚያም ለማያዊ ወደ ሆነው፣ ወደሚያንጸባርቀው እና በፀሐይ ውስጥ ብርማ ቀለም ወዳለው ሰማይ ቀጥ ብሎ ወጣ::



ለረጅም ጊዜ ማንም አልተንቀሳቀሰም:: ጭር ያለ ጸጥታ ነበረ:: ደግሞም ምሕረት የሴት አያትዋ በእርሳቸው ላይ ዘልለው የወጡት እና እርሳቸውን ወደ ምድር የገፉቱበት ስፍራ ላይ ተኝታ ምን እንደ ተከስተ ለማወቅ ዓይኖችዋን ለመክፈት አልፈለገችም::

ከዚያም ልቅሶው እና የቍስለኞች ማቃሰት ተጀመረ፤ ደግሞም ያልተጐዱት ሰዎች ምን ማድረግ እንደሚችሉ ለማየት በዝግታ ወጡ:: ተክሌን እጉያው አድርጎት የነበረው ገብሬ አልተጐዳም ነበር፣ ደግሞም መሪነቱን ያዘ:: ሁለት ጥንዶች ርዳታ ለማግኘት ወደ ካምፑ በፍጥነት እየሄዱ ሳሉ፣ እርሱና ሌሎች ሁለት ሰዎች ቍስለኞችን ተሸክመው ወደ ጠፍጣፋ ስፍራ ወሰዱአቸው:: የሞቱት ጥልቀት በሌለው ጉድጓድ ውስጥ ተጋደሙ ደግሞም በድንጋይና በኮሾሽላ ተከደኑ:: ስለ እነርሱ አዘኑ እና አለቀሱ:: ደግሞም ካህኑ የማያንጸባርቀውን መስቀሉን በአየሩ ላይ ከፍ አድርጎ ይዞ ጸሎት አቀረበ:: ነገር ግን ምሕረት ተክሌን ወደ ፊት እና ወደ ኋላ እያወዛወዘችው ምንም ነገር ሳታይ ስለ ምግብ፣ ውኃ እና ሙቀት ሳታስብ ቁጭ አለች:: ምክንያቱም ከሴት አያትዋ ሥር ለመውጣት ታግላ ነበር:: ደግሞም በአያትዋ የበስተኋላ ራስ ላይ ጥይቱ ያስከተለውን ቍስል ተመልክታለች፤ አሁን ደካማውን ያረጀ ለውነት ተሸክመው በጉድጓዱ ውስጥ ሲያጋድሙት ተመለከተቻቸው::

ስለዚህ አሁን እጅግ ደንግጦ በክንዶችዋ ውስጥ ከቁጥር የማይገባ ሆኖ ካለው ከተክሌ እና ድንጋይ ፊት መስሎ ከቆመው፣ ያንንም የብዙዎች መቃብር ቁልቁል ከሚመለከተው ከአጐትዋ፣ ከገብሬ፣ በቀር የቀራት ማንም የለም::

# 7

በደቡብ በብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮች ርቀት፣ ተሰፋዬ እና ሙና ከጭራሮ እንጨት እና ከመቃ ለሴን በገነቡዋት እና አሁን ቤት ብሰው በሚጠሩዋት ደካማ መጠለያ ውስጥ ጐን ለጐን ተኝተዋል። ጊዜው አሁንም ጨለማ ነበር፣ ደግሞም በጣራው ውስጥ ባሉ ሰንጣቂዎች በኩል ብልጭ ድርግም የሚለውን የከዋክብት ብርሃን ማየት ይችሉ ነበር። ነገር ግን እየሩ ደስ የሚል ቀዝቃዛ ነበር፣ ደግሞም ልክ ጽኑ እንደ ሆኑ በላተኛ እንስሳት ጥንካሬአቸውን ለማዳከምና ከናፍሮቻቸውን ለመሰነጣጠቅ ፀሐይዋ በቡና እርሻዎች ላይ ተንሰራፍታ ወጥታለች። ከደጋማዎቹ ቦታዎች እንደ መምጣታቸው ያህል፣ የቆላማው ሙቀት ከሚቋቋሙአቸው አስከፊ ነገሮች መሃል አንዱ ነበር።

ያህ ጊዜያቸው ስለሆነ በማለዳ መንቃቱን ይወድዱታል። ተ ሰፋዬ በጠዋት ተጨቅጭቆ ወደ ቡና እርሻው ይሄዳል፣ ደግሞም ሙና እርሱ ከወጣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ትከተላለች። ምናልባትም ፀሐይዋ እስከምትጠልቅበት፣ የማያጠግብ ቀለብ የሆነውን እንጀራቸው እስከሚጋገርበት፣ ጥቂት ውኃ እስከሚጠጡበት፣ ደክሞአቸውም በመጠለያቸው ውስጥ ምንም ቃል ሳይለዋወጡ እስከሚተኙበት ጊዜ ድረስ አይገናኙም ይሆናል። ነገር ግን በቀዝቃዛማው ማለዳ ላይ የዕለታዊው ኃይላቸው በጥቂት መጠን ይመለስላቸዋል፤ ደግሞም በጸጥታ ተኝተው ሳለ እርስ በርሳቸው ይመለጋገናሉ፤ ምክንያቱም ብዙዎች ሞተዋልና። ደግሞም የሚናገሩት ስለ ልጆቻቸው እና ማምለጥ ስለሚቻልበት ሁኔታ ነበር።

እያንዳንዱ ሰው ስለ ማምለጥ ያወራል፣ ደግሞ ጥቂቶች ጠፍተ ዋል። ከካምፖቹ ውጭ ወዳሉ ሽንት ቤቶች ሄደው ነበር፣ ደግሞም



ከዚያ ወዲያ ከቶ አልታዩም። ያሁን እንጂ፣ ጠባቂዎቹ ይህ ከዚህ በኋላ እንደማይከሰት አረጋግጠዋል፤ ደግሞም አሁን ማንም ከሥራ ሰዓት ውጭ ካምፖችን ትቶ መውጣት አይፈቀድለትም፣ ስለዚህ ጉረኖው ይገማና ሽታውም እየከረረ ይሄድ ነበር። ማንም ሊያሻሽለው የሠራ የለም። መሬቱ ለመቆፈር አስቸጋሪ ነበር፣ መሣሪያውም ቢሆን የላቸውም። ዝንቦች በብዛት ተራብተዋል፤ ደግሞም ሕመም ተንሰራፍቶአል። የሞቱ አካላት እንኳ ዘመዶቻ ቸው ጥልቀት የሌለው መቃብር ሊቆፍሩላቸው ኃይላቸውን እያሰባሰቡ ሳለ በፕላስቲክ ተጠቅልለው፣ በሚያቃጥለው ሙቀት እየጠወለጉ ሳይቀበሩ ተጋድመዋል። አንዳንዶቹ በቅርቡ የኮሌራ በሽታ ይከሰታል፣ ከዚያም ብዙ፣ እጅግ ብዙ፣ ብዙ የሆኑ የሚሞቱ አካሎች ይኖራሉ ሲሉ ያንሾካሹካሉ።

ጨለም ያለው፣ የማለዳው ጊዜ ግን የገዛ ራሳቸው ሰዓት ነበር። ደግሞም ሙና በባልዋ እቅፍ ጥላ ውስጥ ጋደም ብላለች። እንዲሁም እርሱ እስካለ ድረስ እርስዋ እንደምትሄድ አውቃለች፤ ደግሞም አንድ ቀን በእርሱ ከሞላ ጐደል ማመን ያቆመችበት እምላክ (ስለ እርሱ ብዙ የምታውቀው ነገር የለም) ወደ ልጆቻቸው እንዲመለሱ ይረዳታል፤ በጉዳዩ አእምሮዋ ተይዞአል። ደግሞም ስለ እርሱ ማሰብ ማቆም አትችልም ነበር። በየቀኑ አዳዲስ የማምለጫ ዕቅድ ይዛ ከእንቅልፍዋ ትነቃ ነበር፤ እነዚህም ዕቅዶች ተሞክረው የከሽፉ እና የማይቻሉ ዕቅዶች ነበሩ።

«ነገር ግን አንዳንዶች ጠፍተዋል፣» ስትል አንሾከሾከች። «ደግሞም ያለነው ከጠረፉ ርቀን እንዳይደለን አስታውስ። ይህን የአውቶቡሱ ሹፌር ነግሮናል። ፀሐይ ከየት እንደምትወጣና ወዴት እንደምትጠልቅ እናውቃለን። ከእኛ የሚጠበቀው የፀሐይን ዱካ መከተል ነው።»

«እናስ የፀሐይን ዱካ ተከትለን ስንሄድ ተኩሰው የጣሉን እንደ ሆን፣ ከዚያስ በኋላ ምን ይከተላል?» ሲል ተስፋዬ በትዕግሥት መለሰ። ተስፋው ከሞላ ጐደል ተሟጦአል፤ ነገር ግን በሚስቱ ውስጥ ያለ ያ ጽኑ የሆነ የእናትነት ደመነፍስ ያደንቀዋል፣ ወደ ልጆቿ ለመመለስ የምታደርገውን ትግል ከቶ እንድትተው

እንደማያደርጋት ይገነዘባል::

«በምሽት ልንሞክረው እንችል ይሆናል፣» ስትል አንሾካሾከች:: «አዲሷ ጨረቃ ከመውጣትዋ ጥቂት ቀደም ብሎ በእርግጥ በጣም ጨለማ ነው፤ አሊያም አዲስዋ ጨርሳ ከመጥለቅዋ ትንሽ ቀደም ብሎ በጣም ጨለማ ነው፤ እነርሱ ይተኛሉ:: ሙታን የተኙበትን ስፍራ ተጠግተን ብንሄድ፣ ዕድል ይኖራል:: በሙታን አቅራቢያ አይቀመጡም::»

ተስፋዬ ወደ ራሱ አስጠጋት:: «ከሌሎች ሰዎች ጋር እንነጋገርበታለን፣» አላት:: «እታች በግቢው በሌላ ጫፍ ላይ ረብሻ ያስነሡ ይሆናል፤ ስለዚህም ጠባቂዎቹ የላይኛውን ጫፍ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ትተውት ወደ ታች ይንቀሳቀሳሉ:: ወይም ምናልባት፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፣ መከታተላቸውን ላላ ያደርጉታል:: አንቺ እንዳልሽው፣ ጠረፉ ሩቅ ሊሆን አይችልም:: በቁጥቋጦዎች ውስጥ የፀሐይን መንገድ መከተል እንችላለን:: ነገር ግን፣ ሙና፣ ወደ ቤታችን ለመመለስ ያለን መንገድ ረዥም ነው፣ ዓቅምም ያንሰናል::»

እውነተኛ ተስፋ ከመያዙ ይልቅ፣ እርሷን ለማጽናናት ብዙ ይናገር ነበር፣ ደግሞም እርሷ ይህን ታውቃለች፤ ነገር ግን እርሱን አመስጋኝ ነበረች:: ትንሽ ነፋስ በካምፑ ክርፋት የሚከረፋውን ጨፈውን በጥንዶቹ ራሶች ላይ በተነው፣ ደግሞም ጨለማው የደበዘዘ ነበረ:: በጸጥታ የመጨረሻዎቹ በአንድ ላይ የሚሆኑበትን የዕረፍት ደቂቃዎች እያጣጣሙ ቆዩ፣ ከዚያም ሙና በፍጥነት ተነሣች፤ ደግሞም አመዱን ከጐጆው ፊት ለፊት እራገፈች:: ምግቡንና ውኃውን በወፍራሙ አደባለቀችው፣ ደግሞም ጭራሮውን በእሳት ማንደጃው ብረት አቀጣጠለችው:: ቀላ ወዳለው ወጋገን ገብተው ተወሽቁና ቀሪውን ውኃ ጠጡት:: ከዚያም ተስፋዬ ስለ ሥራው ሪፖርት ለማድረግ ሄደ:: ደግሞም ሙና የፕላስቲክ ዕቃዋን ይዛ ውኃ ልትቀዳ ሄደች:: አሁንም ርቦአቸዋል:: በምሽት በድጋሚ ይመገባሉ፣ ነገር ግን የሚቀርብላቸው እህልና ዘይት እስከ ወሩ መጨረሻ መቆየት ይኖርበታል::

ሙና ቀስ እያለች በእግርዋ ተጓዘች፣ ይህም በከፊል እርሷ



የደከማትና መሬቱ ሸካራ በመሆኑ ሲሆን፣ በከፊል ደግሞ ከገዛ ራስዋ አሳቦች በስተቀር ስለ ማንኛውም ነገር በንቃት የምታስብ ባለመሆኗ ነበር:: ሌሎች ሴቶች በውኃ አቅርቦት ላይ እየተነጋገሩ ነበር፤ ነገር ግን የሙና እግሮች ሳይታወቃት እንዲሁ ተሸክመዋታል፤ እርሷ ፍጹም ልብ አላለቻቸውም:: ከሩቅ ስፍራ፣ ከሰሜን ተራሮች፣ ከሞላ ጐደል አካላዊ በሆነ ጥንካሬ እርሷን ለመቅረብ እየፈለጉ የት መሄድ እንዳለባቸው ሳያውቁ እና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሳያውቁ፣ ተክሌም ድክም ብሎና ታምሞ፣ እርሷን እየፈለጋት ልጆችዋ ወደ እርስዋ ይጮኻሉ:: ዕቃዋን በውኃ ሞልታ ተመለሰች፣ ቁርጠኝነትዋ በእያንዳንዱ ደረጃ እያደገ ነበር:: የባልዋን ጥበብ ትገነዘብዋለች፤ ነገር ግን፣ የትኞቹም ችግሮች ይኑሩ፣ መሄድ እንደሚኖርባቸው እንዲመለከት ልታደርገው ትሻለች:: እርሱ አፍቃሪ ባልና መልካም አባት ነበር፣ ነገር ግን እርሷ እንደምትሰማው ሁሉ የልጆቹን ድምፅ መስማት አይችልም::

እዚያ በደረሱ ጊዜ በሠሩዋት መጠለያ ውስጥ አንዳንድ ነገሮችን እያስታወሰች ተቀመጠች፤ እነርሱ የሚወስዱበት ስለ ሆነች በእርስዋ ፍራፍሬ፣ ሥጋ እና በቂ ውኃ ይኖርበታል ስለ ተባለች የጥጋብ አገር፣ ብዙ ታሪኮችን ሰምተው ነበር:: ነገር ግን እነዚያ የሚገሙ አውቶብሶች የተራቡ፣ የተጠሙ የምድሪቱን ነዋሪዎች በዚያ መኖርን ወደ ማስቆሙና ወደ ማፈናቀሉ ባመጡዋቸው ጊዜ፣ አዲስ መጪዎቹ ለእነርሱ ቤት ለመሥራት ሊባል እንዲወጡ የተደረጉበትን ምድረ በዳ (የሚኖርበት ሰው የሌለን ምድር) ተጋፈጡ:: በአንድ ወቅት ይታረሱ የነበሩ አሁን ግን የደረቁ ትናንሽ መሬቶች ነበሩ:: ለሁሉም የሚሆን በቂ ስፍራ ስላልነበረ፣ ለወንዶቹ መጥረቢያ ተሰጥቶአቸው የራሳቸውን መጠለያ እንዲሠሩ ተነግሯቸዋል:: የእህልና የዘይት ቀለብ ይሰጣቸዋል፤ ደግሞም ሊያገኙት ከሚችሉት ነገር ማብሳያዎችን እንዲያበጁ ተነግሮአቸዋል:: ሚሊሺያዎቹ በጠመንጃ በጠዋት ወደ ቡና እርሻው በኅብረት ሲሄዱ እየሸኙዋቸው፣ በምሽት በቍጥቋጦዎቹ መልሰው በምሽት በጠመንጃ አፈ ሙዝ ወደሚጠበቁበት ስፍራ ሊያመጡዋቸው፣ በእጅ የሚሞላ ማገዶ ሲለበስቡ ሊመለከቱዋቸው፣ አካባቢውን በሞላ ይቃኛሉ (ይቈጣጠራሉ)::

ስፍራው እሾሃማ ቁጥቋጦዎች እና ዝቅተኛ እድገታቸው የተገታ ዛፎች ያሉበት ነበር፤ ነገር ግን ወደ ምዕራብ እስከ ዝቅተኛዎቹ ኮረብቶች የሚደርስ በአቀበቶቹ ላይ ደኖች ያሉበት ጠፍጣፋ መሬት ተዘርግቶ ነበር። ሙና እነርሱን ደጋግማ ደጋግማ በትኩረት ተመለከተቻቸው። እድገታቸው የተገታባቸው ትናንሽ ዛፎችና እሾሆች ትንሽ መጠለያነት ይሰጣሉ፣ ነገር ግን እነርሱ በዓቀበቶቹ ኪሶች እና በደኖቹ ውስጥ ሊደበቁ ይችላሉ። ፀሐይዋ ከዚያ ወጣ ገባ አድማስ በስተያ በምትወጣበት ጊዜ ነበልባላማ የሆኑትን (የሚንቀሰቀሱትን) ቀለሞች ትመለከታቸው ነበር፤ ደግሞም በአሳብዋ በእርሱ በኩል አድርገው ተመልሰው ወደ ልጆቻቸው እንደሚባረሩ ይታሰባታል።

በጣም እየሞቀ ነበር፣ በቅርቡም ይሰበሰባሉ፣ ደግሞም ከሌሎች ሴቶች ጋር በአንድነት በመሆን ወደ ቡና ተክሉ ይሄዳሉ። የውኃ መያዣዋን አስቀመጠችውና ሕፃኑ በሚያስገርም ሁኔታ ከአሳዳጊ እናቱ ጋር አሁንም ወደሚኖርበት ወደ ትንሽዋ ያዘመመች ጐጆ ተሻገረች። ነገር ግን ልጅቷ ቀጭጫ ነበር ያደገችው፣ ደግሞም የጡትዋ ወተት መድረቅ ጀምሮ ነበር። ተስፋ በመቍረጥ ትንሿን ፍጡር ወደ ታች ተመለከተቻት፣ ከዚያም ደግሞ ሙናን ተመለከተቻት።

«ደኅና ሁኑ ለማለት ነው የመጣሁት፣» አለች ሙና።

ልጅቱ ትናንሽ ዕንባዎች እየወረዳት ማልቀስ ጀመረች፣ ምክንያቱም ሙናን እንደ እናቷ ነበር የምትወድዳት። ከዚያም ዕንባዋን አደረቀች ደግሞም ፊትዋ የቈረጠ መሰለ።

«ብዙዎች ሄደዋል፣» አለች በቀስታ። «አንዳንዶች በጥይት ተመትተዋል፣ ነገር ግን አንዳንዶች ወደ ቍጥቋጦው አምልጠዋል። ባለቤቴ ብዙዎቹን አነጋግሮአል። የዚህ ልጅም አባት መሄድ ይፈልጋል። እቤት ልጆችን ትቶአል። መሞከር ይፈልጋል። ከእርሱ ጋር መነጋገር ይኖርብሻል።»

«እንዲመጣ ንገሪው፣» ስትል ሙና አንሾካሾከች። «ዛሬ ማታ መነጋገር አለብን። ነገ የአዲሷ ጨረቃ መመለሻ ነው።»



ስለዚህ እነርሱ በዚያ ምሽት በጀመረበት እና ትናንሾቹ እሳቶች በተያያዙበት ጊዜ የልጁ አባት፣ ሁለት የተቈጡ ወጣት ወንዶች እና ወጣት ጥንዶች፣ ወደ ቤተሰብዎችዋ ለመሄድ በከፊል የቀወሰች አንዲት ሴት መጡና በድንኳኑ በር ዙሪያ ተቀመጡ። በቀስታ፣ ምንም ቃላት ሳያባክኑ፣ ተነጋገሩ። የእሾህ አጥሮች በሰሜኑ አቅጣጫ ዙሪያ ተደርገው ስለ ነበር፣ አንዱ ሜካኒክ ስለ ነበር - ብረት የሽቦ መቍረጫ አበጀ። ሙና እንደ ተናገረችው፣ ነገ አዲስ ጨረቃ ይኖራል። እርሷ ከመውጣትዋ ጥቂት ቀደም ብሎ በደቡቡ የካምፑ ጠረፍ ላይ አንዳንድ ሰዎች ሁከትን ይጀምራሉ፤ ደግሞም በዚያው ጊዜ አጥሩ ይቈረጣል፤ እንዲሁም አምላጮቹ በሙታን አጠገብ ሳይንቀሳቀሱ ይጋደማሉ። ድምፁ በሚጀምርበት ጊዜ በሆዳቸው እየተሳቡ በጨለማው ውስጥ በዝግታ ይወጣሉ፣ በተለያዩ አቅጣጫዎችም ለሜን፣ ምሥራቅ፣ እና ምዕራብ ተበትነው ይሮጣሉ። ጠባቂዎቹ ያለ ጥርጥር የደረቁን ቍጥቋጦ ጩኸት ይሰሙና ይተኩሳሉ። አንዳንዶች ይሞታሉ፣ ነገር ግን አንዳንዶች ያመልጣሉ። ሊቈሰሉና ወደ ኋላ ሊመለሱ ስላሉቱ፣ ለማሰብ አልፈለጉም።

እያንዳንዳቸው ወደ የገዛ መጠለያቸው ሄዱ። ሙና እና ተስፋዬ ጐን ለጐን ተጋድመዋል፣ እንቅልፍ ሊወስዳቸው አልቻለም፤ ነገር ግን አንዳቸው ከሌላቸው ብርታትን ይወሳሰዳሉ። ነገ ሙና በማለዳ መነሣት ይኖርባታል፤ የቀራትን ርጋፊ ዱቄት ተጠቅማ ለመንገድ የሚሆን እንጀራ መጋገር ይኖርባታል። ነገ በደንብ መጠጣት ይኖርባቸዋል፣ ደግሞም ትንሽ ውኃ ብቻ ነው መሸከም የሚኖርባቸው። ነገር ግን ዛሬ ምሽት የፍቅር ጊዜ ማሳለፍና ማውራት ይኖርባቸዋል፣ ምክንያቱም አብረው የሚያሳልፉት የመጨረሻዋ ምሽት ይህች ልትሆን ትችላለች። ዛሬ ምሽት ወደ እግዚአብሔርና ወደ ማርያም ደግሞም ወደ ቅዱሳን ሁሉ እንዲጠብቁዋቸው መጸለይ ይኖርባቸዋል፣ ነገር ግን ሙና በግማሽ ልብ ነበረች፣ ምክንያቱም እግዚአብሔርና ማርያም ደግሞም ቅዱሳን ሁሉ፣ እነዚህ ወገኖች ከልጆችዋ ነጥለው ሲወስዷት፣ ያች ልጅ በአውሮፕላን ውስጥ ሕፃኑን ስትወልድ፣ ሙታን ሳይቀበሩ በተተዉ ጊዜ የት ነበሩ? ለዚያ አንድ ጥያቄ መልስ አልነበረምና

አሳብዋን ጨዋ ወደ ሆነው ባልዋ አደረገችና በጨለማው ውስጥ በደረቱ ላይ ተጋደመች:: የምድር መብራቶች ሁሉ በሚደበዝዙበት ወይም በሚጠፉበት ጊዜ፣ የፍቅር ብርሃን እየበራና እየፈካ የሚሄድ መምሰሉ ምን ያህል እንግዳ ነገር ነበር! በዚያ ጋደም ብላ ስለ እርሱ እያሰበች ነበር:: ፍቅር ከየት ነው የሚመጣው? ምንጭ ይኖ ረው ይሆን? ረሃብም ሆነ ጥማት ወይም ኀዘን ስምን አያጠፋትም? ፍቅር በዚያ ምሽት እጅግ በጣም የቀረበ መሰለ፣ ይህም በእርሷ ውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ ጠጉርዋን እየደባበሰ እየሸፈናት በዙሪያዋ ባለው ሁሉ ላይ ነበር:: ፈገግ አለች ደግሞም የሰላም እንቅልፍ ተ ኛች::

ቀጣዩ ቀን ሙቀት ነበር:: ሠራተኞች ወደ ቤት በምሽት መጡና እንደተለመደው በሉ እና ጠጡ፣ ከዚያም ደክሞአቸው ተኙ:: ብዙም የሚደረግ ዝግጅት አልነበረም:: ጠቆር ባለው ካባቸው (መደ ረቢያቸው) ላይ የውኃ ዕቃቸውን አስቀመጡ፤ ደግሞም የተጠቀለለ እንጀራ በወገባቸው ዙሪያ አደረጉ፤ እንዲሁም ሙና የምትጋግርበትን ብረት ምጣድ ጭምር ያዘች:: ከዚያም፣ በጨለማው ሰዓት ጨረቃ ከመውጣትዋ በፊት፣ በምድር ላይ በሆዳቸው እየተሳቡ ሄዱ፣ ደግሞም ከሙታን ክምር በስተኋላ ተ ጋደሙ:: አንድ በአንድ ደረሱ:: ደግሞም ከተረፉት መካከል ማጥወልወሉን እና የእነዚያን ቀጣይ ሰዓታት ፍርሃት፣ አሊያም ሽቦውን በብረት በቀስታ ስመቁረጥ የሚደረገውን ተግባር የሚረሳው ማንም የለም።

ወቅቱ ከእኩለ ሌሊት በኋላ ነበር:: ቆረጣው አብቅቷል፣ ደግሞም ወጣቱ ሜካኒክ ሥራውን ሠርቶ መንገዱ ክፍት ሆኖ ሳለ በጸጥታ ተጋድሞአል:: ወዲያውም ከደቡብ የካምፑ ወገን የጠብና የግርግር እንዲሁም ጆሮ የሚበጥስ ጩኸት ድምፅ ተሰማ:: ጠባቂ ዎች ከቁጥቋጦው ዘልለው ወጡ፤ ጠመንጃቸውን አቀባበሉ፣ ደግሞም ፋኖሳቸውን አብርተው፣ በጠመንጃቸው አየር ላይ እየተኮ ሱ ድምፁን ወደ ሰሙበት አቅጣጫ ሮጡ:: እየጠበቁ ያሉት ጥቂት ቡድኖቹ በተፈጠረው ክፍተት በቀስታ መንገዳቸውን አቀኑ፤ በእግሮቻቸው ተነሥተው ወደ ሰሜን፣ ምሥራቅ እና ምዕራብ



በሥሮች እየተጠለፉ፣ በእሾሆች እና በትናንሽ ቅርንጫፎች እየተ ቄነጠሩ ወደ ነፃነት መሮጣቸውን ቀጠሉ:: ነገር ግን ቅኝት አድራጊ ዎች ሞኞች አልነበሩም፤ በፍጥነት በደቡብ በኩል የተደረገው ሽብር የሐሰት ምልክት እንደ ሆነ አረጋገጡ፤ ከዚያም ወደ ስፍራቸው ተ መልሰው መጡ:: በውጪ በቍጥቋጦዎቹ መካከል የሆነ ቦታ ላይ እየተበጣጠሱ ያሉ ቅርንጫፎችን እና የተረበሸ የምሽት ወፍ ድምፅ ለመስማት ቻሉ:: ወታደሮቹ ወደ ቍጥቋጦው በማነጣጠር በሁሉም አቅጣጫዎች ተኰሱ፤ ደግሞም አንድ ሰው ጮኸና ወደቀ:: ከዚያም ፋኖሳቸውን ወደ ቍጥቋጦዎቹ ላይ አደረጉ፤ ደግሞም ደግመው ደጋግመው ሲተኵሱ መላው አካባቢው በእሳት ተያያዘ::

ሙና እና ተስፋዬ የካምፑን ጠርዝ በመከተል ከእርሱ በፊት ነበልባሉን ወደሚሸከመው የምሽቱ ጭላንጭል በብርሃን መንገድ በቀጥታ ወደ ምሥራቅ ሮጠዋል:: በዚህ ጊዜ ቍጥቋጦው በጣም እየነደደ ነበር፤ ደግሞም በምዕራብ አቅጣጫ ለሄዱት ሰዎች የሚኖራቸው ዕድል በጣም የመነመነ ነበር፤ ነገር ግን ከዚያ ከሚጋርድ ጢስ አልፈው የንፋሱን አቅጣጫ ተከትለው የሚሄዱት የማምለጡን ተግባር ይወጡታል ሲል ተስፋዬ ባለማወላወል አሰበ:: ይሁንና፣ በዙሪያቸው ያለው አየር የሚያቃጥል ነበር፤ ደግሞም የነበልባሉቹ ጩኸት በጣም ቅርብ ነበር:: በሙቀት እና በሚሸከረከ ረው ጢስ ማየት እየተሳናቸው፣ ሙና ከኋላው እየተራመደች መሆንዋን በአስቸጋሪ ሁኔታ እየተገነዘበ በእንቅፋት ተመታ::

ጩኸትዋን እና መውደቅዋን በሰማ ጊዜ ብቻ መጓዙን አቆመ:: ወደ ኋላ ተመልሶ ሮጠ እና እንድትነሣ ረዳት፣ ደግሞም ወደፊት ጎተት አደረጋት:: ከዚህ በኋላ መሮጥ የማትችል ትመስላለች፣ ነገር ግን ወደ ኋላ ሲመለስ አንድ ነገር ልብ አለ:: እርሱ ከዚህ በኋላ በእሾሆችና በሥራሥሮች መካከል በኃይል እየተራመደ መሄድ ሳይኖርበት፣ ደረቅ በሆነው ድንጋያማ መሬት ላይ ነበር የሚጓዘው፣ ደግሞም ከቁጥቋጦ ነፃ የሆነ ስፍራ ላይ ደርሰዋል:: አነሣትና በጀርባው ላይ አዘላት፣ ከዚያም ወደ ፊት ለመጓዝ /ለመግፋት/ ይታገል ጀመር፣ ደግሞም ወደፊት መጓዝን በገፋው መጠን ሙቀቱ እየቀነሰ አየሩ ንጹሕ እየሆነ ሄደ:: በዚህም እሳቱና ጢሱ ከዚህ

በኋላ እንደማይመጣ አወቀ፣ ምክንያቱም በተጥታ በነፋስ አቅጣጫ ላይ እየተንዘ/እየሮጠ ነበርና:: በተጨማሪም ነበልባሎቹና ጢስ ለማራኪዎቻቸው ለሰዓታት የማይታለፍ መሰናክሎችም እንደሚሆኑባቸው አወቀ:: የሙና ክብደት ተጨምሮበት ወደ ኋላ በጣም ጎንበስ ብሎአል፣ ደግሞም ንጹሕ የምሽት አየር እስከሚያገኝ ድረስ ጉዞውን ቀጠለ:: ከዚያም እርሷን በምድር ላይ አጋደማት እና ፊትዋ ላይ ውኃ ረጫት:: ጊዜው በጣም ጨለማ ነበር:: ነገር ግን ትንፋሽዋን ማዳመጥ ይችል ነበር፣ ደግሞም በከዋክብት ብርሃን የዓይኖችዋን ነጭ ክፍል መመልከት ይችል ነበር:: ስለዚህም እርሷ ወደ ላይ ወደ እርስ እየተመለከተች እንደ ሆነ አወቀ::

«ሙና፣» ሲል አንሾካሾከ::

በትንሽ ማቃሰት ውስጥ ተናገረች:: «መሄድ አልችልም:: እግሮቹ በእሳት ተቃጥለዋል፣ ደግሞም እየደማሁ ነኝ:: አንተ ትተ ሽኝ መሄድ ይኖርብሃል. . . ወደ ልጆቹ መሄድ ይኖርብሃል::»

ነገር ግን እርሷን ትቶ መሄድ አልቻለም፤ ከልጆቹ በላይ እርሷን ይወድዳታል:: እጆቹን ከበታችዋ አደረገ ከዚያም ሙቅ የሆነ የደምዋን እጣብቂኝ ባሕርይ ተሰማው:: እግኝተው እርሱንም ጭምር ቢገድሉት ደንታ አልነበረውም፣ ምክንያቱም ያን የመጨረሻ ጉዞ ቀድሞውኑ ጀምሮታልና፤ ደግሞም ከእርሷ ጋር ቢሄድ ደስተኛ ነበር:: ሊያያት ቢችል ወይም እርሷን ለመርዳት አንድ ነገር ማድረግ ብችል ሲል ተመኘ:: ከሸሚዙ ላይ እራፊ ጨርቅ ቀደደ እና ቍስሉን ለማሰር ሞከረ፣ ነገር ግን መልካም እንዳልነበረ ያውቃል:: ጸጥ ብላለች፣ ትንፋሽዋ ፈጣን ነበር፤ ደግሞም የደም ግፊትዋ እየሮጠ ነበር::

«ከእንቺ ጋር እዚህ እቆያለሁ፣» አላት:: «አንቺ የተወደድሽ ሚስቴ ነሽ::» መደረቢያ ልብሱን ለእርስዋ ትራስ ለመሥራት ወሰደና፣ ይህን እያደረገም እያለ፣ የንፋስ መንፈስን እና ትንሽ የቊጥቋጦ ወፎች መንጫጫት በዚያ መኖራቸውን ተገነዘበ:: ለእፍታ ዓያኖቹን ጨፈናቸው፤ ከዚህ በፊት እንደዚህ ያለ እጅግ ደብዘዝ ያለ ስሜት ተሰምቶት እንደ ነበረ ለማስታወስ አልቻለም::



እንደገና በከፈታቸው ጊዜ፣ በማስዳው ጭጋግ የዛፎች ቅርጽ ደብዘዝ ያለ ነጭ እንደ ሆነ ተረዳ:: ከዚያም ወደ ሙና ፊት ለመመልከት ደፈረ፣ እርሷም እንደዚሁ በሆነ መልኩ ትመለከት ነበር፣ ዓይኖችዋ ተጨፍነዋል:: ደግሞም በዙሪያዋ ያለ መሬት በድቅድቅ ጨለማ ተዋጠ:: ይሁንና፣ ፊትዋ ሰላም የሞላበት ነበርና ከጉኑ ልትተኛ ቻለች::

ከላይ ያለው ሰማዩ መርግድ መስሎ እስኪቀየርና ብሩህ እስኪሆን ድረስ፣ ቀይ ቀለም ካለው ላባማ ደመና ጋር ብናኝ እስኪሆን ደግሞም ምሥራቁ ብሩህ ቀይ ሆኖ ከወጣ፣ ጠቆር ያለ ሰማያዊ፣ እና ወርቃማ ማለዳ ጋር እሳት እስኪለኩስ ድረስ ከእጠገብዋ ተቀምጦአል:: ከእንቅልፉ ተነሣ፣ መደረቢያውን፣ እንጀራውን፣ የውኃ መያዣ ዕቃውን እንዲሁም መጥበሻውን ከወገብዋ ላይ ወሰደ፣ ደግሞም በገዛ ራስ ወገብ ላይ አደረገው:: ከዚያም ጭራሮ እና ድንጋዮችን በላይዋ ላይ ጫነ፤ ከዚህ በኋላም ስለሚያደርገው ነገር ግራ ይጋባ ነበር:: ከእጠገብዋ ተጋድሞ እርሱም እንዲሁ ሲሞት ፈልጎ ነበር፣ ነገር ግን ይህን ሲያደርገው እንደማይችል አሰበ:: ካህን በኖረና በጸለይሁ ሲል ተመኘ፣ ነገር ግን የደከመ አእምሮው ቃላቶቹን ለማስታወስ የማይችል ይመስል ነበር::

ነገር ግን የሚያስታውሳቸው ሁለት ቃላት ነበሩ- እነርሱም ለመጨረሻ ጊዜ እርሷ የተናገረችው ነበሩ:: ወዲያውም አሁንም እንኳ ሲደረጉ የሚገቡ ነገሮች እንዳሉ ደግሞም የተሳሳተውን መንገድ እንደ ተጋፈጠው ተገነዘበ:: ወደ ኋላ ዞሮ ቀስ በቀስ ከፀሐይዋ በቀኝ ትከሻው አንጻር አድርጎ ወደ ሰሜን ምሥራቅ መጓዝ ይኖርበታል::

«ልጆቹ፣ አዎን፣ ልጆቹ፣» ሲል አጉተመተመ:: ሸክሞቹን አነሣ:: በድጋሚ ለአንድ ጊዜ ቁልሉን ተመለከተ፣ ደግሞም በፊቱ ላይ እንባ እየወረደ ወደ ጠረፉ አመራ::

# 8

«በቅርቡ እዚያ እንደርሳለን፣» አለ ገብሬ።

አሁን በጣም ቀላል ሸክም የሆነው ተክሌ፣ ራሱን ለማዞርና ለመመልከት ኃይሉን ሲያሰባስብ ሳለ ለአፍታ ዝምታ ሆነ። ነገር ግን እይታው መልካም አልነበረም፣ ደግሞም የደበዘዘ ነገርን ብቻ ነበር ለመመልከት የቻለው።

«የት?» ሲል ጠየቀ።

«ጉዞ ወደምናቆምበት ካምፕ። በዚያ ምግብና ዕረፍት አለ፣ ዛፎች በወንዙ ውኃ የሚያድጉበት ቦታ ነው።»

«ለሁልጊዜ ጉዞን እናቆማለን? ከዚህ በኋላ አንጓዝም?»

«ምናልባት፣ ለረጅም ጊዜ አንጓዝም፣ አንተ እንደ ገና ጠንካራ እስክትሆን ድረስ።»

ተክሌ በስተኋላው ያለችውን ምሕረትን ለመጥራት ወደ ኋላ ዞረ፣ «በቅርቡ እዚያ እንደርሳለን፣ ምሕረት። ደግሞም ከዚህ በኋላ ብዙ በእግራችን አንጓዝም። ከዚያም እጅግ ከብዶ የሚታየውን ራሱን መልሶ ወደ ገብሬ ትከሻ አመጣው፣ ደግሞም የጉደጉዱ ዓይኖቹን በደስታ ጨፈናቸው። ትከሻው ሾል ያለና እያንዳንዱን አጥንት ከታች ወደ ላይ በቆዳው ወጥቶ የሚወጋ ነበር፣ ነገር ግን ለረጅም ጊዜ ተክሌ ትራስ አድርጎት ነበር ደግሞም እየተጠቀመበት ነበር። ከዚህም ባሻገር፣ የሚጠብቀውን መልካም ዕድል ያውቀዋል፤ ከእርሱ ብዙም በዕድሜ የማይበልጡ ልጆች ነበሩ፣ አሁንም በቀጫጭን እንጨት መሳይ እግሮቻቸው ለብቻቸው ለመጓዝ ይታገላሉ። ነገር ግን አሁን እጅግ ብዙዎቹ አልተረፉም ነበር።



የተክሌ ድምፅ እጅግ ትንሽ እና ደካማ ስለ ነበር ምሕረት ያለውን በችግር ነው ያዳመጠችው፣ ነገር ግን ከፊታቸው ካለው የዛፎች ድርድር ጋር የተያያዘ እንደ ሆነ ታውቅ ነበር፣ ከበስተ ጀርባቸው በመጣውና በሚያሞቀው የማለዳ ፀሐይ ብሩህ ሆና ፈገግ አለችለት። እግሮችዋ ከበታችዋ የሚቈላለፉ ይመስላሉ፣ ነገር ግን የመጨረሻው ይህ ከሆነ፣ እዚያ መድረስ ትችላለች።

አንዳንድ ጊዜ፣ ከሴት አያትዋ ሞት ጀምሮ፣ የመጓዝ ጥቅሙ (ቁም ነገሩ) ምንድን ነው ስትል ግራ ትጋባለች፤ ነገር ግን አሁን በሕይወት ውስጥ አንድ ኃይለኛ የሆነ ዓላማ ብቻ፣ ጥላ ወዳለበት ስፍራ መድረስ ደግሞም ጋደም ብሎ ማረፍ ከዚያም በኋላ ከቶ አለመጓዝ፣ ስለዚህም ተክሌን በክንዶቿ ውስጥ ማድረግ እና ወደ ብርታት እንዲመለስ እርሱን ማሳረፍ ያለ ይመስላል። ወደ ፊት መጓዙን ቀጠለች፣ እንዲሁም ዛፎቹ ክምችት ብለው ያሉበት ስፍራ እየቀረበ መጣ። ገና አሁንም ጨለማ ሆኖ ሳለ በዚያ ቀደመው የደረሱ፣ በጥላው ውስጥ ቁጢጥ ያሉ፣ እንክብካቤን ለማግኘት ተራቸውን እየጠበቁ ያሉ የተሰባሰቡ ሰዎችን ማየት ቻለች።

እጅግ ብዙዎች ናቸው፣ ብዙ ሰዎች! አሁን እየቀረበች መጣች፣ ሁኔታው ለእርሷ አስገራሚ እይታ ልክ ደቃቃ የሆኑ መጠለያዎች እንዳሉት ሩቅ ስፍራ ድረስ እንደ ተዘረጋ ከተማ - እኩል ሳልሆኑ ቋሚ ብረቶች ላይ በተመጣጣኝነት የተወጠሩ ምንጣፎች እና ወረቀቶች፣ በሺህዎች የሚቈጠሩ ሰዎች በወንዙ ምሥራቃዊ መታጠፊያ ላይ የተሰበሰቡት ነበር፣ ምክንያቱም ታላቁ ወንዝ ዘወትር ወደ ታች ወርዶ ነበርና። ነገር ግን ከዚያ የሚሳብ ውኃ ዝልግልግ ያለ እና ቡናማ ነበር።

በጣም ጸጥ ረጭ ያለ ጊዜ ነበር። እነርሱ በሌላኛው ሰዎች በተሰበሰቡበት ጥግ ቁጢጥ አሉ፤ ደግሞም ገብሬ አዲስ ስለ ደረሱ ተጓዦች ሪፖርት ሊያቀርብ ተክሌን በምሕረት ክንዶች ላይ አድርጎ ሄደ። ፈገግ ለማለት የተጨማደደ ፊቱን ወደ ታች ትመለከተው ነበር፤ ደግሞም እርሷ ፈገግ በማለት አጸፋውን መለሰች። ጠረፉን ከተሻገሩት ጊዜ ጀምሮ፣ ደግሞም ቀጣይ የሆነ የቦምብ ድብደባ

ፍርሃት ካለፈ በኋላ፣ እና እንግዳ የሆነ የደከመ ለላምን ካወቀችበት፣ ነገር ግን ሹል የሆኑ የጉንጭ አጥንቶቼን እና የጕደጕዱ ዓይኖቼን ስትመለከት ልብዋ የተደበቀ ፍርሃትን ያዘ:: ተ ክሌ የሚሞት ከሆነ . . . ነገር ግን የአሳብ ማውጠንጠንዋ ርቆ መሄድ አልቻለም፤ ደረቅ ከሆነው ምድር አንሥታ፣ ወደ ራሷ አስጠጋችው፣ እንቅልፍ ጣላቸው::

*****

«ከቡራን!» የሚል ድምፅ ተሰማ:: «ያንን ተመልከቱ! ስለ እርሱ አንድ ነገር በፍጥነት አድርጉ፣ አሊያም እጅግ የዘገያችሁ ትሆናላችሁ:»

ምሕረት በፍጥነት ተነሣች፣ ምክንያቱም ተክሌን ከእርሷ ላይ ወስደውታል፣ ደግሞም እርሱ ይነጫነጭ ነበር:: ሁለት ባዕዳን የሆኑ ሴቶች ቊልቊል ይመለከቱት ነበር፣ ደግሞም ባዕድ በሆነ ቋንቋ አንድ ነገር ተነጋገሩ:: ፈረንሳይኛ የሚያውቅ የእነርሱ ከሆኑት ሰዎች አንዱ ያስተረጕም ነበር::

«ይህ ልጅ ለተጨማሪ አንድ ጊዜ መምጣት ይኖርበታል፣» አለ:: «እናቱና ቀሪዎቹ ቤተሰቦቹ የት አሉ? ሁላችሁም መምጣት ይኖርባችኋል::»

«እናቴ እና አባቴ ወደ ደቡብ ተወስደዋል፣» አለች ምሕረት፣ «ደግሞም አያቶቼ ሞተዋል:: ያለነው እኔና ተክሌ እንዲሁም አጕታችን ገብሬ ብቻ ነው::»

ከዚያም ወጣት የሆነው ኃላፊ፣ «ኑ» አለ:: ተክሌን በክንዶቹ ላይ አድርጎ ዕንግዳ (ባዕዳን) ከሆኑት ሴቶች ጋር አብሮ መሄድ ጀመረ፣ ደግሞም ምሕረት በቻለችው ፍጥነት ተከተለቻቸው:: ከእነዚህ ግራጫ መልክ (ፊት) ካላቸው ባዕዳን ሰዎችና ባዕድ የሆነ ቋንቋቸው የተነሣ ተስፋ ቆርጣለች፣ ደግሞም የገዛ ሕዝቦችዋ እንክብካቤ ወደሚያደርጉላት በመንገድ ላይ ወዳሉ መጠለያ ካምፖች መሄዱን መርጠዋለች:: ነገር ግን በፊታቸው ላይ ጥልቅ



የሆነ ርኅራኄ እና ግድ መለኘትን ተመልክታለችና ደግሞም የሚችሉትን ሁሉ እንደሚያደርጉ አውቃለችና፣ በእውነቱ በእነርሱ ላይ አልተቈጣችም:: ወንዶች፣ ሴቶች እና ልጆች የተ ጋደሙባቸውን፣ ያረፉባቸውን ወይም ለአንድ ነገር አሊያም ለሌላ የተሰለፉባቸውን እነዚያን ማብቂያ የሌላቸውን መጠለያዎች እያለፉ፣ ለዘላለም የሚሄዱ ይመስላሉ:: እነዚህ ተጓዦች ብዙ አይነጋገሩም ነበር፣ ምክንያቱም በአብዛኛው በአንድ መንገድ ላይ የተጓዙ ናቸው፣ ደግሞም ጕዞው እንዳለቀ ያውቃሉ፣ ደግሞም ሊነጋገሩት ያለ ነገር አልነበረም:: ነገር ግን ምሕረት ባዕዳን የሆኑት ሴቶች በተክሌ ላይ በጣም ባዕድ የሆነ ነገር በሚያደርጉበት ማዕከል ከተክሌ ጋር ተገኝታ ነበር:: ኃላፊው ሰውዬ እርሱን በቅርጫት ውስጥ አስቀመጠው እና በማንጠልጠያ ላይ አንጠለጠለው፣ ደግሞም ሴቶቹ፣ ትንሹ አሳዛኝ ልጅ እያለቀሰ ቢሆንም፣ እየተ መለከቱ ያረጋግጣሉ:: ምሕረት ልታድነው በሞከረች ጊዜ፣ እንዳታደርገው በጨዋነት ተከለከለች፤ ደግሞም ልክ እንደ ልብስ ጨርቅ አጋድመው ሲመዝኑት መመልከት ይኖርባት ነበር::

«ለእኔ ስጡኝ፣» ስትል ጮኸች:: «እርሱ ፈርቷል:: ምንድን ነው እያደረጋችሁት ያለው?»

ኃላፊው ሰውዬ ጸጥ እንድትል አደረጋት:: «አትፍሪ፣» አላት:: «እየመዘኑትና ከብደቱን እየለኩት ነው:: እርሱ ታምሞአል፤ ተ ጨማሪ ምግብ ይሰጡታል::»

አየሩ ቀዝቃዛ እና ጨለም ወዳለ ክፍል እንደገና እየተጓዙ ነበር:: በመሬቱ ላይ ምንጣፍ ነበር፤ ደግሞም የሕዝብ መግተልተል አልነበ ረም፣ በዚያ የነበሩት በመካከላቸው አባት ወይም እናት የነበሩበት ሕፃን ልጅ ወይም ልክ በትክክል ተክሌን የሚመስሉ ልጆች የጕደጕዱ ዓይኖች፣ ያበጡ የሆድ ዕቃዎች፣ እንዲሁም ጭራሮ መሳይ እግሮችና እጆች ያሉዋቸው ልጆችን የያዙ የቤተሰቦች ቡድኖች ነበሩ:: ሌላ ባዕድ የሆነች ሴት ለላምታ ሰጠቻቸው እና ባልተያዘ ምንጣፍ ላይ እንድትቀመጥ ለምሕረት ምልክት ሰጠቻ ት:: ኃላፊው ሰውዬ ሁለት ኩባያ ወተት፣ ጥቂት ብስኩቶች እና ጕድጓዳ ሳህን ደግሞም ማንኪያ አመጣላት::

«ጠጪ፣» አላት፣ «ወንድምሽን መግቢውና አጠጪው:: ብስኩቱን በወተቱ ውስጥ ለባብረሽ በየጊዜው ጥቂት ስጭው፤ ደግሞም ለራስሽም ብዪ:::»

ተክሌ በክንዶችዋ ላይ አርፎ፣ ወተቱን በማንኪያ እየሳበ የብስኩቱን ፍትፍት እየወሰደ ሳለ፣ ገነት ደርሰው እንደ ሆነ ምሕረት በሚጫጫን ስሜት ውስጥ ሆና ትገረም ነበር:: የመሬት ምንጣፍ በሆነው ጣራ በኩል የብርሃን ነጸብራቆች ሰርገው ገቡ፣ ደግሞም እልፍ ብሎ የቤቱ ማዕዘን ከፍተኛ ገነቢ ንጥረ ነገር ያለው ወተት በስታቲ ድስት ይዘጋጅ ነበር:: ነገር ግን በዙሪያዋ ወደ ጉዞዋቸው መጨረሻ የደረሱ ሰዎች ሁሉ ነበሩ:: በታመመ ወንድማቸው ወይም እኅታቸው ዙሪያ የተሰበሰቡ ልጆች እንኳ ጸጥ ብለው ይቀመጡ ነበር፣ ደግሞም በዓይኖቻቸው አርቀው በትዕግሥት ይመለከቱ ነበር፣ በአብዛኛው እጅግ የደከሙ በመሆናቸው፣ ወደ ውጭ ወጥቶ መጫወትን የሚፈልግ አልነበረም፣ ደግሞም ከመጠለያው ውጭ ሙቀቱ እየጨመረ ነበር የሚሄደው:: ምሽት በሚሆንበት ጊዜ፣ መላው ቤተሰብ በአንድ ላይ ለማንቀላፋት ጋደም ይሉ ነበር፣ ደግሞም ምሕረትና ተክሌም እንዲሁ ያደርጉ ነበር:: ሕልም በምታይበትም ጊዜ፣ ከበረሃው ባሻገር፣ «ከዚህ በኋላ አንጓዝም፣» የሚለው የተክሌ ድምፅ ይሰማት ነበር::



# 9

ተስፋዬ በቊጥቋጦው ውስጥ ዕንቅፋት መትቶታል:: የሰዓት አቈጣጠሩ ጠፍቶበታል፣ ደግሞም በማለዳ ከበስተኋላው የምትወጣውን እና በምሽት ከፊት ለፊቱ የምትጠልቀውን የፀሐይን ሁኔታ ንቁ ሆኖ ይከታተል ነበር:: ፀሐይ ከአናት ሆና በምታቃጥልበት ጊዜ፣ የሚስቱን መደረቢያ ልብስ ያወጣል፣ በጭራሮዎች ላይ ይዘረጋ እና በጥላው ውስጥ ጋደም ይላል:: በምሽት፣ ከፀሐይዋ መጥለቅ ረጅም ጊዜ በኋላ በሰማዩ ላይ እሁንም ወዳለው ሞቃታማ ወደ ሆነው ደምቆ የሚታይ ብርሃን ለመድረስ ይታገላል:: ነገር ግን አንዳንድ የሌሊቶች ዕንቅልፍ አስቸጋሪ ነበር፣ ምክንያቱም አየሩ ሞቃት ቢሆንም፣ እርሱ እጅግ ይንቀጠቀጥ ነበር፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ይቃጠል እና በሌላ ጊዜ እንደ በረዶ ይቀዘቅዝ ነበር::

ለራሱም፣ «የወባ በሽታ ይዞኛል፣» ብሎ ይናገራል:: «ከዚህ ብዙ ርቄ መሄድ አልችልም::»

ነገር ግን የውኃ ጥማት እያቃጠለው ነበር፣ የሚችለውን ያህል ጥንቃቄ ከማድረጉ ባሻገር ቢያደርግ በውኃ መያዣው የያዘውን ውኃ ሊጨርሰው ተቃርቦአል:: ደግሞ የቀረው ነገር ቢኖር ሙቀት እና ጨው ጨው የሚለው ነበር:: ምግቡ ሁሉ አልቋል:: ነገር ግን የሚበሉ ቅጠሎችን እና ሥሮችን አግኝቶአል:: ደግሞም እንበጦችን እና ትላትሎችን ይበላ ነበር:: አሁን ደግሞ ትኩሳቱ የረሃብ ስሜቱን ከልክሎለታል::

ፀሐይን በምዕራብ አቅጣጫ ምን ያህል ርቀት እንደ ተከተላት አያስታውስም:: ጋደም ባለበት እና የመጨረሻዎቹን የውኃ ጠብታዎች በጠጣበት ጊዜ በሦስተኛው ቀን ምሽት እንደ ነበረ ያስባል:: ብዙ በመጨነቅ እጅግ ግራ ተጋብቶ ነበር፣ ወዲያውም አስቸጋሪ

ወደ ሆነ እንቅልፍ አመራ፣ ባዕድ በሆኑ ሕልሞችና ቅዠቶች እንቅልፉ ተቋረጠበት። ረጅም በሆነ መንገድ ላይ የቆመ፣ በሁሰት አቅጣጫዎች የሚጐተት ይመስለዋል፤ ጭጋጋማ የሆነ የሚስቱ ምስል ወደ ኋላ ይጐትተዋል፣ ደግሞም ሕያዋን የሆኑ የልጆቹ ምስሎች ወደ ፊት ይጐትቱታል። በጣም አልቦት ሳለ፣ ነቃ፤ ደግሞም ከተሰመደው እጅግ ብዙ እንደ ተኛ አውቋል፣ ምክንያቱም ፀሐይዋ ከበስተኋላው ወጥታሰች፣ ደግም ቀድሞውኑ መሬቱን ሸፍናዋሰች። ዓይኖቹን ከፍቶ ሰመመልከት አልፈሰገም ነበር። እድገታቸው የተገቱ ዛፎች እና እሾህ እንዲሁም ድንጋያማ ዓቀበቶችን ለረጅም ጊዜ ተመሰከታቸው፤ ደግሞም ከጥማቱ ባሻገር፣ በዚያ ረጅም መንገድ ሰመመሰስ፣ ከሙና ጐን ሊተኛ እንዲሁም ዓይኖቹን ዳግመኛ ከቶ ሳይከፍታቸው በደስታ ይመሰስ ነበር።

ነገር ግን ዓይኖቹን ከፈተ እና ሰረጅም ጊዜ አልተንቀሳቀሰም ነበር፣ ምክንያቱም እንደገና በእውነት ሕልምን ያልም ነበርና። በተ ጨማሪም፣ ትኩሳት በሰዎች አእምሮ ውስጥ የሚፈጥረው መምታታት አለ፣ ደግሞም ያየውን ሰማመን እምቢ አሰ። ነገር ግን ፀሐይዋ፣ ቀድሞውኑ ሞቃት ሆና፣ በጀርባው ላይ አንጸባርቃ ነበር፣ ደግሞም ያ እውነት ነበር። ከንፈሮቹ ተጣብቀው ነበር፣ እንዲሁም ሰውነቱ እና ከፍ እያለ የሚሄደው ሙቀቱ ካመጣው ላብ ጋር ከብዶ ነበር፤ ደግሞም ያ እውነት ነበር። ነገር ግን ያ አነስተኛ ከጭቃ የተሠሩ የመኖሪያ ቤቶች ሰብሰብ፣ በትንሽ አረንጓዴ ነገር የተከበበ ነገር እውነት ሲሆን ይችላልን? የደከመ አእምሮው ብዥታ፣ ከበላይ ካለው የውኃ ነጸብራቅ ጋር እንዲሁም ሩቅ ካሰው የደን ዛፎች ጋር የተጣመረ መሆን አለበት ሲል አሰበ። ነገር ግን ደስ የሚያሰኘው የሕልም ፈንጠዝያ እንዳያሸሸው ፈቃደኛ ባለመሆን ደስ በማያሰኝ ሁኔታ አትኩሮ ሲመለከት፣ በትከሻዋ ላይ እንስራ የያዘች እና ወደ ወንዝ እየሄደች የነበረች ሴት ከቤቶቹ ከአንዱ ወጥታ ሄደች።

የሴቲቱ መኖር መታየትን እውነታ ስሕተት አልነበረም። ከእግሮቹ ጋር ታገለ ደግሞም ከአራት ቀናት በኋላ ከዚህ የሕይወት



መኖር ምልክት ጋር ተላተመ። ውኃ እንድታመጣለት እየለመነ ሴቲቱን ተጣራ፣ ነገር ግን በፍርሃት ተመልሳ ሄደች፣ ደግሞም ወደ ቤትዋ ተመልሳ ገባች። ከአፍታ በኋላ ባልዋ መኩትኩቻ ተሸክሞ በበሩ መግቢያ መንገድ መጣ።

«ከየት ነው የመጣኸው ደግሞስ አንተ ማን ነህ?» ብሎ ጠየቀ፣ ደግሞም ዓይኖቹ በጥርጣሬ ተሞልተው ነበር።

ተስፋዬ በዝምታ ቆመ። ይህ የመንግሥት ግዛት ከሆነ፣ እንግዲያውስ የማምስጡ ተግባር አልቆሰታል፣ ደግሞም ወዲያው ተመልሶ ወደ ካምፕ ይመሰሳል፣ ደግሞም የወንጀለኝነትን ክስ እንዲሁም የሞት ፍርድ ይጋፈጣል። በተጨማሪም፣ ሰዎች በቍጥቋጦዎቹ ይዘዋወሩ ሰለ ነበሩ ሽፍቶች ይነጋገሩ ነበር፤ ይህ ሰው ያልታጠቀ ሰው ይመስላል፣ ነገር ግን በእጁ ያለው መኮትኮቻ ከፍተኛ መሣሪያ ይመስላል። ከዚያም ዕድል ፊትዋን ያዞረች መሰሰ፤ ብርድ ብርድ የሚልና የሕመም ስሜት ተነሣበት ወዲያውም መንቀጥቀጥ ጀመረ። ጥርሶቹ ተንገጫገጩ፣ ራሱም ዞረበት። ራሱን ሰቶ ፣ ነገር ግን ሙቀት እና ውኃ እየፈሰገ፣ በምድር ላይ ወደቀ።

ሴቲቱ ከትንሽ የርጎራኄ ጩኸት ጋር እየሮጠች ወጥታ ከአጠገቡ በርከክ አለች። «ከእነርሱ አንዱና ሌላው ሰው ነው፣» አለች። «ከካምፑ አምልጦአል ደግሞም በወባ በሽታ ተይዟል።»

«ትክክል እንደ ሆንሽ አሰባሰሁ፣» አላት ባልዋ፣ ዘና ባሰ ሁኔታ እግሮቹን እያንቀሳቀሰ። «ከዛፍ ሥር ከጥላው በታች ተሸከመን እንውሰደው እና ውኃ እንሰጠዋሰን። በኋላም፣ መነጋገር ይጀምራል።»

ተስፋዬ ቀኑን ሙሉ በማንጐ ዛፍ ጥላ ሥር ተኛ፣ ትኩሳት ከፍ ባለ ጊዜ የሚያቃጥለው መስሎ ታየው። ነገር ግን ዕሰቱ መልካም ነበር፣ ምክንያቱም ውኃ ተትረፍርፎ ነበር፣ እንክብካቤ እና ደግነት የተሞላበት ሰብአዊ ርኅራኄም ነበር። የትንሽዋ መንደር አባላት የሆኑ ሰዎች እያንዳንዳቸው ይመጡ እና አትኩረው ይመለከቱት ነበር። በግምት ስምንት ዓመት የሚሞላው ልጅ ራሱን ጠባቂ

አድርጎ ሰየመ እና ዝንቦቹን እያባረረ እና በከንፈሮቹ ላይ ውኃን እያራሰው ቀኑን ሙሉ በአጠገቡ ተቀመጠ። በተጨማሪ ምግብ፣ እንጀራ እና የምሥር ወጥ እንዲሁም ማንጎ አመጡለት። ስግብግብ ብሎም በላ እና ጠጣ፣ ደግሞም ምሽት ላይ ትኩሳቱ ለቀቀው፤ እንዲሁም በዚያ ምሽት መልካም እንቅልፍ እንደሚወስደው ያውቅ ነበር። መሳው ሰውነቱ ፀሐይ ከመግባቱዋ የተነሣ በመጣው ቅዝቃዜ ተሞልቶአል፣ አሁንም በወንዙ ውስጥ የሚፈስሰውን ውኃ ነጸብራቅ እና ከማገዶ እሳት የሚወጣውን ጢስ እየተመለከተ አሁንም ጭምር እንደ ተኛ ነው። ከዚያም፣ ብልጭ ድርግም በሚል የከዋክብት ብርሃን፣ በመጀመሪያ አይቶት የነበረው ሰው መጣና ከአጠገቡ ተቀመጠ።

«የምትጓዘው ሩቅ አይደለም፣» አለ በድንገት። «አንተ ከጠረፉ በትንሹ ነው ርቀህ ያለኸው። ነገ ማለዳ ላይ ጉዞ የምትጀምር ከሆነ፣ ከነገ ምሽት በፊት ትሻገራለህ። በዚያም ከሥጋት ነፃ ትሆናለህ።»

«ከሥጋት ነፃ?» ሲል ተስፋዬ ጠየቀ። ሲጠቀሙት ባዕድ የሆነ ቃል ይመስል ነበር። «ከጠረፉ በስቲያ ምግብና ውኃ ይኖራልን?»

ሰውዬው ትከሻውን ነቀነቀ። «ሌሎች ሄደዋል፣» አለ፤ «ደግሞም አልተመለሱም። እነርሱ ፀሐይዋን ተከትለህ ወደ ምዕራብ የምትሄድ ከሆነ፣ በጣም ቅርብ የሆነ ካምፕ አለ ይላሉ። ወደ ሰሜንም ሌላ ካምፕ አለ፣ ነገር ግን ሩቅ ነው። ውኃ አለ፣ የትልቁ ወንዝ ገባር የሆኑ ብዙ ወንዞች አሉ። በማምለጥህ ዕድለኛ ነህ። ሁለት ሰዎች ትናንት መጥተው ነበር። ሌሎች በቁጥቋጦዎቹ እሳት ውስጥ ሞተዋል አሉ?»

ተስፋዬ ኀዘን ተሰማው። ከእነዚያ ከሁለቱ ጋር አብሮ መጓዙን ይወድደው ነበር፤ ደግሞም እነማን ይሆኑ ሲል በአሳብ ባዘነ። በሕይወት ያሉት እና የሞቱት እነማን ይሆኑ? ነገር ግን ምናልባት ፀሐይዋን ተከትለው በምዕራብ አቅጣጫ ወዳለው ካምፕ ሄደው ይሆናል ደግሞም እርሱ በሕይወት ወደሚገኙት ልጆቹ መጓዝ ይኖርበታል። ስለ እንግዳ ተቀባይነቱ ሰውየውን አመሰገነው ደግሞ



በማለዳ ተነሥቶ እንደሚሄድ ተናገረው። ነገር ግን ተነፈሰ፣ ምክንያቱም ከካምፑ እና ከቁጥቋጦው በኋላ፣ ይህን ስፍራ ትቶ መሄድ ልክ ገነትን ትቶ መሄድ ይመስል ነበር።

«ይህ ልክ እንደ አዲስ መንደር ይመስላል፣» አለ። «እዚህ ለ ረጅም ጊዜ ኖረሃልን?»

ሰውየው ግንባሩን ቋጠረ።

«እኛ ከመኖሪያችን የተፈናቀልን ሰዎች ነን፣» አለ በቍጣ። «ቤቶቻችን እና መሬታችንን ከሰሜን በከባድ መኪናዎችና በአውሮፕላን ላመጧቸው ዓማፂያን ሲሉ ወሰዱብን። ወደምንችለው ስፍራ ሁሉ እንሄዳለን፣ ደግሞም እንደ ሁኔታው ተክሎችን እንተ ክላለን፣ ነገር ግን ከጕሳዎቻችን ርቀን ነው ያለነው። በተጨማሪም፣ ገባር ወንዝ ጥልቀት የሌለው ነው፣ ምናልባትም በታላቁ የሙቀት ወቅት ይደርቅ ይሆናል። በዚያን ጊዜ እኛም እንደዚሁ ጠ ረፍን መሻገር ይኖርብናል።»

«ብዙዎች ሰዎች ጠረፉን ይሻገራሉን?»

«ጥቂቶች ይሻገራሉ፣ አንተ ካመለጥክበት ባሻገር ሌሎች ካምፖች አሉ። ብዙዎች ለማምለጥ ሞክረዋል፣ ነገር ግን አንዳንዶች በጥይት ተመትተው ወድቀዋል፣ እንዲሁም ሌሎች መንገድ ጠፍቶአቸው፣ በረሃብ ወይም በጥማት ወይም በሃሩሩ ንዳድ ወይም በቍጥቋጦዎች ውስጥ በእባብ ተነድፈው ሞተዋል። አንዳንዶች በድጋሚ ተማርከዋል። ነገር ግን አሁንም ለማምለጥ ይሞክራሉ!»

ተስፋዬ ፈገግ አለ። የጥንካሬ ስሜት ተሰማው፣ ደግሞም ትኩሳቱ የለቀቀው ይመስላል። «እነዚያ ልክ እንደ እኔ፣ ልጆቻ ቸውን በቤት ትተው የተወለዱ ናቸው፣» አለ በጸጥታ። «ይፈልጉሃል። በሕይወት ሳሉ ወደ እነርሱ መሄድ ይኖርብሃል። ሚስቴ በቍጥቋጦው ውስጥ ሞተችብኝ፣ ነገር ግን እንድሄድ ነግራኛለች።»

«ደግሞስ እነርሱም እንደዚሁ ጠፍተው ቢሆንስ?»

ተስፋዬ ትከሻውን ነቀነቀ:: «እንግዲያውስ እኔም እንደዚሁ ልጥፋ:: የሚኖሩለት የቀረ ነገር ማን አለ? ነገር ግን ቢያንስ ቢያንስ በገዛ ሕዝቦቼ መካከል ልጥፋ::»

የሚባል ነገር ያለ አይመስልም ነበር:: ሁሉም ነገር ከዚህ ቀደም ተብሎአል፣ ደግሞም መጪው ጊዜ ግራጫማ የሆነ ጭጋግ ነው:: ሰውየው ወደ ጉጆው ሄደ እና የተበጣጠሰ የብርድ ልብስ ይዞ መጣ እና በእንግዳው ላይ ጣል አደረገው፣ ደግሞም እንዲተኛ ነገረው:: ተስፋዬ በቅርቡ ሊደርቅ የተገባው በሆነው ጥልቀት የሌለው ወንዝ ላይ፣ ከምዕራቡ በተቃራኒ ጠቍረው ባሉት ከበላይ ባሉ ዛፎች ዓይኖቹን ተከለ:: ለጥቂት ጊዜ ይተኛል፣ ከዚያም በኋላ ይነሣ እና እየጠፉ ባሉ ከዋክብቶች እየተመራ በቀጥታ በጨረቃ ብርሃን ይጓዛል:: ምንም ጊዜ ማባከን አይኖርበትም፣ ምክንያቱም ነገ ትኩሳቱ ይመለሳል፣ ስለዚህም ማረፍ ይኖርበታል::

ነገር ግን ለረጅም ጊዜ እንዲህ አይሆንም፣ ምክንያቱም ከጠረፉ ብዙም ሩቅ አይደለም፤ ወደ ሰሜን መጓዝ ይኖርበታል፤ ደግሞም ታላቁን ወንዝ በመከተል ራቅ ወዳለ ሰሜናዊ ክፍል መሄድ ይኖርበታል:: አንድ ቀን ወደ ምሥራቅ እና ጠረፉን ተሻግሮ ወዳለ ስፍራ ይመለሳል-ምሕረትን የያዙ ዝናቦች ይዘንባሉ. . . ታላላቆቹ ተራሮች ደመና በነጐድጓድ መልክ ያከማቻሉ. . . በተለነጣጠቀው መሬት ላይ አረንጓዴ ልብስ ይሸፍነዋል . . . ልጆቹ እርሱን ለመቀበል ሮጠው ይመጣሉ:: ነገር ግን አንድ ሰው ከአመክንዮ እና ከጋራ መረዳት ስንለስት ሊያመልጥ የሚቻለው በእንቅልፍ ውስጥ ብቻ ነው፤ ምክንያቱም ሕልሙ ይኸው ነበር::



# 10

የሚያዝያ ወር አየር ንብረት እየሞቀ እየሞቀ ከመሄዱ በቀር፣ የእነ ምሕረት ቸሩ ሽማግሌው ካህን ከሚኖሩበት አጠገብ የነበረችው ደቃቃ መጠለያቸው እየፈረሰች እየፈረሰች ከመሄድዋ በቀር፣ ምሕረትና ተክሌስ ጠረፍ ላይ ካለው ትልቁ ካምፕ በሰከነ ሁኔታ ተቀምጠው ነበር:: ተክሌ ልዩ እንክብካቤ በሚደረግበት የመመገቢያ ጣቢያ የዕለቱን አብዛኛውን ክፍል አሳልፎአል፣ ደግሞም ክብደቱ ጨምሮአል፣ ነገር ግን አሁንም እንደ ደነዘዘና እንደ ተበሳጨ ነበር፣ ደግሞም ለመሄድ እጅግ የደከመ ይመስላል:: ጠዋት በማለዳ ወይም ከሰዓት በኋላ ማምሻው ላይ፣ የዘንባባ ዛፎች ጥላ ረጅም ሆኖ በሚያድግበት ጊዜ፣ ማገዶ ለመሰብሰብ እና እንጀራ ለመጋገር ደረቅ የሆነውን የወንዙን ውኃ መፍለሻ ስፍራ በመከተል ይዘዋወራሉ:: በማለዳው ክፍለ ጊዜ፣ ምሕረት በትልቅ የውኃ ጋሪ ከሚመጣው ውኃ ለመቅዳት (ለመውሰድ) ወረፋ ትይዛለች:: በአንድ ወቅት የነበራት ጉጉት፣ ንቁ የሆነ አእምሮ፣ አሁን በኀዘን እና በስልቹነት ደንዝዞአል፣ ወደፊት መመልከትን እንቢ ብሎአል:: እርሷና ተክሌ ዛሬ አብረው መሆናቸው በቂ ነበር፣ ምግብና ውኃ አለ፣ ደግሞም ከጥላው ሥር ጋደም ማለትና ማረፍ ትችላለች:: ገብሬ ሥራ የበዛበት ኃላፊ ሆኖአል፣ ነገር ግን በእያንዳንዱ ቀን ይጐበኛቸዋል፣ ደግሞም እሮጊት የሆነችው የካህኑ ሚስት ለእነርሱ ደግ ነበረች:: ይህ በቂ ነበር:: አንድ ቀን ምሕረት ባዶ ወደ ሆነው የወደፊት ጊዜ ተመለከተች፣ ነገር ግን ምንም ተስፋ አልነበረም::

በቀጣዩ መጠለያ ያለ ሕፃን እያለቀሰ ስለ ነበረ፣ አንድ ማለዳ ላይ በጣም ማልዳ ተነሣች፣ ጩኸቱ ጉርናና ነበር፤ ደግሞም እናቱ ልታባብለው አልቻለችም ነበር:: ትንሽ ጭጋግ ከወንዙ ላይ ተነሣ ደግሞም አሁንም ቀዝቃዛ ነበር:: ምሕረት ለጊዜው ጋደም ብላ

ነበር፣ ከዚያም የራስዋን ብስጩ ልጅ አዝላ ሴቲቱ ወደ ተቀመጠችበት ስፍራ ሄደች።

«ታምሞአል?» ስትል ምሕረት ጠየቀች።

«የታመመ ይመስለኛል፣» ስትል ሴቲቱ መለሰች። «ቆዳዎቹ ያተኩሳሉ ደግሞም ዓይኖቹ ቀልተዋል፣ በእንባም ረጥበዋል። ውኃ ሰጠሁት ነገር ግን ሊውጠው አልቻለም። ጉሮሮው የቈሰለ ይመስለኛል።»

«ወደ ማዕከሉ ልትወስጂው ይገባል። ነርስዋ ትመረምረዋለች።»

«ምናልባት ትመለከተው ይሆናል፤ ነገር ግን የታመሙት ብዙዎች ናቸው፣ እንዲሁም እጅግ ግሉአል፣ እዚህ ከዛፎቹ ሥር ትንሽ ቀዝቀዝ ያለ ነው። በእጆቼ ለትንሽ ጊዜ ካቀፍሁት ይተኛል።» ተክሌ ከእንቅልፉ ተነሣ ደግሞም በእንቅልፉ እየናወዘ ሽቅብ ወደ እኅቱ ተመለከተ። በምሕረት ጭን ላይ እየወጣ ወደ ታመመው ጓደኛው ተመለከተ። «ኪሮስ ታምሞአልን?» ሲል በኀዘን እንጉርጉሮ ጠየቀ። «ዛሬ ከእኔ ጋር መጫወት አይችልምን?» እጁን እንሥቶ የኪሮስን ራስ ነካ አደረገው። ልክ አብዛኛውን ጊዜ እንደሚሆነው፣ የተላጨ አልነበረም፣ ነገር ግን ጠጕሩ ቀይ እንዲሁም ከረሃብ የተነሣ ጥሩነቱ ያልተሟላ ነበር። ለጥቂት ጊዜ በጸጥታ አብረው ተቀመጡ፣ ነገር ግን ማልቀሱን አላቆመም፣ ደግሞም ኪሮስ ውኃ አልጠጣም ነበር።

«በመጨረሻም እናቱ ወደ ማዕከሉ እወስደዋለሁ፣» አለች፤ ደግሞም በወንዙ መታጠፊያ በኩል በማለዳው ብርሃን ሄደች። ነገር ግን ወዲያው ተመልሳ መጣች፣ እንዲሁም ዓይኖቿ በፍርሃት ተሞልተው ነበር። «በመቶዎች የሚቈጠሩ ይመስላሉ፣» አለች፤ ደግሞም የሁሉም ልጆች ዓይኖች ቀልተዋል፤ እንዲሁም አፍንጮቻቸው ንፍጥ በንፍጥ ሆነዋል፤ ደግሞም ሁሉም በትኩሳት እየተቃጠሉ ናቸው። አንዳንዶች በቀይ ሽፍታ ተሸፍነዋል። ተራዬ የሚደርሰው እኩለ ቀን አካባቢ ነው። በጥላው ውስጥ እቀመጥና በኋላ እሄዳለሁ። በልጆቻችን መካከል የተነሣ አንድ የሆነ በሽታ አለ። ተክሌን ከዚህ አርቀሽ ብትወስጂው የተሻለ ነው።»



«እታች በመመገቢያው ጣቢያ፣ ከስዊዘርላንድ ቀይ መስቀል የመጡት ሜሪ እና የሥራ ጓደኞችዋ ኩፍኝ በሽታን እየተዋጉ በትጋት እየሠሩ ናቸው። በጥቂት ቀናት ውስጥ ነው በሽታው የተከሰተው፤ ነገር ግን እነዚያን ትናንሽ የመነመኑ ሰውነቶች፣ ተጨማሪ የትኩሳት ሰለባ መሆንን ለመቋቋም እጅግ በረሃብ የጠወለጉ ሰውነቶችን እያጠቃ እንደ ሰደድ እሳት ተሰራጨ። ከተወሳሰበ የኩፍኝ በሽታ፣ ከማጅራት ገትር፣ ከጆሮ ደግፍ በሽታ፣ ከተቅማጥ እና ትውከት እንዲሁም ከድርቀት የተነሣ እንደ ዝንቦች ሞቱ፣ ምክንያቱም ወደ ጨጓራ የሚገባውን ቱቦ ለማስተላለፍ እና አመጋገብን ሁሉ ለመቆጣጠር ለመምራት በቂ ባለሙያዎች አልነበሩም። በአንዳንድ የካምፑ ክፍሎች ውስጥ በጸጥታ የሚደረጉ ልቅሶዎች የማይሰሙበት ገሰልተኛ የሆነ ጊዜ አልነበረም። እነዚያን ትናንሽ አሳዛኝ ጥቅልሎች እቤት ውስጥ በተሠራ ወሳንሳ የሚሸከሙ ሰልፈኞች የተሰመደ እና ልብ ሳይባሉ የሚያልፉ ሆነዋል። በመቃብር ስፍራዎች ያሉ ቁልሎች መደዳ በመደዳ ሆነው በሚንቀለቀለው አድማስ ማዶ ተዘጋግተዋል። ሙቀቱ ከፍ ብሎአል፣ እንዲሁም ወንዙ እየቀነሰ እየቀነሰ ሄዶአል።

ኪሮስ ሕመሙ እንደ ጀመረው ብዙም ሳይቆይ ሞተ። በተራው በማዕከሉ የመታከም ዕድል አግኝቶ ነበር፣ እነርሱም የሚችሉትን ሁሉ አደረጉ፣ ነገር ግን ብዙ ከተጐዳ በኋላ ነበር የደረሰው፣ ከቀዝቃዛማው ተራራማ አገር እስከዚያ የሚወስደው ጕዞ ወደ ጕዳት ወሰደው። በሦስተኛው ቀን ማለዳ ላይ የሚያደርገው ለቅሶ አበቃ። በፍጥነት እየተነፈሰ፣ የተሰነጣጠቁ ከንፈሮቹን በውኃ ለማርጠብ ነገር ግን መልሶ ለማስወጣት ከፍቶ በእናቱ ክንዶች ላይ ተኛ። ከዛፎቹ በታች ቀዝቃዛ ስለ ነበረ፣ ደግሞም አሁን ልትሰጠው የምትችለው ነገር የእጆችዋን እቅፋት ስለ ነበረ ወደ ማዕከሉ አልወሰደችውም ነበር። ትንሽ ትንፋሽ በሰጠበት፣ ወደ እርስዋ መለስ ባለበት እና ትግሉን ባቆመበት በቀጣዩ ማለዳ ወቅት ፀሐይዋ በሰማይ ላይ ከፍ ብላ ወጥታ ነበር። ምሕረትን ጣራቻት፣ እና

«የሞተ ይመስለኛል፣» አለች። «ባለቤቴን እና ካህኑን ብትጠሪ

ይሻላል፡፡» ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየተወዛወዘች ለብቸኛው ልጇ፣ ለኪሮስ፣ እያዘነች አለቀሰች፡፡

ምሕረት በልቅሶውና በጸሎቱ ላይ ተካፈለች፣ ነገር ግን ተክሌ እንዲቀርብ አልፈቀደችም፣ ይሁንና፣ በዚያ በመጀመሪያው ማለዳ በኪሮስ ላይ ጋደም ብሎበት እና ነክቶት ነበርና ልብዋ በፍርሃት ክብዶባት ነበር፡፡ ቀኑን ሙሉ ትመለከተው ነበር፣ ደግሞም የግንባሩን ሙቀት በዳሰሳ ለማወቅ በሌሊት ትነቃ ነበር፡፡ ነገር ግን ከአሥር ቀናት በኋላ ነበር በጭንዋ ላይ ጋደም ብሎ ስለ ራስ ምታት ማጉተምተም የጀመረው፣ ደግሞም ዓይኖቹ የቀሉት፣ ይህ የሕመሙ መጀመሪያ ስለ ነበረ፣ ሰውነትዋ በፍርሃት ራደ፡፡

ነገር ግን ልጆቹ በአሁን ሰዓት በመርፌ መድኃኒት የተወጉ ስለሆነ፣ ደግሞም ተክሌ የጀግና ትግል አደረገ፡፡ በካምፑ ውስጥ ብዙ ሳምንታትን አሳልፈዋል፣ ደግሞም በሽታውን ለመቋቋም አድጎ ነበር፡፡ ጉርናና ድምፅ በሚጀምርበት ጊዜ ጉሮሮውን ውኃ ታ ረጥብለታለች፣ ደግሞም ከራስዋ ድርሻ ውኃ በመውሰድ ሰውነቱን በውኃ ታርስለታለች፡፡ በማለዳው ቀዝቃዛ ጊዜ ወደ ማዕከሉ ትወስደዋለች፣ እነርሱም መድኃኒቶችን ይሰጡት እና ደግሞም ዓይኖቹን ያክሙለት ነበር፡፡ በአራተኛው ቀን አቃዣት ደግሞም በሕይወት ሊኖር ነው ስትል አሰበች፤ ከዚያም ሊሆን ያለው ነገር ምን እንደሚሆን፣ ከእርሱ ውጭ መጪው ጊዜ ምን እንደሚመስል ለማሰላሰል የደፈረችው በዚህ ጊዜ ብቻ ነበር፡፡

በምሽት ከመጠን በላይ ያልበው ነበር፣ ደግሞም የሰውነቱ ሙቀት እየወረደ መጣ፡፡ በጉርናና ድምፅ የሚያደርገው ጩኸት አቁሞአል፣ ደግሞም ደክሞ እና አምሞት፣ ነገር ግን በሰላም አንቀላፍቶ በክንዶችዋ ውስጥ ተጋድሞአል፡፡ እርሱን ከማጣት ለጥቂት ስለ ዳነች፣ ደግሞም እርሱ ተመልሶ ስለ ተሰማት ጉጉ በሆነ መልኩ መጪውን ዘመን ትመለከታለች፡፡ እንዲሁም መጪው ዘመን አንድ ላይ እንደሚያኖራቸው ተገነዘበች፡፡ በዚህ የሚያቃጥል የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆዩ ወይም ምን ዓይነት ለውጥ ሊመጣ እንደሚችል አታውቅም ነበር፣ ነገር ግን ተክሌ አሁንም እጆችዋን ይይዛል፣



በምሽት ደግሞ ከጐንዋ ይተኛል፡፡ ሕይወትዋ አሁንም ዓላማ ያለበት ነው፤ ደግሞም አንድ ቀን የሙቀቱ ወቅት ያልፋል . . . አንድ ቀን ተክሌ እየጠነከረ እና እየቆነጀ ይሄድና ያድጋል. . . አንድ ቀን ዝናብ ይዘንብና ሰብሎች ያድጋሉ እንዲሁም እርሷ እና እርሱ በአንድነት ጠረፉን ተሻግረው ይሄዳሉ፡፡ በዚያን ጊዜ እርሷ ትልቅ ትሆናለች፡፡ አብረዋቸው የሚመለሱ አያቶችም ሆነ ወላጆች ስለማይኖሩ፣ በዚህ ነጥብ ላይ አሳብዋ ግልጽ ያልሆነ እና ያልተለየ ሆነ፡፡ ከዚያም፣ ያለቀ የምሽት (ልብስ) ለብሳ እየጠበቀች ሳለ እንቅልፍ ሊወስዳት ተቃርቦ በነበረበት ጊዜ የፍቅሬን ድምፅ የሰማች መሰላት፡- «ከጥቂት ወራት በኋላ፣ እመጣና እፈልግሻለሁ፡፡ ዝናቡ ይዘንባል፡፡»

ተክሌን በበርኖሱ ላይ አስተኛችው፣ እርሷም ደግሞም አጠገቡ ተዘርግታ ተኛች. . . በአበባ የተሸፈኑ ተራሮች ላይ እየሮጠ፣ በእርሻ መሬቶች ላይ እያሳበረ፣ እርሷን ለማግኘት ፍቅሬ እየመጣ ነበር፡፡ እርሷ ወጣት እና ቆንጆ ነበረች፣ እንዲሁም ብሩህና በጥልፍ የተሠራ ልብሷን ለብሳ ነበር፤ ደግሞም የሚያንጸባርቀው አረንጓዴው ምድር ዝናብ ዝናብ ይሸትት ነበር፡፡

# 11

ተስፋዬ በቊጥቋጦዎች በኩል እየተጓዘ ሲሄድ ወደ ሌላ ትንሽ ማ ረፊያ ስፍራ መጣ። ከለሜን ምዕራብ የሚመጣውን ወንዝ እንዲከተል እና ሩቅ ያልሆነው ጠረፍ እንዲሻገር ነግረውታል። በበቂ ውኃ ትኩሳቱ በርዷል፣ ደግሞም በወንዝ አቅራቢያ የሚኖሩ ሰዎች ደጎች ነበሩና ምግብ ሰጥተውታል። እየተጓዘ ሳለ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተገናኘ፣ በዚህ ጊዜ በእርግጥ ተሻግረው ነበር፣ ብዙ ጥንካሬም ተሰማው።

ብዙዎቹ ተጓዦች በሙቀቱ እና በጉዞው አደጋዎች የደከሙ፣ እንዲሁም በረሃብ የታመሙ ከስፈራ ጣቢያ ያመለጡ ሰዎች ነበሩ። በጠረፉ ላይ ባረፉ ጊዜ፣ እንደ ገና እንድ ጊዜ ሲያርፉበት እንዲሁም ምግብ እና ውኃ ሲያገኙ ወደሚችሉበት በምዕራፍ አቅጣጫ ወዳለው ወደ ካምፑ ለመሄድ ደስተኞች ነበሩ። ነገር ግን ተስፋዬ ከእነርሱ ጋር አልተቀላቀለም፣ ምክንያቱም ምንም እንኳ ወደ መጠለያ የሚወስደው መንገድ እጅግ ሩቅ እና መንገዱ በከፊል በምድረ - በዳ ውስጥ የሚያልፍ ቢሆንም፣ የራሱ የሆነ ውስጣዊ ስሜት ወደ ለሜን ይስበው የነበረ ይመስላል። እርሱ እመነታ፣ በጀርባው ጋደም አለ፣ ደግሞም ወደ ለሜን በሚመራው በኮረኮንቹ መንገድ አጠገብ ባለው የናፍጣ ማደያ ለማረፍ ቁጭ አለ።

ከዚያም ደግሞ ይህ ተከሰተ፤ ወደ ደቡብ ዕቃ ጭኖ የነበረ እና ባዶውን በመመለስ ላይ የነበረ ከባድ መኪና በመጥፎ ዕድል እየተንገጫገጨ መሄድ አልቻለም፤ ደግሞም አንድ ነጭ ሰው ከውስጥ ወጣ፤ ቢያንስ ቢያንስ እርሱ ነጭ መሆን ይጠበቅበታል፣ ነገር ግን ፊቱ እና ወርቃማ ጠጉሩ በአቧራ ተሸፍነዋል፣ እንዲሁም ዓይኖቹ ደም መስለው ነበር። በቀስታ ለራሱ እየተራገመ፣ የፊት ከ ፈኑን ከፈተ እና ወደ ውስጥ አተኩሮ ተመለከተ። ከዚያም ቀና



ብሎ እጆቹን ጭንቅላቱ ላይ አደረገ። እርሱ እና ከባድ መኪናው፣ ሁለቱም በግልጽ በመጥፎ ሁኔታ ላይ ነበሩ።

«ሜካኒክ ይኖራል?» ሲል ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ በናፍጣ ማደያው የተኛውን ግለሰብ ጠየቀ።

በዚያ የተገኘው ሰው ራሱን ነቀነቀ፣ እንዲሁም ከትንሽ ልጅ ብዙም የማይበልጠው ነጩ ሰውዬ በድጋሚ ተራገመ። ከከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ መካኒክ የሆነው ተስፋዬ ወደፊት ቀረበ። «እኔ ሜካኒክ ነኝ፣» አለ በዝግታ። «ልረዳህ እችላለሁ?»

«በርግጥም ልትረዳኝ ትችላለህ!» ሲል ልጁ በጩኸት ተናገረ። «እዚህ ጋ ተመልከት እና ችግሩን እግኝ። መፍቻዎቹ ከመቀመጫው ሥር ናቸው። እኔ ብጥብጥ ብያለሁ። የምጠጣው ለማግኘት እና ለማረፍ ወደ ውስጥ መግባቴ ነው።» ወደ ውስጥ ዘለቀ፣ ወዲያውም በጣም ታመመ።

ተስፋዬ ስለ ከባድ መኪናዎች ብዙ ያውቃል። ከዋናው ከተማ የምግብ አቅርቦት የሚያደርጉ ከባድ መኪናዎችን ይነዳ ነበር፤ ደግሞም የሞተር ሜካኒክ ሆኖ ለዓመታት ሠርቷል። ዙሪያውን ሲመረምር እና የችግሩን መንስኤ ሲጠቁሙ ጣቶቹ ወደ ሕያውነት መመለሳቸው ተስማምቶታል። ትንሽ ችግር ነበረች፣ ደግሞም ተ ስፋዬ ወዲያው አስተካከላት። ወደ ውስጥ በገባ ጊዜ፣ ልጁ ራሱን በክንዶቹ ላይ አድርጎ ተቀምጦ ሁለት ባዶ የኮካ ኮላ ጠርሙሶች በአጠገቡ ተቀምጠው ሳለ ተኝቶ ነበር። ተስፋዬም እንደዚሁ ተ ቀመጠ እና ኮካ ኮላ ለመግዛት ብችል ሲል ተመኘ። ልጁን አልቀሰቀሰውም፤ ያም ሆነ ይህ፣ የሚያስቸኩል ነገር አልነበረም።

በናፍጣ አዳዩ እና በአንድ መንገደኛ መካከል የተፈጠረና ሌሲቱን ሙሉ የነበረ ነገር ግን፣ ወደ አደባባይ ያልወጣ ጠብ ሊኖር ይችላል። ጮኸ ያለው ክርክር ልጁን ቀሰቀሰው። ዓይኖቹ በተስፋዬ ላይ እስኪያተኩሩ ድረስ፣ ዓይኖቹን አንሥቶ ዙሪያውን ትኩር ብሎ ተመለከተ።

«የት ነው ያለነው?» ሲል ጠየቀ።

ልጁ የታመመ ይመስላል፣ ተስፋዬ ሊያጽናናው ሞከረ።

«ከባድ መኪናህ አሁን በመልካም ሁኔታ ላይ ነው፣» አለ ረጋ ብሎ፣ «ነገር ግን ቀኑ አሁንም ሞቃታማ ነው:: የበለጠ ዕረፍ:: በኋላ ትጓዛለህ::»

ልጁ በመገረም ትኩር ብሎ ተመለከተው::

«ያንን ማድረግ አልችልም፣» አለ:: ነገ ማምሻው ላይ እዚያ መድረስ አለብኝ:: ነገር ግን ሕመም ይሰማኛል:: ፀሐይዋ ስለ መታችኝ ሊሆን ይችላል፣ ደግሞም በመንገድ እየሄድሁ እንዳልተኛ እፈራለሁ:: ወደ ሁለተኛው ሾፌር ወጣሁ:: ነገር ግን ወዲያውኑ ወደ ቤቱ ለመሄድ ወደ ራሱ ወሰደው:: መልካም፣ እኔ ኃላፊነቱን ብወስድ ይሻላል:: ሌላ ተጨማሪ ኮካ ኮላ ይኖረኛል፣ ከዚያም እንሄዳለን:: አንዷን ኮካ ኮላ ያዝና ከእኔ ጋር ጠጣ፣ ከዚያም መኪናውን ለመንዳት ትሞክራለህ::»

አሁን በደንብ እየነቃ ነው፣ እየጠጡ ሳሉ፣ ከአጠገቡ ያለውን እንደ አገዳ የቀጨጨውን ለውዬ፣ ደግሞምም ረጋ ባለ ድርዝ ያለው አነጋገር የሚናገረውን ልክ እንደ ጥቁር የኀዘን ገንዳዎች የሚመስሉትን ዓይኖች ያሉትን ሰው በማስላሰል ተመለከተው::

«ስምህ ማን ነው?» ሲል ጠየቀው

«ተስፋዬ፣ ያንተስ?»

«እ፣ እኔ ቻርሊ እባላለሁ:: ከባድ መኪናውን እንቃኘው::» ብድግ አለ፣ ነገር ግን ክፍሉ በዙሪያው የሚዋኝ መሰለ:: እና እንደገና ወዲያው ቁጭ አለ:: «እንዴት እንደምችለው አላውቅም፣» አለ በምሬት:: «ተስፋዬ፣ ስማ፣ በተገኘ አጋጣሚ አትነዳም አይደል? ትነዳለህ?»

ተስፋዬ ፈገግ አለ:: «ከባድ መኪናዎችን ዘወትር እነዳለሁ:: እኔ እነዳለሁ፣ አንተ ተኛ::»

ቻርሊ በጥርጣሬ ተመለከተ:: «የመንጃ ፈቃድ የለህም ብዬ እገምታለሁ?»

«የለም፣ መንጃ ፈቃድ የለኝም:: እኔ ስደተኛ ነኝ:: ነገር ግን በጥሩ ሁኔታ እነዳለሁ::»

«መልካም፣ በጥሩ ሁኔታ ብትነዳ ይሻላል:: እስቲ እንዴት



እንደምትነዳ እንይህ::»

ተስፋዬ ወደ ሹፌሩ መቀመጫ ወጣ:: በመጀመሪያ ማርሾቹን እየለዋወጠ ለመንዳት እንደሚቸገር አስቦ ነበር፤ ነገር ግን ሞተሩ እንደ ተነሣ፣ ካልታወቀ ምንጭ ከውስጡ የሚወጣ ጥንካሬ ያገኘ መሰለ:: ምናልባት ቀምሶት ከማያውቀው ነገር ሁሉ የተሻለ ከሆነው ከኮካ ኮላው የመጣ ሳይሆን አይቀርም ሲል አሰበ:: ቻርሊ፣ አፉን ከፍቶ ይመለከተዋል::

«ግሩም ነው!» ብሎ ጮኸ:: «መንዳትህን ቀጥል:: መንገዱ ቀና ነው:: ምንም ጠመዝማዛ የለበትም:: እኔም እተኛለሁ:: ተስፋዬ አንተን ስላገኘሁህ እግዚአብሔር ይመስገን::»

ዓይኖቹን ጨፈነ:: «ተመስገን አምላኬ!» አለ ልጁ:: ተስፋዬ እግዚአብሔር መልካም እና ሊመስገን እንዲሁም ሊወደስ የሚገባው መሆኑን ረስቶታል:: ይህ ልጅ አስታወሰው:: እርሱ እግዚአብሔርን በማስታወሱ ሃይማኖተኛ ልጅ መሆኑ አያጠራጥርም:: በብዙ ሳምንታት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ተስፋዬ የምስጋና ጸሎትን በማጉተምተም አቀረበ:: እግዚአብሔር ረድቶታል:: ተስፋዬ ወደ ስሜን እየተጓዘ ነበር::

እስከ ከሰዓት በኋላ ረፋዱ ላይ፣ እንዲሁም ቀዝቃዛው ምሽት እስኪመጣ ለጥቂት ሰዓታት በሞቃታማው ጊዜ ነዳ:: በትናንሽ አቧራማ መንደሮች በኩል አለፉ፣ ደግሞም ወንዙ ከቶ ሩቅ አልነበረም:: በስተግራው፣ ፀሐይ እያቈለቈለች ሄደች፤ ሰማዩም ብርቱካናማና ደማቅ ቀይ፣ እንዲሁም ሐምራዊ ቀለሞችን በአስገራሚ የምሽት ትዕይንት ውስጥ አንጸባርቋል፣ ቻርሊ ግን አሁንም እንዳንቀላፋ ነበር:: በቀጣዩ ትንሽ መንደር፣ ተስፋዬ መኪናውን አቆመና ቀለቀለው::

«ምን ተፈጠረ? እንቀጥል እንጂ፣» ሲል አጕረመረመ ልጁ:: በመቀጠል፣ «ደኅና እየነዳህ እኮ ነው፣» አለ::

«መቀጠል አልችልም፣» ሲል ተስፋዬ ረጋ ብሎ ተናገረ:: «ለ ረጅም ጊዜ ምግብ አልቀመስሁም:: እኔም ሰው ነኝ፣ ደክሞኛልና መተኛት ይኖርብኛል::»

ቻርሊ ነቃና ብድግ ብሎ ተነሣ:: ቀዝቀዝ ያለችው ምሽት ፈውስ

ነበረች፤ እርሱም እጅግ የተሻለ ስሜት ተሰማው:: «አ፣ በጣም አዝናለሁ:: የምትበላው እንዳልነበረህ ከቶ አልተከሰተልኝም:: ሳንድዊቹን ብላ፣ ደግሞ ጥቂት ተጨማሪ ኮካ ኮላ እዚህ ማግኘት እንችላለን:: አንድ ጠርሙስ ኮካ ኮላ አመጣልሃለሁ፤ ደግሞም ተመልከት፣ እዚያ የተቀቀለ እንቁላል እየሸጡ ነው:: አንድ ይምጣልህ?»

የቻርሊ አሳቢነት ማለፊያ ነበረ፤ ደግሞም ከፌስታል አውጥቶ ተስፋዬን ከዚህ ቀደም ከቶ አይቶት በማያውቅ ደግሞም አልፈጭ ይል እንደ ሆን ብሎ በስጋበት በአውሮፓውያን ምግብ አንበሸበሸው:: በመጨረሻም፣ ከከባድ መኪናው ወጡና ከግርዶሽ ሥር ተቀመጡ እና ተስፋዬ ትኩስ ዳቦና አንድ የተቀቀለ እንቁላል በላ፣ ኮካ ኮላም ጠጣ:: በከፊል በምግቡ አማካይነት፣ በከፊል ደግሞ ከልጁ ጋር በነበረው ጓደኝነት እና ግልጽ አድናቆት፣ የበለጠ ሕያው እየሆነ መምጣቱ ተሰማው::

«አንተ ታላቅ ሰው ነህ፣» አለ ቻርሊ በስሜት ተውጦ፣ ካርታ እያሳየው:: «ደግሞም አሁን ጥሩ ስሜት ይሰማኛል:: መኪናውን የመንዳቱን ሚና ለአፍታ እወስደዋለሁ፣ አንተም ከኋላው ላይ ጋደም ማለትና መተኛት ትችላለህ:: በኋላም፣ አንደገና እንቀያየራለን:: ተስፋዬ፣ ያለ አንተ ምን ማድረግ እንደምችል አላውቅም:: ካጋጠሙኝ ነገሮች ሁሉ አንተ ምርጡ ነህ::

«ይህን ያደረገው እግዚአብሔር ነው. . . እግዚአብሔር ይመስገን፣» አለ ተስፋዬ በአክብሮት፣ ጥልቀት ያለው ሰማያዊ ምሽትን አትኩሮ እየተመለከተ:: ከከባድ መኪና ኋላ በተከመሩት ጆንያዎች ላይ ጋደም አለ:: ትንሽ የምሽት ነፋስ በፊቱ ላይ ነፈሰበት:: ጨረቃም ነጭ በሆነው አሸዋማ መሬት ላይ እያበራች ወጣች:: ደስ በማይል ቅጽበት ሙናን የቀበረበትን ጊዜ በቍጥቋጦው ውስጥ ያለውን ቁልል አስታወሰ፣ ነገር ግን በቈራጥነት ከመመልከት አእምሮውን ከእርሱ ገለል አደረገ:: አሁን እርሱ ማየት ያለበት ወደፊት ነው:: ቻርሊ ደግ ነበር፤ እግዚአብሔር መልካም ነበር:: የመኪናው ጐማዎች ወደ ሰሜን አቅጣጫ እየተንገጫገጩ እየሄዱ ሳለ እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰደው::



# 12

ተክሊ አልሞተም:: ሽፍታው ረግፎለታል፣ ደግሞም ቀጭን እና እንደ ጥላ ደካማ አድርጎት፣ ትኩሳቱ ቀንሶለታል፤ ነገር ግን ወደ ጤንነት እና ጥንካሬ ረጅሙን መሰላል ለመውጣት ዝግጁ ነበር:: ነገር ግን የደከመ ሆኖም ለ75,000 ረሃብተኞች ምግብ ለመስጠት የተሰጡ ከሆኑት ቡድኖች ከሚሰጠው ከተጨማሪው ምግብ እና እንክብካቤ ባሻገር፣ ካምፑ ያንን መሰላል ለመውጣት የሚመች ስፍራ አልነበረም:: ሙቀቱ እየጨመረ ነበር፣ ደግሞም የውኃ አቅርቦቱ እያሽቈለቈለ ነበር:: በወንዙ ውኃ መውረጃ የነበሩት ገንዳዎች እየደረቁ ነበር፣ ደግሞም በወንዙ ዳርቻ የነበሩት አረንጓዴ ተክሎች ጠውልገዋል:: ብዙዎቹ ደቃቃ መጠለያዎች ወድቀውፀተ ሰባብረዋል፣ ደግሞም እነርሱን ለመመለስ የሚያስችሉ የቀሩ ነገሮች አልነበሩም::

ከዚያም ዜናው ወዲያው ተሰራጨ፤ በሰሜን ሌላ ካምፕ ከፍቶው ነበር፣ ደግሞም ብዙዎች ይሄዱ ይሆናል:: አንዳንዶች ደስ ተሰኝተዋል፣ ሌሎች ደግሞ አዝነዋል፣ ነገር ግን የሚሆነውን ነገር ለመገመት የነበረው ጊዜ ትንሽ ነበር:: በዚያው የከሰዓት በኋላ ወቅት ከወንዙ ውኃ መውረጃ በስተምዕራብ ክፍት የሆኑ 40 የጭነት መኪናዎች ቆመው ነበር፣ ደግሞም 1600 ብዛት ያላቸው ቤተሰቦች ንብረታቸውን ሁሉ እንዲጠቀልሉና ፀሐይ ስትጠልቅ ለሚኖረው ጉዞ እንዲያዘጋጁ ተነግሮአቸው ነበር::

በሺህዎች የሚቈጠሩ ሰዎች ደኅና ሁኑ ብለው እጆቻቸውን ለማውለብለብ እና ወደ መኪና ሲወጡ ለመመልከት ተሰብስበዋል:: ሕፃናት ልጆቻቸውን በእጆቻቸው ጨብጠው ይዘው፣ የአልባሳት ጥቅልሎቻቸውን (ሸክሞቻቸውን)፣ የፕላስቲክ ጠርሙሶቻቸውን እንዲሁም የማብሰያ ዕቃዎቻቸውን አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ ቆለሉት::

ነገር ግን፣ ልጆቹ ደስ ተሰኝተዋል፤ ምክንያቱም በምሽቱ በሰሜን በኩል መንዝ ለእነርሱ እንደ ጆብዱ የሚወሰድ ነበር፣ ደግሞም ሁልጊዜ «እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል::» ከባድ መኪናዎች እየተሽከረከሩ ወደ ጨለማው በሚገቡበት ጊዜ እየጮኹ ያደሰቱ ነበር፣ ደግሞም በወንዙ ዳርቻ ላይ ተሰብስበው የነበሩት ሕዝቦች እየተደነቁ ተመልሰው ወደ መጠለያቸው ሄዱ::

ከሞላ ጎደል በእያንዳንዱ ቀን ማለት ይቻላል ከባድ መኪናዎቹ ይደርሳሉ፣ ደግሞም እነዚያ የተመረጡት ወገኖች ይጫኑና ያለ ተቃውሞ ይሄዳሉ:: ምሕረት ከሌሎች ሰዎች ጋር ቆየች፣ ምክንያቱም መቆየት የሕይወት ዘይቤ ሆኖአልና፤ ደግሞም አንድ ጊዜ ውኃ ከቀዳችና እንጀራ ከጋገረች በኋላ፣ የምትሠራው ምንም ነገር የለም:: የሚተጣጠፍ ሰውነት ያለውን ትንሹን ተክሌ እየመገበች ወይም እያጫወተች በጥላው ሥር ቁጭ ብላለች፣ የምሽቱንም ቅዝቃዜ በተስፋ ትጠባበቃለች:: በሙቀቱ ደክመው፣ በጊዜ ተኙ፣ ደግሞም ፀሐይዋ እንድትወጣ በጉጉት እየጠበቁ ማለዳ ተነሡ:: የመጀመሪያዎቹ ተጓዦች ከመልቀቃቸው በፊት እንደ ኃላፊ ሆኖ እንዲሠራ ወደ አዲሱ ካምፕ ስለ ሄደ፣ አጐትዋ ገብሬ እንኳ ከዚህ በኋላ አልጐበኛቸውም::

ከዚያም በአንድ ማለዳ ላይ ተራቸው ደረሰ:: ምሕረት እና ተክሌ ደግሞም በመጠለያዎቻቸው ተጠልለው የነበሩ ሰዎች ሁሉ ፀሐይዋ በምትጠልቅበት ጊዜ ስፍራውን ለመልቀቅ ዝግጁ እንዲሆኑ ተነገራቸው:: በአጠቃላይ፣ ደስተኛ ነበረች:: ለብቻቸው አይጓዙም:: ካህኑ እና ባለቤታቸው እንዲሁም የኪሮስ ወላጆች ከእነርሱ ጋር የሚሄዱ ይሆናሉ፣ ምናልባትም ደግሞ በአዲሱ ካምፕ ከእነርሱ ጋር ይቀመጡ ይሆናል፣ ተክሌን ከዛፍ ሥር ተወችውና የማሽላ እና የባቄላ እንዲሁም የዘይት ቀለብዋን ለመቀበል ሄደች:: ከዚያም ልብሳቸውንና ምግባቸውን ቋጠረች፣ ደግሞም ጉዞው የሚፈጸምበትን ጊዜ ለመጠበቅ በድጋሚ ቁጭ አለች:: ከሰዓት በኋላውን በመተኛት አሳለፉ፣ እንዲሁም የዛፎቹ ጥላዎች እየረዘሙ በሄዱ ጊዜ፣ ሸክሙን፣ የፍየል ቆዳውን፣ ማብሰያ ዕቃዎችንና ቁሳቁሶችን ሁሉ እስራ በጀርባዋ ላይ አደረገች፤ ተክሌን



በእጅዋ ይዛ ሁሉም በአንድነት ተጓዙ፤ አሮጊትዋ የካህኑ ሚስት ትንሽ አለቀሱ፣ ምክንያቱም የጉዞአቸው መጨረሻ ላይ ደርሰው በጸጥታ በጥላው ሥር ሞትን ዝግጁ ሆነው መጠበቅ እንጂ፣ እንዲረበሹ ፍላጎት አልነበራቸውም::

ከባድ መኪናዎቹ እየጠበቁ ቆመዋል፣ ደግሞም እነርሱ ወጥተው ሕፃናትን ወደ-መኪናዎቹ እያወጡ እና ሻማግሌዎችን እየረዱ ነበር:: በአንድ ተሽከርካሪ ላይ የተሳፈሩት 40 ሰዎች ነበሩ፤ ለመተኛት ስፍራ አልነበረም፤ ነገር ግን ብዙዎቹ መቀመጥ ይችሉ ነበር፣ በዚህም የሚያጉረመርም ሰው አልነበረም:: ልጆቹ በድጋሚ ይሳሳቁ እና እጃቸውን ያውለበልቡ ነበር፣ ነገር ግን ትላልቅ ሰዎች ፊቶቻቸው የዕድል ንፋስ ወደሚነፍስበት ለመሄድ ፍዝዝ ባለ ሁሉን ተቀባይነት በሚታይበት በዕድሜ-ጠገብ የለደተኝነት ትዕግሥት ታትሟል::

ማርሾቹ ሲለዋወጡ እና የጭነት መኪናዎቹ አንዱ ከሌላው ኋላ ሆነው ወደ መንገዱ ሲወጡ፣ ከሞላ ጎደል መሽቶ ነበር:: የመጨረሻውን ስንብት ለማድረግ (ደኅና ሁኑ ለማለት) እጅን ለማውለብለብ እና ከዚያም በምዕራብ እየጨለመ ባለው ሰማይ ላይ ወዳሉት ብሩህ ቀይ ምልክቶች ለመሄድ ትላልቅ ወንዶች እና ልጆች ወደ ፓራውልቱ ተሰብስበዋል:: እያንዳንዱ ሰው ጸጥታ ይሰማዋል፣ ምክንያቱም የጉማዎቹ መንኰሻኰሽ እንዲሁም ኮረኮንች በሆኑ የበረሃ መንገዶች ላይ የሚደረገው መንገጫገጭ መነጋገርን የማይቻል አድርገውታል::

ልጆቹ ወዲያው እንቅልፍ ወሰዳቸው፣ ደግሞም ቀሪዎቹ እርስ በርሳቸው ተቀራረቡ፣ እንደሚገባቸውም አንቀላፉ:: መርገፍገፍ የነበረባቸው ድምፅ የበዛባቸው ሰዓታት በሆነ መልኩ አልፈዋል፣ ደግሞም ጠዋት በሦስት ሰዓት አካባቢ ተጓዦቹ ረጅም በሆነ ጥላ ተሸፈኑ:: ተጓዦቹ ምግብ እና ውኃ ተሰጣቸው፣ ደግሞም የተጣጠፉ እግሮቻቸውን እንዲያፍታቱ እና እንዲዘረጉ ተፈቀደላቸው:: አሁን ብሩህ የሆነ የጨረቃ ብርሃን ወጥቶአል፣ እየሩ ንጹሕ ነበር፣ ደግሞም ኃላፊዎቹ ደጎች ነበሩ:: «ሌሎች ሁለት ሰዓታት ብቻ ነው የሚቀሯችሁ፣» አሉ፣ «ከዚያም እካምፑ ትደርሳላችሁ::»

ከባድ መኪናዎቹ ወደ ሰሜን ምሥራቅ ዞሩ፤ የደከሙት ተጓዦች ደግሞ እድገታቸው በተገታ ቍጥቋጦዎች ወይም በግመል ወይም ላም ጥንብ ከመቋረጡ በቀር በስፋት የተዘረጋ ምድር በዙሪያቸው በከበባቸው ስፊ በረሃ ላይ ስረቅ የሚያደርገው ማለዳውን ተመለከቱ:: እዚህ ጥላማ የሆኑ ዛፎች የሉም፣ ደግሞም መንገዱ እንኳ ለበረሃው ቅድሚያ ሰጥቶታል:: ነገር ግን የያዛቸው ፍርሃት ዛፎች በመስመር የተደረደሩበትን አካባቢ ሲያዩ ቀነሰ:: ብዙዎች ተነሥተው በፓራውልቱ ላይ ዘመም በማለት ለማየት ቆሙ፣ በመሬቱ ላይ አረንጓዴ ጭጋግ ነበርና:: እጅብ ያሉ የትናንሽ አትክልት ቦታዎች እንዲሁም በምንጮቹ መካከል በጎች እና ፍየሎች የሚግጡበት ዝቅ ያለ ሣር ያለበት ሰፍራዎችም ነበሩ:: ከዚያም ታላቁን ግድብ እና የሚያንጸባርቀውን ማጠራቀሚያ ተመለከቱ፣ እንዲሁም እንዳንዶች ስልቻቸውን ገለጡ፣ ምክንያቱም እዚህ በእርግጠኝነት፣ በዚህ ዕድለኛ የሆነ ቦታ፣ ውኃ አልተቋረጠም ነበርና::

ትልቁን ግድብ ተሻገሩ፣ ደግሞም ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ በበረሃው አቋርጠው ተጓዙ:: አሁን ከባድ መኪናዎቹ በፍጥነት እየተጓዙ ነበር፣ ደግሞ ከሞላ ጐደል ሁሉም ዓይኖቻቸውን ከልለው፣ ሕይወት ሰጪ የሆነውን የነፋስ ሽውታን እያጣጣሙ ቆመው ነበር:: ካምፑ ከፊታቸው በሚታየው ከፍ ባለ አድማስ ላይ ያለ ይመስላል፤ እንዲሁም በመካከላቸው ባሉ በተርታ የተደረደሩ መጠለያዎቹ- በቋሚ ብረቶች ላይ በተዘረጉ ምንጣፎች ላይ ስፍር ቍጥር የሌላቸው ሰዎች ነበሩ:: ከባድ መኪናዎቹ ኩርባውን በፍጥነት ታጠፉ፣ ያም አንዳቸውን ወደ ሌላው ከንዶች ወሰዳቸው፤ ከዚያም በመጠለያዎቹ ፊት ለፊት በነበሩበት ሁኔታ መለሳቸው:: እነርሱ ይጓዙበት ወደ ነበረበት ስፍራ ደርሰዋል::

ሰዎች ወደ እነርሱ ይሮጡ ነበር:- የገዛ ራሳቸው ሕዝቦች ንጹሕ የሆነ ነጭ ሸሚዝ ለብሰው፣ ደግሞም ባዕድ የሆኑ ሴቶች ከጥጥ የተሠሩ በእዘቦት የሚለበስ ሱሪ እና ሸሚዝ ለብሰው በዚያ አሉ፤ ለሕሙማን እና በዕድሜ ለገፉ ወይም ፈጣን እንክብካቤ ለሚያስፈልጋቸው ለየትኞቹም ሰዎች ዕርዳታ ለመስጠት ከባድ



መኪናዎቹን እያዩ እንደ ነበረ ምሕረት ተገነዘበች:: በመንገዱ ላይ እንደዚህ ያለ ብዙ ቍጥር ያለው ሕዝብ መልምሎ ለማውጣት ሁልጊዜ የማይቻል መሆኑን አታውቅም ነበር፣ ደግሞም አንዳንድ ጊዜ በፍጥነት የሚከናወኑ ድርጊቶች ሰቆቃን ለመቀልበስ ይችላሉ:: አንዳንድ ጊዜ ያዘገይ ነበር፤ በጭነት መኪናው ላይ በአንድ ምሽት ሕፃን ተወለደ፣ ደግሞም እናቲቱ ሞተች፤ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ቤተሰቦችዋ ቀረቡና በሞቱ ስውነትዋ ላይ ተጠመጠሙ:: እያዘገሙ መሄድን እና ገፍተው መግባትን ለመቋቋም የማይችሉ ደግሞም በአስቸኳይ እንክብካቤ ሊደረግላቸው የሚገቡ የደከሙ ልጆች ነበሩ:: ቀሪዎች ከጭነት መኪናው ላይ ወረዱ፣ ደግሞ በዚያ ለመቆየት ወደ ሚሰፍሩበት መጠለያ ተወሰዱ:: ነገር ግን፣ ልጆቹ፣ መልካምነትን እየተመለከቱ፣ በሚስተናገዱበት ስፍራ በደርዘን የቆሙ ሰዎችን እጆች ለመጨበጥ እና ለመነቅነቅ እየሮጡ ሄዱ፣ ዓይኖቻቸው ቀጭን፣ ብሩህ በሆኑ ፊቶቻቸው ውስጥ ያበሩ ነበር::

በመጠለያዎቹ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ቆዩ:: አንድ ኩባያ ወተት እና ብስኩቶች ታደሉ፣ ደግሞም እንዲመዘገቡና ምርመራ እንዲደረግላቸው በቤተሰብ ደረጃ ተጠሩ:: ነጮቹ ሴቶች ስማቸውን ለማንበብ (ለመጥራት) ያልቻሉ ወይም የሚሉትን ነገር ለመረዳት የማይችሉ መሰሉ፣ ነገር ግን ለማስተርጐም የራሳቸው የሆኑ ብዙ ሰዎች በዚያ ነበሩ:: አዝጋሚዎቹ ረጃጅም ሰዓቶች አለፉ፣ ወረፋው በጣም እየበዛ ሄደ፣ ደግሞም በድንኳኑ ውስጥ የነበረው የሙቀት መለኪያ 120 ዲግሪ ሙቀት ያሳይ ነበር፣ ነገር ግን ማንም ያለመታገሥን ወይም የመቁጥቁጥን ስሜት አላሳየም ነበር:: መቈየትን ተምረው ነበር:: መቆየት የሕይወት ዘይቤአቸው ነበር::

ተክሌ ክብደቱን ተመዝኖአል፣ ነገር ግን በዚህ ጊዜ አሻፈረኝ ለማለት እጅግ ደክሞት ስለ ነበር፣ በመንጠቆው ላይ ዝም ብሎ ተንጠለጠለ:: ጉዳዩን እየተከታተለች ያለች ሴት ቀይ ብሩህ ቀለም ያለውን ሰነድ ተመለከተች፣ ራሷን ነቀነቀች እና ወደ መመገቢያው ጣቢያ መወሰድ ይኖርበታል አለች:: ምሕረት እነሣችው ደግሞም በተጠቀለሉ ሸክሞች ላይ እየዘለለች፣ ጨለምለም ወዳለ በግድግዳው ዙሪያ ምንጣፍ ወደ ተነጠፈ

ደግሞም የሣር ክዳን ያለውን ጣራ ትናንሽ የፀሐይ ብርሃን ዘልቀው የገቡበት እና ከበታቹ ቁጭ ያሉትን ቡድኖች ወዳዥጉረጉረው ሌላ መጠለያ እስኪደርሱ ድረስ በልጆቹ በላይ አልፋ እየተራመደች በሆነ መልኩ ወደ ፊት አመራች:: ሁሉም ነገር ከዚህ ቀደም እንደ ነበረው ነበር፤ ሕሙማን እናቶች፣ የተራቡ ትናንሽ ልጆች፣ ደስ የሚሉ ብሩህ ኩባያዎች፣ እንዲሁም በስታቴው ድስት ዙሪያ ያሉ ቡድኖች ሁሉ እንደ ነበሩ ናቸው:: አንድ ለየት ያለ ነገር ብቻ ነበር፣ ባዕድ የሆነች ሴት በክንዶችዋ ውስጥ ሕፃን ልጅ ይዛ ተቀምጣ ነበር፣ ደግሞም ከቡናማዎቹ ጨርቆች እና ቀለማቸው ከደበዘዘው ብርድ ልብሶች መካከል በእነዚያ የማይጥሙ፣ ቀሰም-አልባ አካባቢዎች የሚገርም በቀለም ላይ የሚደረግ ትኩረት ነበር:: ምሕረት ተክሌ ገንፎ በልቶ ለመተኛት ጋደም ባለ ጊዜ እጅግ ተገርማ ትመለከተው ነበር::

«ልክ እንደዚያ አድርገው የሚያለብሱት እርሱ ሀብታም የሆነ ታዋቂ ሰው ልጅ ነውን?» ስትል በቅርባቸው ሆኖ አንድ ሕፃንን ቱቦ በአፍንጫው ሰክቶ እየመገበ ያለ ኃላፊን ጠየቀችው::

እርሱም ፈገግ አለ:: «አ፣ እንደ እርሱ አይደለም፣» ሲል መለሰ:: «ዛሬ ማለዳ በጭነት መኪና እዚህ የደረሰ ሕፃን ልጅ ነው:: ተመልከቺ፣ እናቱ በቅርቡ ተቀምጣለች:: እንዲሞቀው ኤማ በዚህ መልኩ አለበሰችው፣ ምክንያቱም የቀዘቀዘ እና እየሞተ ያለ ነው:: እርሱ በፈሳሽ ምግብ መመገቢያ በቱቦ እየመገበችው ነው::: ለመዋጥም እጅግ የደከመ ነው::»

ለጥቂት ጊዜ ተቀመጡ:: እንቅልፍ ከወሰዳቸው ልጆች አጠገብ ሽክሞቻቸውን በራሳቸው ሥር ተንተርሰው እናቶች አንቀላፉ:: ከሁለት ሰዓታት በኋላ እንደገና ልጆቻቸውን ይመግባሉ፣ ከዚያም ወደ ድንኳኖቻቸው ይሄዱ ነበር:: ምሕረት አንቀላፋች፣ ከዚያም ብሩህ በሆነው ትንሽ ፍጡር እና አጠገቡ ተቀምጣ እያባበለችው በጠብታ እየመገበችው ባለች ነርስ ላይ አትኩራ ተመለከተች::

ወዲያውም አንድ ነገር ተከሰተ:: ሕፃኑ ትንሽ ስቅታን ሰጠ:: ነርሷ በአጠገቧ ተኝታ ያለች ሴትን በመጨነቅ ገርመም አድርጋ ተ



መለከተቻት:: ሌላ እንግዳ ነርስ መጣችና ሁለቱም ደርቀው የቀሩ ይመስል ወደ ታች አተኩረው ማየትን ቀጠሉ:: ማንኛቸውም የሚናገሩም ሆነ የሚተነፍሱ አይመስሉም ነበር:: በእርሱ ላይ በአንድነት ዘመም ብለው በዝግታ ይናገሩ ነበር:: ከዚያም ሁለተኛዋ ነርስ ከሕፃኑ አፍንጫ ውስጥ ቱቦውን ሰባ አወጣችው፤ የሚያምር ልብሱንም ካወለቀች በኋላ ለስለስ ባለ ሁኔታ ማልቀስ ለጀመረችው ለእናቱ ሰጠቻት:: ወጣትዋ ነርስ፣ እንባዋ በጉንጮችዋ ላይ እየፈሰሰ፣ በፍጥነት ተመልሳ ሄደች::

«ነገር ግን ለምንድን ነው እንደዚያ የምታለቅሰው?» ስትል ምሕረት ጠየቀች፣ በመገረም:: «በእርግጠኝነት የገዛ ራስዋ ልጅ መሆን አለበት» አለች::

ወተት የሚያድለው ኀላፊው ለውዬ አሻግሮ ቃኘት አደረገ::

«አይደለም፣» ሲል መለሰ፣ «እኔ እንደ ነገርኩህ ነው::» በከባድ መኪና መጥቶ ዛሬ ማለዳ እዚህ የደረሰ ልጅ ነው:: አሁን በዚህ ጊዜ ሞተ::»

# 13

ተስፋዬ በጥሩ ሁኔታ ተኝቶ ነበር፣ ደግሞም የነቃው ከባድ መኪናው ድምፅ በሞላበት ትንሽ ገበያ በቆመ እንዲሁም ቻርሊ ከበስተኋላው ራሱን ባከከ ጊዜ ብቻ ነበር:: «ትንሽ ቊርስ ብንበላስ?» አለ:: «ጥሩ ስሜት ይሰማ ` መሪውን መውሰድ ከቻልህ፣ አሁን እኔ እተኛለሁ::»

ጊዜው ገና ማለዳ ነበረና በትንሽ ካፍቴሪያ ውስጥ የለማያዊ ጢስ ሽታ ባለበት እና ጥብስ በሚጠበስበት ዙሪያ ተቀምጠዋል:: ተ ስፋዬ ግልጽ ባልሆነ መልኩ ታምሞአል:: ቻርሊ ቡናና ደረቅ ነገር እየወለደ ሳለ፣ አንድ ጉድጓዳ ሳህን መረቅ ጠጣ፣ ደግሞም ብርቱካን በላ:: የቻርሊ ዓይኖች ቀልተው ነበር፣ ደግሞም ማዛጋቱን ቀጠለ:: የመጨረሻውን ጉርሻ ጉርሶ እንደ ጨረሰ እንቅልፍ ጣለው፣ ደግሞም ተስፋዬ በቀስታ ቀሰቀሰው:: «አንተ ተኛ፣ እኔ እሾፍራለሁ፣» አለ:: «በስተኋላ ጋደም ብለህ ተኛ::»

ቻርሊ ነቃ አለና፣ «አንተ ደኅና ባልሆንክበት ሁኔታ አላደርገውም:: እንደ እኔ ከሆነ፣ አንተ ተለማማጅ ነህ! የመንጃ ፈቃድ እስካገኝልህ ድረስ በአጠገብህ እቀመጣለሁ:: እንሂድ፣» አለው::

በአረንጓዴ እና በመከር ቡቃያ መሸፈን በነበረበት ፈዛዛ ቢጫማ ቡኒ ቀለም ባለው የመሬት አቀማመጥ ላይ ለአምስት ሰዓታት ያህል አሽከረከሩ:: ተስፋዬ በዚያ ሙቀት ውስጥ በጣም ጉልህ እና አንጸባራቂ እየሆነ ሊነሣ እና ሊመታው በሚመስል መንገድ ላይ መጓዙን እየቀጠለ በሄደበት ጊዜ፣ ቻርሊ የመቀመጫውን ጀርባ ተ ደግፎ ተኝቶአል፣ ደግሞም ጮኽ ብሎ ያንኰራፋል:: አንዳንድ ጊዜ ሊቀርባቸው የሚጠፉ እንግዳ የሆኑ የዛፎች ማጥበርበር እና ውኃ ተመልክቷል፣ ደግሞም ትኩሳቱ ተመልሶበታል፣ ምክንያቱም



ራስ ምታት ይዞታል፣ ደግሞም አፉ እንደ አሸዋ ደርቋል:: በወንዝ ዳርቻ አቅራቢያ ወደ ነበረው መንደር ሲደርሱ ጊዜው ቀትር ነበር፣ ደግሞም የዘንባባ ዛፍ ወዳለበት ወደ ላይ ነዳና ከጥላው በታች አሳ ረፈ:: በዚያም በመሪው ላይ ራሱን አስደግፎ ዐረፈ:: የመኪናው ፊጥኖ መቆም ከእንቅልፉ ተነሥቶ ሰዓቱን የሚመለከተውን ቻ ርሊን ከእንቅልፉ አነቃው:: «ኦ፣ ጊዜው እኩለ ቀን ነው ደግሞም ይህን ያህል ርቀት ተጉዘናል!» አለ:: «ይህ ድንቅ ነገር ነው! ተ ስፋዬ፣ ምሳ እንብላ::»

እንደ ምንም ብሎ ተስፋዬ ከዳሰዋ/መጠለያዋ በታች በትንሿ ጠ ረጴዛ ላይ የተከሰተውን መንገዳገድ ለመቆጣጠር እንዲሁም በረዶ ያለው ቀዝቃዛ ውኃ ጠጣ:: ሌላ አንድ ሳህን ሾርባ ለመጠጣት ሞከ ረ፣ ነገር ግን በመሃሉ ሊወጣና ሊያስታውክ ግድ ሆነበት:: ራሱን በዶሮ አሮስቶ እና በተጠበሰ ድንች ጠምዶ የነበረው ቻርሊ ከዚያ ወጣና ረጃጅም ጠጉር ያለው ራሱን እያከከ በአጠገቡ ቆመ:: ምን ማድረግ የሚገባው ስለ መሆኑ ትንሽ እሳብ እንኳ አልነበረውም፣ ነገር ግን ከልብ አዝኖ ነበር::

«ምናልባት ከእኔ ተጋብቶብህ ይሆናል?» አለ:: «በእውነቱ አዝኛ ለሁ፣ ነገር ግን ጉዳዩ የ24 ሰዓታት ብቻ ነው:: አሁን ደኅና ነኝ:: እኔ አሽከረክራለሁ፣ አንተ ከበስተኋላ ሁን::»

ወደ ግባቸው በደረሰቡት ጊዜ ለሁለት ሰዓት ገደማ ጨለማ ነበር:- የተጨናነቀች መጥፎ ጠረን ያሳት ድርቅ ያለባት ከዋና ከተ ማ የሚመጣው በምሥራቅ ጠረፍ ወደ ካምፖቹ በሚወስደው ዋናው መንገድ ላይ ትንሽ ከተማ አለች::

ቻርሊ፣ ዜግነታቸው ምንም ይሁን፣ የእርዳታ ሠራተኞች በጉዞ ላይ ሳሉ ዕረፍት ለማድረግ ወደሚሄዱበት (ወደሚጠቀሙበት) ሆስቴል በቀስታ መኪናውን አሽከረከረ፣ ደግሞም ተስፋዬን እንዲከተለው ነገረው:: በትልቅ ግድግዳ ላይ ያሉ በደንብ በእንክብካቤ የተያዙ የአትክልት ቦታ ያለውን ቤት በክበቡ በሮች ውስጥ ዘልቀው ገቡ:: ቤቱ ከፊት ለፊት ወደ በረንዳው ክፍት ሆነው የሚታዩ ክፍሎችን ይዞ ይታያል፣ ነገር ግን ብዙውን ጊዜ

ጎብኚዎች አልጋዎቻቸውን ንጹሕ አየር ወዳለበት በሚያመጡበት ጊዜ ክፍሎቹ ባዶ ሆነው ነው የሚታዩት፣ እየዘገየም በሄደ መጠን፣ ሁሉም ይተኛሉ:: ነገር ግን ረጅም፣ ጥቁር ቆዳ ያለው መንግሥቱ ተብሎ የሚጠራ ሰው ለአፍታ ተነሣና ለእነርሱ ምግብ ማዘጋጀት ጀመረ::

«ግሩም ነው!» አለ ቻርሊ በሹክሹክታ:: «እየሆነ ያለው ነገር ሁሉ ጥሩ ነው:: እንዳገኘሃቸው፣ ሁለት ተጨማሪ እንሰሳዎችን ወደ አትክልት ስፍራው እንወስዳቸዋለን:: ተመልከት፣ አበቦቹ ካሉበት አጠገብ አንድ ክፍል አለ::»

ተስፋዬ እየጠነከረ ነበር፣ ደግሞም ትንሽ ሰላጣ እና ጥቂት የምስር ወጥ ማጣጣም ጀምሮአል፤ እንዲሁም፣ ምንም እንኳ በእግር ለመንዝ እጅግ የደከመ ቢሆንም፣ ይህ ረጅም ትሑት የሆነ የአገሩ ሰው ጉጉ በሆነ መልኩ እየተመለከተው ነበር:: ወዲያውም የቆሸሹ ልብሶቹንና ዕድፋማ ቆዳውን ልብ አለ:: ነገ ወደ ስደተኞች መጠለያ ይወስዱታል፣ ደግሞም ሁሉም ነገር ያበቃለታል::

«እኔ ለመታጠብ መሄዴ ነው፣» አለ ቻርሊ፣ ሳህኑን እየጠራረገ:: «አንተስ ምን ታስባለህ፣ ተስፋዬ? ሁለታችንም በአቧራ ተከናንበናል:: ራሳችንን እንለውጠው. . . » ካለ በኋላ ጓደኛው ያደረገው ሰው ምንም ቦርሳ አልነበረውም:: ነገር ግን አንድ ብርድ ልብስ፣ አንድ ማብሰያ ድስት፣ እንዲሁም አንድ የውኃ ኮዳ ነበር የያዘው:: ስለዚህም ግራ በመጋባት ንግግሩን አቋረጠ::

ለአፍታ ደስ የማይል ጸጥታ ሰፍኖ ነበር፣ ከዚያም የተመገቡበትን ሰሐን የሚሰበስበው መንግሥቱ፣ ዝግ ባለ ሁኔታ፣ «አንተ ከሩቅ ስፍራ፣ ምናልባትም ጠረፉን ተሻግረህ፣ ይሆናል የመጣኸው:: ለዚህ ምሽት ንጹሕ የሆነ ሸሚዝ ላውስህ እችላለሁ::»

«ደግሞም አንድ ተቃያሪ ሱሪ አግኝቻለሁ፣» ሲል ቻርሊ ጣልቃ ገባ:: «እኔ ትንሽ ከአንተ እወፍራለሁ፣ ነገር ግን አንተ በወገብህ ዙሪያ ልታስረው ትችላለህ:: እንግባ እና እንታጠብ::»

እንደገና ንጹሕ መሆን መልካም ነበር:: የቻርሊ ሳሙና እና ያየተባረከ ቀዝቃዛ ውኃ የተስፋዬን ትኩሳት እና የራስ ምታት



የሚያስወግድ መሰለ፤ ደግሞም ቀዘቀዝ ብሎና አእምሮው ብሩህ ሆኖ ጋደም አለ:: አልጋዎቹ የተጠጋጉ ነበሩ፤ ቻርሊ ቀድሞውኑ እያንኮራፋ በአንዱ በኩል፣ ጋደም ብሎአል፣ እንዲሁም በሌላው በኩል፣ ለስ የሆነ የምሽት ልብስ የለበሰች፣ ቆንጆ የሆነች ሴት እጆችዋ በራስዋ ላይ ሆነው፣ ደግሞም እንሶላዋ ወደ ታች ወርዶ ተኝታለች::

መታቀፉ እንዳይሰማው እጅግ ደክሞአል፤ የሆነ ሆኖ፣ ተስፋዬ ነገሮችን የሚያደርገው በዚህ መልኩ ከሆነ፣ ከዚህ አመሉ ጋር መኖዝ ይችላል፣ ምክንያቱም እርሱም ቻርሲን መምሰል ጀምሮአል:: ንጹሑን ጥጥ መኝታ እያጣጣመ፣ ውኃ ባለው ገንዳ የተተከሉ አበቦችን ትንፋሽ እየተነፈሰ፣ ስለ መጪው ጊዜ ግራ እየተጋባ፣ በባዶ ሆድ ዝም ብሎ እስከ ወዲያኛው መሄድ እንደማይቻል ስላልተገነዘበው፣ በከፊል ረሃብተኛ ለሆነ ሰው የማይስማማ ምግብ ስለ ሰጠው፣ ምንም ነገርን ለመለወጥ መጣርን ከቶ ስለ ረሳው፣ ይሁንና እንክብካቤ ስላደረገለትና ሱሪውን ስላዋሰው ሰው ቻርሊ ስለሚሰው ልጅ እያሰበ ነቅቶ ሳለ ለረጅም ጊዜ ጋደም እንዳለ ቆየ:: ነገ፣ እንደሚለያዩ/እንደሚለነባበቱ ምንም ጥርጥር የለውም:: ከዚህ ቀደም እንደ ሆነው፣ ጉዳዩ አንድ ተጨማሪ መለያየት ይሆናል፣ ያም ሆነ ይህ፣ በዚህ የዓለም ክፍል ውስጥ እጅግ ብዙ የስደተኞች መጠለያዎች ነበሩ:: በዚያ እንክብካቤ ያገኛል::

ወደ አራት መቶ ማይል ገደማ ተጉዟል፣ ደግሞም አንድ ቀን ወደ ገዛ ቀዬው ጠረፉን ተሻግሮ ለመሄድ ሩቅ አልነበረም:: በታላቅ ደግነት ይመግቡታል፣ ያለብሱታል እንዲሁም ይይዙታል፣ ደግሞም እግዚአብሔርን በጣም አመስጋኝ መሆን ይኖርበታል፤ ነገር ግን በዚያኑ ጊዜ፣ ይህን አያደርገውም ነበር:: በድካሙ ውስጥ ሳለም ፊቱን ወደ ፍራሹ መልሶ አሰቀሰ::

# 14

በሚ.ቀጥለው ቀን ተስፋዬ ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ፣ ቻርሊ ከጥጥ የተሠሩ ጥንድ የሆኑ ሰማያዊ ፒጃማዎችን እንደ ለበሰ በአልጋው ጠርዝ ላይ ተቀምጦ፣ ወደ እርሱ አተኩሮ ይመለከተው ነበር:: ልጅቷ በመሄድዋ ዕረፍት ሆኖለታል:: ተስፋዬ ተነሣና እንድምን አደርክ? አለ:: ከዚያም የገዛ ራሱን ልብሶች ለማጠብና የቻርሊን ሱሪ ለመመለስ ጥያቄ  አቀረበ፣ ነገር ግን ቻርሊ ደስተኛ መስሎ አልታየም::

«ተስፋዬ፣ ዛሬ  የት ልትሄድ ነው?» ሲል ጠየቀ::

ተስፋዬ ስለዚህ ጉዳይ አሰበ:: «ድንበሩን ተሻግሬ ከስፈራ ጣቢያው ነው የመጣሁት፣» አለ በመጨረሻ:: «ባለቤቴ አብራኝ አምልጣ ነበር፣ ነገር ግን በቍጥቋጦው ውስጥ ሞተች. . .እየሸሸች ሳለ ተኵሰው ገደሏት:: እኛን በወሰዱበት ጊዜ የተውናቸው ልጆች እቤት አሉ:: አንድ ቀን፣ ዝናቡ በሚዘንብበትና ሕዝቤ ተመልሰው ወደ ቀዬአቸው በሚሄዱበት ጊዜ እፈልጋቸዋለሁ:: ነገር ግን፣ ዛሬ . . . የማውቀው ነገር የለም:: ወደ ካምፑ የምትወስደኝ ከሆነ፣ ደስተኛ  እሆናለሁ::  ከዚህ  በኋላ  በእግሬ  መጓዝ  የምችል አይመስለኝም::»

«ወደ ካምፑ ልውሰድህ?» ሲል ቻርሊ አቋረጠው:: «በፍጹም አይሆንም:: እኔ ሹፌር እፈልጋለሁ:: እንደገና ለብቻዬ ረጅም መንገድ አልሄድም፣ በተለይ እንዲህ ያለ ነገር ከሆነ በኋላ:: ጥቂት ወረቀቶችንና የመንጃ ፈቃድ እስካወጣልህ ድረስ ለትንሽ ጊዜ ከእኔ ጋር ብትከርምስ፣ ተስፋዬ?»

ተስፋዬ በኀዘን ራሱን ነቀነቀ:: የልቡን ድንገተኛ መነሣት ለተወሰኑ ጊዜያት አልነበረም የካደው:: «ላገለግልህ  ዝግጁ ነኝ፣» አለው:: «ነገር ግን ልብሶች ሊኖሩኝ ይገባል::»

ወዲያውም በጀርባው ላይ ሕመም በሚሰማው መልኩ መታ መታ እያደረገው፣ «ምንም ችግር የለም፣» አለ ቻርሊ:: «ይህን ፈጥነን እናስተካክለዋለን::» መላው ፊቱ ፈካ አለ፣ እንደ ተስፋዬ አሳብ፣ ከባድ መኪና መንዳት ለዚህ ልጅ እጅግ ተገቢ ያልሆነ ነገር ነበር:: «አሁን እሑድ እንደ መሆኑ፣ ወረቀቶችህን ለማግኘት ብዙ ቢሮዎች ዝግ ስለሚሆኑ አንድ ሁለት ቀን ይወስዳል:: ነገር ግን አንተ አሁንም እጅግ ትመጥናለህ የምትባል አይደለህም፣ ነህ እንዴ? ደግሞም መንግሥቱ እኔ ዝግጁ እስከሆን ድረስ እዚህ መቆየት እና ማረፍ ትችላለህ፣ እንደዚሁም ደስ እንዳለህ መሄድም መምጣትም ትችላለህ» አለው:: «ረቡዕ ማለዳ ላይ ሰሜን ወዳለ ካምፕ (ጣቢያ) የምግብ አቅርቦት ለማድረስ እሄዳለሁ:: ሩቅ አይደለም፣ የአራት ሰዓት መንገድ ብቻ ነው:: ከእኔ ጋር አብረህ እንድትሄድ እፈልጋለሁ::»

ተስፋዬ፣ «በቀላሉ ረቡዕ ማለዳ እዚህ ታገኘኛለህ፣» አለ፤ ቻርሊም ደስ ብሎት እየዘለለ ሄደ::

ተስፋዬ ለተወሰነ ጊዜ የአትክልት ስፍራውን ሰላምንና አረንጓዴነትን እንዲሁም የመጪው ዕድሉን እያጣጣመ ተቀመጠ፣ ከዚያም ቍርስ እንዲበሉ አንድ ሰው ጠራው:: በመጀመሪያ የእነዚህ ወጣት ወንዶች እና ሴቶች ዓለም አቀፋዊ ቡድንን ለመቀላቀል አፍሮ ነበር፣ ነገር ግን የጋራ ቋንቋቸው እንግሊዝኛ ሆኖ ተገኘና እርሱን ወዲያውኑ ከእነርሱ እንደ አንዱ አድርገው ተቀበሉት:: በመልካም መንፈስ ውስጥ ያሉ መሰሉ፤ የሚያከናውኑት ሥራ ስለ ነበራቸው በፍጥነት በሉ እና ጠጡ፣ እርሱም ወዲያውም ከመንግሥቱ ጋር ተገናኘ:: ተስፋዬ ጠረጴዛውን በመወልወል እና ድስቶቹን በማጠብ መንግሥቱን ረዳው፣ ወዲያውም መንግሥቱ፣ «በአሥር ሰዓት እግዚአብሔርን ለማምለክ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን እሄዳለሁ:: ከእኔ ጋር መሄድ ትፈልጋለህ?»

ተስፋዬ አመነታ:: በቍጥቋጦው ውስጥ በወደቀ ጊዜ ከልጆቹ የለየውን፣ ሙናን የወሰደበትን አምላክ ለማምለክ ያልፈለገበት ጊዜ

ነበር፣ ነገር ግን ባለፉት ጥቂት ቀናት ስሜቶቹ በሆነ መንገድ ተለውጠዋል። ቻርሊ እግዚአብሔር መልካም እና ሊመሰገን የሚገባው መሆኑን አስታወሰው፣ ስለዚህ ግብዣውን ተቀበለ። ዘጠኝ ተኩል ሲሆን ሄዱ፣ ደግሞም መስጊዱን እና የገበያ ስፍራውን እንዲሁም ቅርጫት ሠሪዎችን እና ሸክላ ሠሪዎችን አልፈው ገለል ወዳለው መንገድ እስከ ታጠፉና ረጅም ወደ ሆነው ዝቅ ያለ ሕንፃ እስኪደርሱ ድረስ ሄዱ። ተስፋዬ እጅግ ፈጥነው የመጡ እስኪመስለው ድረስ ሁኔታው ጸጥ ያለ ነበር። ራሶቻቸውን ዝቅ አድርገው ተቀምጠው በጸጥታ በሚያመልኩ ስዎች ስፍራው ተሞልቶ በማግኘቱ ተስፋዬ በጣም ተገረመ፣ ደግሞም መቀመጫ ማግኘት እጅግ አስቸጋሪ ነበር። ልጆችና ወጣቶች በወለሉ ወይም በመድረኩ ደረጃዎች ላይ ተቀምጠዋል፣ ደግሞም የገዛ ራሱን ሕዝቦች ይመስሉ ነበር።

ምን ዓይነት ልዩና አስገራሚ ቤተ ክርስቲያን ናት! በግድግዳዎቹ ላይ ምንም ዓይነት ቅርጸች፣ ሥዕሎች ወይም ምስሎች አልነበሩም፣ ደግሞም ምንም የዕጣን ሽታ አልነበረም። በመድረኩ ላይ የቆመው እና የሚዘመሩ መዝሙሮችን ይመራ የነበረው ሰውዬ እንደ ካህን አልለበሰም ነበር፣ ደግሞም በተስፋዬ አነጋገር (ቋንቋ) ይናገር ነበር። ከዚያም መዝሙሩ በደመቀ ሁኔታና በደስታ እንዲሁም በጭብጨባ ይዘመር ጀመር፣ ደግሞም ከዚህ ቀደም ከቶ አይቶት የማያውቀው ብርሃን በማኅበረ ምእመናኑ ፊት ላይ ይታይ ነበር። ከዚያም፣ ከሁሉም ለእርሱ ባዕድ የሆነው፣ መጽሐፍ ቅዱስ በገዛ ራሱ ቋንቋ ተነበበ፣ ደግሞም ተጨማሪ መገረም የሆነለት፣ ብዙዎች ሰዎች የገዛ ራሳቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያላቸው መሆኑን ልብ አለ፤ ደግሞም ስብከቱን ለመከተል ጥቅሶቹን ያወጡ እንደ ነበረ ተመለከተ። ራሱ መጽሐፍ ቅዱስን ከቶ አንብቦ የማያውቅ ስለሆነ፣ ደግሞም ለመጀመሪያ ጊዜ እርሱ በእውነት ሊረዳው በሚችል ቋንቋ  የስቅለትን ታሪክ፣ በግልጽ አዳመጠ።

በመጀመሪያ እርሱ ቀድሞውኑ በተመለከታቸው በብዙዎች ሞት ተጨማሪ የሆነ የጭከና ሞት (አሟሟት) ይመስል ነበር፣ ነገር ግን እያዳመጠ ሲሄድ፣ አስተሳሰቡ ተቀየረ። ወዲያውም



በክፍሉ ውስጥ፣ በቊጥቋጦዎቹ ውስጥ፣ በመንገድ ዳር፣ በረሃብ እና በጥማት፣ በበሽታ እና በከባድ ቊስሎች የሞቱትን ከዚያ በእንጨት መስቀል ላይ ከተሰቀለው ብቸኛ ሰው በቀር የሚወክል ማንም የሌለ መሰለ። ሁሉም እነዚያን፣ «አምላኬ፣ አምላኬ ስለ ምን ተውኸኝ?» የሚሉትን አሳዛኝና ለረጅም ጊዜ ከአእምሮ የማይጠፉ  ቃሎች ሁሉም አስተጋቡዋቸው።

ለምን? ለምን? ኢየሱስ በጊዜው መልሱን አያውቀውም ነበር፣ ወይም ይህን ጥያቄ መጠየቅ አይገባውም ነበር። ይሁንና፣ የተሰጠፈ ምስል ወይም ሩቅ ያለ ታሪካዊ ሰው ሳይሆን፣ ነገር ግን እነርሱ እንደ ተሠቃዩት ሁሉ ወደዚህ ቀርቦ እንዲሠቃይ በሆነ መልኩ እርሱን ቅርብ እንዲሆን አደረገው። መንፈሳዊ አገልግሎቱ እየተቋጨ ነበር፣ ደግሞም እንደገና ይዘምሩ ነበር፣ ዝማሬው «ኦ፣ ኢየሱስን በኃይል እወደዋለሁ፣ ለእኔ ብዙ ነገር አድርጎልኛል» የሚል ነበር፣ ደግሞም እየዘመሩ ሳለ ፊታቸው ያበራ ነበር። ነገር ግን ለምንድን ነው ያንን የተሰባበረና የተሠቃየ ሰው ሊወድዱት የተገደዱት? ለእነርሱ በትክክል ያደረገላቸው ነገር ምንድን ነበረ?

ወዲያውም የበለጠ ለማወቅ ታላቅ ፍላጎት አደረበት። ሕዝቡ እየተግተለተለ በመውጣት ላይ ነበር፣ ደግሞም ስብከቱን ያቀረበው ወጣት ሰውዬ በበር ላይ ቆሞ የሰዎችን እጆች እየጨበጠ ይሰናበት ነበር። የተስፋዬ ተራ በደረሰ ጊዜ፣ በኃፍረት፣ «መጽሐፍ ቅዱስ መዋስ እችላለሁኝ? መጽሐፍ ቅዱስ ለመግዛት ገንዘብ የለኝም፣» አለው።

ወጣቱ መጋቢ አንድ አዲስ ኪዳን አነሣና አስረከበው። «ከዚህ በፊት አንብበኸው ታውቃለህ?» ሲል ጠየቀው።

«በገዛ ራሴ ቋንቋ ከቶ አንብቤው አላውቅም፣» አለ ተስፋዬ። በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ካህናቱ ብቻ በሙላት ሊረዱት በሚችሉት በጥንታዊ ቋንቋ (በግዕዝ) ይነበባል፣» አለ።

መጋቢውን አመስግኖ ሊያልፍ ነበር፣ ነገር ግን እጆቹ በጽኑ ስለ ተያዙ ሊያልፍ አልቻለም።

«ዛሬ ከሰዓት በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተህ ልታነጋግረኝ

ትወድዳለህ?» ሲል ወጣቱ ለውዬ ጠየቀ:: የሰንበት ትምህርት ካስተማርሁ በኋላ 10 ሰዓት ላይ እዚህ እገኛለሁ፣» አለው::

«እመጣለሁ፣» ሲል ተስፋዬ መለሰ እና ሰምላ ከመንግሥቱ ጋር ሄደ:: ማስረጃዎቹ እስኪዘጋጁ ድረስ ወጪዎቹን ቻርሊ የሚሸፍንለት በመሆኑ የሚጨነቅበት ምንም ነገር አልነበረም:: ከተመገበ በኋላ በሚገባ አንቀላፋና ልክ በመሄጃው ሰዓት ነቃ::

መጋቢ ይስሐቅ በቤተ ክርስቲያን እየጠበቀው ነበር፤ በኤሌክትሪክ አየር ማቀዝቀዣ አየሩ ቀዝቀዝ ያለና አስደሳች ነበር:: ስለ እርስበርሳቸው መረጃዎችን በመለዋወጥ መነጋገር ጀመሩ:: ይስሐቅ በረሃብ ምክንያት ሳይሆን፣ በእምነቱ ምክንያት ከሁለት ዓመታት በፊት በስተደቡብ ያለውን የመኖሪያ ቀዬውን ለቅቆአል:: አብዮቱ በፈነዳበት ወቅት የ16 ዓመት ልጅ ነበር፣ ነገር ግን አብዮቱ የፈነዳው ለጥቂት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን እንደ ተመላለሰ እና መጽሐፍ ቅዱስ ገና እንደ ተሰጠው ነበር:: ስለ ኢየሱስ እርሱ፣ ወደ እግዚአብሔር የሚወስድ መንገድ እና የዓለም መድኃኒት (አዳኝ) መሆኑን እነበበለት፣ ደግሞም ለተስፋዬ ለእርሱ እንግዳ በሆነ መንገድ፣ መጋቢውን ይወድደው ጀመር:: የኢየሱስን መልካም ዜና ለእራሱ ብቻ ሊይዘው አይችልም ነበር፤ ደግሞም እስራትን፣ መገረፍን እና ሞትን ታግሦአል፣ ምክንያቱም የቀደመ እምነቱን ብቻ መተው ሳይሆን፣ ለሌሎችም ሊነግር ተገብቶት ነበርና:: በመጨረሻም በሚቀጥለው ቀን እንደሚታሠር እና በጥይት እንደሚገደል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ነበር:: ጠንካራ እና ሯጭ በመሆኑ፣ እርሱ እና ጓደኞቹ ለ17 ሰዓታት ከሮጡ በኋላ ጠረፉን ተሻግረው ወደ ስደተኞች ማረፊያ ገቡ:: ይስሐቅ በደንብ የተማረ እና እምነት የሚጣልበት ሰው ስለ ነበረ በስደተኞች መርጃ ድርጅት ውስጥ ሥራ አገኘ:: አሮጌ ከሆነው የስደተኞች ሰፈርም ትንሿን ቤተ ክርስቲያን እሁን ወደምትታይበት ሙላት እስክትደርስ ድረስም ገነባት (መሠረታት):: ደግሞም በእያንዳንዱ እሑድ ማለዳ አዳዲስ ሰዎች ያጨናንቋታል::

«እግዚአብሔር ረሃብ፣ መከራ እና ሞትን ላከብን፣» አለ ተስፋዬ፣ ደግሞም ድምፁ ምሬት ያለበት ነበር:: «ባለቤቴን



በቍጥቋጦዎች ውስጥ ቀበርኳት:: እየሮጠች ሳለ ተኩሰው ጣሉዋት፤ እግሮችዋ ተቃጥለው ነበር:: ልጆቼ ለብቻቸው ተትተዋል፣ ምናልባትም ለሞት ተትተዋል:: ለምንድን ነው ይህን ኢየሱስን መውደድ የሚገባኝ?»

ይስሐቅ፣ ግርፋቱን እና ፍርሃቱን እያስታወሰ፣ ለተወሰነ ጊዜ ጸጥ አለ:: ለምንድን ነው እርስ እጅግ መውደድ የሚገባው? ያንን መልእክት ከማስተላለፉ ደስታ ጋር ሲመዛዘን፣ ሕይወት እራስዋ ጉልህ ያልሆነች የምትሆነው ለምንድን ነው?

በመጨረሻም፣ ቀስ ብሎ እየተናገረ፣ ይስሐቅ፣ «የምንኖረው በተበላሸች ዓለም ውስጥ ነው፣» አለ:: «የእግዚአብሔር መንገድ ወደ ጤና እና ደስታ እንዲሁም ወደ ፍቅር ይመራል፣ ነገር ግን እኛ ኃጢአትን እና እራስ ወዳድነትን እንዲሁም ጦርነትን መረጥን፤ ክፉው ጌታችን ሆነ እንዲሁም እኛ የእርስ ባሪያዎች ሆንን:: ነገር ግን፣ አሁን ጠፍተን እና ተበላሽተን ሳለን፣ አሁንም እግዚአብሔር ይወድደናል:: ልጆቻችሁ ጠፍተዋል እንዲሁም ርቀው ሄደዋል፣ የክፉ ሥርዓት አገዛዝ ምርኮኞች ሆነዋል፣ ነገር ግን አሁንም ትወድዱአቸዋላችሁ፣ ደግሞም እነርሱን ለማግኘት የቱንም ርቀት ትጓዛላችሁ:: እግዚአብሔርም እንደዚሁ ወደ እኛ ለመምጣት ትልቅ ርቀትን ተጓዘ:: እርስ ሰው ሆነ፤ ሰው የሆነው ኢየሱስ::»

«ነገር ግን መከራ ስለ ተቀበሉት፣ በሺህዎች ስለሚቈጠሩት ስለ ተራቡት ሰዎች  እንዲሁም ስለ ሞቱት ምን ይባላል? ስለ ታሰሩት ሰዎችና በአደባባዮች ላይ ስለ ሞቱት ሰዎች ምን ይባላል?»

«እርስ የክፉው እና የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ሕግ ፊታቸውን መልሰው ኃጢአትን ለማገልገል የመረጡት አኗኗር ገጽታ ነው:: አንዳንድ ጊዜ በአራችን ውስጥ ክፉ የሆኑ ሽፍቶች የቤተሰብ አባል የሆነ ሰውን ያግቱ እና ብዙ ክፍያ ይጠይቃሉ:: ኢየሱስ ከክፉው ነፃ ሊያደርገን እና መልሶ ወደ እግዚአብሔር ሊያመጣን እንደ መቤዠያ ክፍያ፣ የገዛ እራሱን ፍጹም የሆነ ሕይወት፣ እራሱን አቀረበ:: በመስቀል ላይ በሞተበት ጊዜ በሁሉም ዓለም እና በዘመናት ሁሉ ለሚኖር ለበሽታ፣ ለኃጢአት፣ እንዲሁም

ለመከራ የተጠየቀውን ዋጋ ከፈለ። ይህ ምሥጢር ነው። አሁንም ገና ልገልጸው አልችልም፤ ነገር ግን ይህን አውቃለሁ፦ የገዛ እራሳችንን የግል ኃጢአት ወይም ለቆቃ ወደ ተሰቀለው አዳኝ በምናመጣበት ጊዜ፤ እርሱ ስለ እኛ ሆኖ ይሸከመዋል፤ ደግሞም በእርሱ ፈንታ ይቅርታን፤ ሰላምን እና ድልን ይሰጠናል። እኛ፤ በእምነት፤ በእጆቹ ውስጥ ልናስቀምጠው እንችላለን። ችግራችን በቍስሎቹ ይነካል፤ ደግሞም ፍቅሩ እጥቦ ያስወግደዋል። ሙሉ በሙሉ ለእርሱ የተሰጠ ነገር ወደ ክፋት ሊመለስ አይችልም። ከእርሱ አንድ ውብ የሆነ ነገር ያወጣል። ነገር ግን መምረጥ ይኖርብናል።»

ይስሐቅ ይናገር የነበረው ተስፋዬ በለመደው የአነጋገር ለዛ ነበር፤ ደግሞም ተስፋዬ እንደዚህ ያሉ ቃሎች ከዚህ በፊት ሰምቶ አያውቅም ነበር። ያለፉት ወራት ኃዘኖች ሁሉ እየጐረፉ ወደ እርሱ ተመልሰው የመጡ መሰሉና እርሱም ለማልቀስ ፈለገ። አሁንም በጣም ደክሞታል። ለመሄድ ተነሣ።

«መጽሐፉን አነብበዋለሁ፤ ከዚያም የበለጠ እረዳለሁ። እዚህ የምሠራው ሥራ ስላለኝ ለተወሰነ ጊዜ እቆያለሁ። ተመልሼ እመጣለሁ፤» አለ።

ደኅና ሁን ተባባሉና ወደ ቤቱ ተመልሶ ሄደ። በቤተ ክርስቲያን የምሽት መንፈሳዊ አገልግሎት ነበር፤ ነገር ግን፤ ለመሄድ እጅግ እንደ ደከመው ተሰማው፤ ስለዚህ ስለ ልጆቹ እያሰበ በአትክልት ስፍራው ውስጥ ጋደም አለ። ለሚሠራው ሥራ ገንዘብ የሚከፈለው ይሆናል፤ ስለዚህም፤ ትንሽ ትንሽ ገንዘብ ማጠራቀም ይችላል፤ ዝናብ ከመጣ፤ በእርግጠኝነት አንዳንድ ሰዎች ወደ ቀዬአቸው (አካባቢያቸው) ተመልሰው ይሄዳሉ። ነገር ግን፤ ልጆቹ አሁንም በዚያ ይኖራሉን? ልቡን በፍጥነት ሲመታና በፍቅር ደንድኖ እየናፈቀና በፍርሃት ውስጥ ሆኖ አገኘው። «እነርሱን ለማግ ኘት የቱንም ያህል ርቀት ትጓዛለህ፤» አለ ይስሐቅ። «እንደዚሁ እግዚአብሔር ወደ አንተ ለመምጣት ታላቅ ርቀትን ተጕዟል።»

መጽሐፉን ከፈተና ስለ ኢየሱስ ማንበብ ጀመረ።



ምሕረትና ተክሌ በትንሿ የስደተኞች ጣቢያ ኑሮአቸውን በተረጋጋ ሁኔታ መምራት ጀምረዋል፤ የሚለበልብ ሙቀት ቢኖርም፤ በአጠቃላይ ደስተኞች ነበሩ። በወንዙ ውኃ መውረጃ ስፍራ የነበ ረውን የዘንባባ ዛፍ ጥላ እና የውኃ ምንጮችን አጥተዋቸዋል፤ ነገር ግን ድንኳኖች ለኑሮ ቀላል ነበሩ፤ እንዲሁም ከመጠለያዎች ይልቅ፤ ክትት ያሉ ናቸው፤ ደግሞም ካህኑ እና ባለቤቱ አዲስ መኖሪያ ቤታቸውን ሊያጋሩዋቸው ፈቅደውላቸው ነበር። በየማለዳው ማለት ይቻላል፤ ከባድ መኪናዎች በሚያመጡዋቸው ሰዎች ካምፑ ሙልት ይል ነበር። ነገር ግን ከ20,000 ሰዎች በላይ ከፍ ብሎ ከቶ አያውቅም፤ በዚያ ረሃብ ባለበት ለጥ ያለ በረሃ ቢያንስ ቢያንስ ካምፑ የት እንደ ተጀመረ እና የት እንደሚያበቃ ማየት ትችላላችሁ።

ምሕረትን በተመለከተ፤ ከሁሉ ይሻላል ብላ ያለችው፤ ኤማ በዚያ መሆንዋ ነበር። ኤማ ቡናማ ጥቅል ጠጕር፤ ትላልቅ ቡናማ ዓይኖች፤ ቀጥ ያለ አፍንጫ እና ጠቃጠቆ ፊት ነበራት፤ የሕክምና ድጋፍ በሚሰጥበት የመመገቢያ ማዕከል ውስጥ ወተት በማዘጋጀትና እጅግ የደከሙ ሕፃናትን ጤና በመከታተል ትሠራ ነበር። ምሕረት እርሷን የቀረበቻት ብሩህ ልብስ የለበሰው ሕፃን በሞተ ጊዜ እርሷ ባለቀሰችበት ጊዜ ነበር፤ ነገር ግን ኤማ በዚያው ቀን ተክሌን ወድዳው ስለ ነበረ፤ እርሷም ኤማን ወደደቻት። እርሱ በምሽት ሲጓዝ ከነበረው የጭነት መኪና ትንሽዬ የባንዲ አፍ መስሎ እጅግ ደክሞ ነበር እዚያ የደረሰው፤ ተመገበና ለረጅም ጊዜ ተኛ። እጅግ ለረጅም ጊዜ ከመተኛቱ የተነሣ ኤማ ተደናግጣ እርሱን ለመመልከት ሄደች። ገና የ23 ዓመት ወጣት ስለ ነበረች፤ በቀላሉ ትደነግጥ ነበር። ቀስ ብላ ነቀነቀችው እና ነቃ፤ ደግሞም

ወደ እርሷ ቀና ብሎ ተመለከተ፣ አስቀያሚ የሆነው አጥንተ ወጥ ፊቱ ትልቅ ፈገግታን ሰጠ፡፡ ምንም ምክንያት ባይኖርም፣ እጆቹን ለእርሷዋ ዘረጋላት እና ወደ ዕቅፏ ወጣ፣ እርሷም በወለሉ ላይ ተቀመጠች እንዲሁም ወዲያው በፊት ለፊትዋ ተዝለፍልፎ እስኪወድቅ ድረስ ዕቅፍ አደረገችው፡፡ ነገር ግን ነገሩን ደንታ የሰጠችው አትመስልም ነበር፤ ሳቀች፣ እንዲሁም ሌላ አንድ ኩባያ ወተት እንድታመጣ ምሕረትን ላከቻት፡፡ ምክንያቱም፣ ለኤማ እና ተክሌ በመጀመሪያው እይታ ጉዳዩ ፍቅር ነበር፡፡

ምሕረት እስከ ፍጻሜው ድረስ ደግነትን ታውቀዋለች፡፡ አሁን ከዶክተር ጋር እየሠራ ያለውን አጐታቸው ገብሬን እግኝተውታል፣ እርሱ እድካሚ በሆነ ተግባር ውስጥ ቢጠመድም እንኳ ደግ ነበር፡፡ የካህኑ ባለቤት ከመጠን በላይ የሆነ ጥንቃቄ ባለበት መንገድ እንዲሁ ደግ ነበሩ፤ ነገር ግን የኤማ ደግነት ልዩ ነበር፡፡ በማዕከሉ ውስጥ በደርዘን የሚቈጠሩ ትናንሽ ሕፃናት ነበሩ፣ እርሷም ለሁሉም ደግ ነበረች፣ ነገር ግን ምንም እንኳ ማንም ልብ ያለው ባይኖርም፣ ተክሌ ለእርሷ የተለየ እንደ ሆነ ምሕረት አውቃለች፡፡ ምሕረት ለኤማ ልክ የቈሸሹ ኩባያዎችን መሰብሰብ፣ ትናንሽ ጉድጓዶችን መቆፈር ወይም ተቅማጥ የያዛቸው ልጆች በጊዜው ከመጠለያው ለመውጣት በሚያቅታቸው ጊዜ፣ በስሌኑ ላይ ያመለጣቸውን ተቅማጥ መጥረግ ጀምራለች፡፡ ብዙዎች ሰዎች እርሷ በሥልጠና በሥራው ውስጥ ተሳታፊ እንደ ተደረገች፣ ተክሌ ባይኖር ደግሞ ሥራ ትቀጠር እንደ ነበር ያስባሉ፡፡ ነገር ግን እርሷ ስለ ኤማ ፍቅር ማድረግ የምትችለውን ሁሉ ታደርግ ነበር፡፡

አንዳንዴ በቀትር ጊዜ፣ እናቶችና ሕፃናት በአብዛኛው በሚያንቀላፉበት ጊዜ፣ ኤማ ትመጣ እና ከእጠገብዋ በምንጣፍ ላይ ትቀመጥ እንዲሁም ተክሌ በዕቅፏ ላይ ይለፍር ነበር፤ ምሕረትም ለእርሷ ቋንቋን ታስተምራት ነበር፡፡ ምሕረት በትምህርት ቤት ውስጥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መማር ጀምራ ነበር እና ጥቂት ቃሎችን ታውቅ ነበር፡፡ ኤማ፣ «እንደ ምን እደራችሁ?» እና «ወተታችሁን ጠጡ፣» በምሕረት ቋንቋ በትክክለኛው መንገድ ስትናገር መስማት አስደናቂ ነገር ነበር፤ ወይም በተሳሳተ መንገድ ብትለው ኖሮ፣ ኤ



ማ ጠጕርዋን ወደ ኋላ ትመልሰው እና ትስቅ ደግሞም ምሕረትም እንደዚሁ ትስቅ ነበር፣ ደግሞም ያ መልካም ነበር፣ ምክንያቱም እርሷ ከሳቀች ረጅም ጊዜ ሆኖአት ነበርና፡፡ ኤማም እንደዚሁ ለምሕረት ጥቂት የእንግሊዝኛ ሐረጋትን ታስተምራት ነበር፤ ይህም እንደዚሁ መልካም ነገር ነበር፣ ምክንያቱም ከኀዘን እና ከትዕግሥት በቀር ሌላ ነገር ከተማረች ወራት ተቈጥረዋልና፡፡

ሳምንታት አለፉ፣ ከዚያም አንድ ቀን በእየሩ ላይ፣ ዕረፍት ነሺነት ይታይ ጀመር፤ የድንኳኑን ክዳን የሚያነሣ ሙቀት ያዘለ ንፋስ፣ ጠቅጣቃ የሆነ ክባድ የእየር ንብረት ደግሞም ጥቅጥቅ ያሉ ደመናት በምሥራቁ እድማስ ላይ ነበሩ፡- እየሩ እየተለወጠ ነበር፡፡ በካምፑ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች እራሳቸውን ቀና አድርገው ስለ ቤቶቻቸው አሰቡ፤ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ግግር በሆነው የመሬቱ ዱኳዎችን ተመለከቱና የከባድ መኪናዎች ጐማዎች በጭቃ ሲያዙና ሲቆሙ አሰቡ፡፡

ማንም ሊጋፈጠው የማይፈልግ ውሽንፍር እስኪሆን ድረስ በመላው የከሰዓት በኋላ ጊዜ ንፋሱ ወደ ላይ ተነሣ፡፡ በመመገቢያው ጣቢያ የነበሩ እናቶች በአብዛኛው ወደየ ድንኳኖቻቸው ነበር፤ ነገር ግን ምሕረት እሁንም እዚያው ቆየች፡፡ ተክሌ ወደ ትክክለኛው ክብደት እየመጣ ነበር፣ ነገር ግን እርሷ እራሷ ከተገባው ክብደት በታች ነበረች፡፡ ከእርሱ ጋር በውሽንፍሩ ውስጥ መሮጥ አልቻለችም ነበርና ለእርዳታ ዙሪያውን ተመለከተች፡፡ ምናልባት በዚያ ከሚሠሩ አስተናጋጆች አንዱ ይሸከመው ይሆናል፡፡

ልታድናቸው የመጣችው ኤማ ነበረች፡፡ ሩቅ ከሆነው የመጠለያው ጫፍ ሦስት ባዶ የሆኑ ጆንያዎችን ተሸክማ ብቅ አለች፤ ደግሞም አንዱን በገዛ ራሷ ላይ እንዲሁም ሌላውን በምሕረት ራስ ላይ አጠለቀች፡፡ ከዚያም ተክሌን አነሣችው፣ ፊቱን በትከሻዋ ላይ ሸፈነችውና በሦስተኛው ጆንያ ሸፈነችው፡፡ «አሁን እንሩጥ!» አለች፣ ከዚያም ፍጥነታቸውን በዕጥፍ ጨምረው ማለት ይቻላል ቀጥታ ወደ ማዕበሉ ይሮጡ ነበር፣ ምክንያቱም አቧራው እና የአሸዋው ብናኝ፣ ወደ ዓይኖቻቸው በመንፈስ እይታቸውን ጋረዳቸው፡፡ ክንዶቻቸውና እግሮቻቸውን መጓዝ ከለከላቸው፣

ደግሞም ሁሉም በአንድ ላይ በድንኳኑ በሮች በኩል ወደ ውስጥ እየሳቁ ወደቁ። ምሕረት እየመራቻቸው መንገዱን ትንፋሽዋ ቁርጥ ቁርጥ እያለ እና እየሳለች ጨረሰችው። ጸሎቱን እያነበነበ ያለው ካህን እና አሮጊትዋ ባለቤቱ በንቃት በእግሮቻቸው ጥግ ላይ በፍርሃት ቁጢጥ ብለዋል። ወደ ድንኳኑ ውስጥ የአቧራ ብናኝ በሚያስገባ ዐውሎ ነፋስ ውስጥ የሚያስቅ ምንም ነገር ለማየት አልቻሉም፣ ደግሞም በእንደዚህ ዓይነቱ መደሰት ደነገጡ። ግንባራቸውንም ቋጠር አደረጉ።

ነገር ግን በኤማ ላይ ለረጅም ጊዜ ግንባርን መቋጠር ይከብድ ነበር። ወደ ቤትዋ የሚወስዳት ላንድሮቨር መኪና ለግማሽ ሰዓት ጊዜ ይቆያል፣ እርሷም ራስዋን በማስደሰት ላይ ነበረች። እነርሱን ልታነጋግራቸው አልቻለችም ነበር፣ ነገር ግን ተክሌን በእጆችዋ ውስጥ እስተኝታው በአገርዋ ለትናንሽ ልጆች የሚዘመር መዝሙርን እየዘመረች ወደ ፊትና ኋላ ትመላለሳለች። ምሕረትም፣ በተራዋ፣ የተራራዎችዋን ዝማሬ ትዘምር ነበር፣ ደግሞ ወዲያውም የካህኑ ሚስት እጆቻቸውን እያጨበጨቡ እና በማይረሱ ረገዳዎች እግሮቻቸውን እየጠበጠቡ ቍጣቸውን ትተው ይቀሳቀሷቸዋል። ከዚያም ምንም እንኳ ኤማ በብዙ ብትጥርም፣ ሁልጊዜ ስለምትሳሳት፣ በሳቅ ዘወትር ቢያቋርጡትም፣ ሁሉም በአንድነት ማጨብጨብና በእጆቻቸው መታ መታ ማድረግ ጀመሩ። በጣም የሚያስደንቅ ምሽት ነበር፤ ኤማ በድንኳኑ ውስጥ ተቀምጣ ሳለ በውጭ ያለውን ውሽንፍር መፍራታቸውን አቆሙ። እርሷ ከሄደች በኋላ እንኳ፣ ልክ እንደ ወደብ መብራት ተስፋ ትውስታው አብሮአቸው ነበር። ከጨለማዎቹ ወራት ባሻገር፣ በአንድ ላይ በደስታ ነበሩ። ሳቅ አልሞተም ነበር፣ ደግሞም ጥንታውያኑ መዝሙሮች አልጠፉም ነበር።

ኤማ ራስዋን በጆንያ ሸፈነች ደግሞም በዚያ ነፋስ ኃይል ለትንሽ ወደ ኋላ ተመልሳ ነበር። ነገር ግን በእርሷም ላይ እንደዚሁ አንድ ነገር ተከስቶ ነበር። ከጥቂት ሳምንታት በፊት ከእንግሊዝ በመጣችበት ጊዜ ባየችው ነገር ፈርታ ነበር። ከዚያን ቀን ጀምሮ በድብርት እና በናፍቆት ተቸግራ ነበር። ነገር ግን በድንኳኑ ውስጥ



ያሳለፈችው ግማሽ ሰዓት ልክ እንደ ቤት ውስጥ መጫወት፣ መሳሳቅና በአንድነት መሆን ሆኖ ነበር። በመሠረቱ፣ የእርሷ እያቶች ሊሆኑ የሚችሉቱ በዚያ ጥግ የነበሩ ቡትቶ ለባሽ አዛውንቶች እንኳ በማጨብጨብ እና በመወዛወዝ ራሳቸውን ያስደስቱ ነበር። ውጫዊ ሁኔታዎች በጣም አታላይ ሊሆኑ እንደሚችሉ መማር ጀመረች፤ ወደ ፍሬ ነገር ውስጥ መግባት ይኖርብሃል፣ ፍሬ ነገር በማይለይ መልኩ በዓለም ሁሉ ያው ነው። ምናልባት ከዚህ በኋላ እንዲህ ያለ ባዕድነት እንደማይሰማት መሆን ይኖርባት ይሆናል።

ጨለማ በጊዜ መጥቷል፣ ንፋሳማ በሆነው ጨለማ ጋደም ብለው ለመተኛት ሞከሩ፣ ነገር ግን አውሎ ነፋሱ ከባድ እየሆነና እያየለ መጣና በድንኳኑ ችካሎች መካከል ነፋሱ እያፏጨ አቧራውና ብናኝ ነገሮች መኝታቸው አጠገብ ተቈለለ። ድንኳኑ ከላያቸው ላይ ይነሣ እንደ ሆነ ወይም ይቆይ እንደ ሆነ በመገረም፣ በከፊል ታፍነው፣ በብርድ ልብስ ተሸፍነው ጋደም አሉ።

እኩለ ሌሊት ሆኖአል። ጩኸትና ፉጨቱ አቁሞአል፣ አንድ አጭርና አስጨናቂ ጸጥታ ነበር። ከዚያም፣ በፍጥነት ደብ ደብ የሚሉ የዝናብ ጠብታዎች ደረቁን ምድር ወደ ጭቃነት እየናጡ፣ የቆሻሻ ቦዮችን እያጥለቀለቁ፣ በድንኳኑ ክዳኖች ሥር እየሰረጉ በድንኳኑ ግድግዳዎች ላይ ዝናቡ በዶፍ መልክ ይወርድ ጀመር። ወላጆች በጨለማ ተነሥተው ልጆቻቸውን በክንዶቻቸው አድርገው ማለዳውን በጸሎት እየጠበቁ እርጥብ በሆኑ የምግብ ጆንያዎቻቸው እና በብርድ ልብሶቻቸው ላይ ተቀመጡ።

ለብዙ ቀናት ማለዳዎቹ ብሩህ እና የሚያንጸባርቅ ፀሐያማ ነበሩ፣ ነገር ግን በየከሰዓት በኋላው ዝናቡ በጣም በመዝነቡ ጕርፉ ሜዳውን በማጥለቅለቅ ወደ ጭቃ ባሕርነት ለወጠው። አንድ ስፍራ ሙሉ በሙሉ የተጥለቀለቀ በመሆኑ በድንኳን የሚኖሩ ሁሉ ቀድሞውኑ በጕረቤቶቻቸው ተጨናንቆ ወደ ነበረው ስፍራ ለቅቀው መንዝ ነበረባቸው። ነገር ግን ልጆቹ ወደዱትና በቆሻሻ እና በተ በከለው ውኃ ከመጫወት ማንም ሊያስቆማቸው አልቻለም ነበር። ቦታው በአዳሪና የተጥለቀለቀና ቆሻሻ ነገሮች የሚንሳፈፉበት መጥፎ

ቦታ ነበር።

ምሕረት እና ተክሌ በየማለዳው በተቋጠረ ውኃ በኩል ወደ መመገቢያው ጣቢያ ውኃ እየተራጩ መሄዱን ቀጠሉበት። ነገር ግን ምሕረት በዚያ የሚኖራቸው የቆይታ ጊዜ በቁጥር እንደ ሆነ አውቃለች፤ ተክሌ ምንም እንኳ አሁንም የመነመነ እና አጥንቱ የሚታይ ከሲታ የ4 ዓመት ልጅ ቢሆንም፣ በፍጥነት እየተሻሻለ ነበር። ደግሞም በቅርቡ ተጨማሪ ምግብ የሚያስፈልገው ይሆናል። ስለዚህ ራስዋን ለኤማ አስፈላጊ ለማድረግ እየጣረች፣ በቅርቧ ለመሆን ደስተኛ እና አንዳንድ ጊዜ ፈገግታዋን ለማየት እየፈለገች በቻለችው መጠን ሁሉ ጠንክራ ትሠራ ነበር። አንድ ጧት ዝናቡ ማቆም እየጀመረ ሳለ፣ በድንገት ኤማ ፈገግ ማለቷን አቆመች። አመድ ቡን ባለበት ፊት ወደ ማዕከሉ መጣች ደግሞም ምሕረት ከቶ በዚያ መሆንዋን ለማረጋገጥ የተቸገረች በመምሰል በዚያ ደረሰች። ከጊዜ ወደ ጊዜ ሌሎች ሠራተኞች በመምጣት ላይ ነበሩ። ፊቶቻቸው ገርጥተው እና ደስታ አልባ ሆነው ሳለ ዝቅ ባለ ድምፅ ይናገራሉ። ምሕረት ለኤማ ጥያቄ ባቀረበችላት ጊዜ፣ ረጋ ብላ መለሰችላት፣ ነገር ግን ፈገግ አላለችም ነበር። ከዚህ በኋላ ከቶ ፈገግ የማትል ትመስል ነበር።

አንድ ነገር እየሆነ ነበር። የዚህም አንዱ መገለጫው የሆነ መጠለያ ከድንኳኖች እና ከማዕከሉ ውጭ ርቆ በችኮላ ይሠራ ነበር። በካምፑ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ሁሉ በሥራው ላይ የተሳተፉ ይመስል ነበር። ምሕረት ለምን በእንደዚህ ያለ ችኮላ ውስጥ እንደ ገቡ በመደነቅ ትመለከት ነበር፤ ነገር ግን ከመጨረሱ በፊት እንኳ፣ ገና በከፊል ጣሪያው በተሠራበት ሁኔታ፣ ሁለት ሕሙማን እየተገፉ በሚወሰዱበት ጋሪ ወደዚያ አዲስ መጠለያ ተ ሻግረው ተወሰዱ። ከእርሷ ጋር የቆሙ ልጃገረዶች እርስ በርስ ተ ያዩ። «ይህ የሚሰራጭ በሽታ ነው፣» ሲሉ አንሾካሾኩ። «ራቅ ወዳለ ስፍራ እየወሰዱዋቸው ነው።»

በሚቀጥለው ማለዳ፣ ምሕረት ወደ መመገቢያው ጣቢያ በሄደች ጊዜ፣ ኤማ በዚያ አልነበረችም፣ ቀኑን ሁሉ አልመጣችም ነበር። ምሕረት በዚያ የሚሠሩ ሰዎችን በጠየቀቻቸው ጊዜ ኤማ በሌላ



ስፍራ እየሠራች መሆንዋን ነገሩዋት። ማንም ሰው ከዚህ ያለፈ ነገር አልነገራትም፣ ነገር ግን ጭምጭምታዎች ይነሡ ደግሞም ሰ ዎች ይፈሩ ነበር። ቀን በቀን ወደዚያ ገደቢስ አዲስ መጠለያ ብዙ ብዙ ሰዎች ሕሙማን እየተገፉ በሚወሰዱበት ጋሪ ተጭነው ሲወሰዱ፣ በቡድን ቀጥጢጥ ብለው የተደናገጡ ሰዎች የማሆነውን ይመለከቱ ነበር። አሁንም ትንሽ ቆይቶም ሙታን እንኳ የሚበከሉ ይመስል አንድ ሰው ራቅ ብሎ ወደ ተቆፈረው የመቃብር ስፍራ ይወስድ ነበር። ምሕረት ምንም ጥያቄ ሳትጠይቅ በኀዘን ደንዛዛ ወጥታ ሄደች፣ ምክንያቱም መልሶቹን ልትሸከማቸው አትችልም ነበር። ኤማ ጠፍታ ስለ ቀረች፣ በእርግጥም ኤማ በበሽታው ተ ይዛለች። ምናልባት ማንም ሰው ወደዚያ እንዲሄድ ወደ ማይፈቀድለት ሩቅ ወደ ሆነ ስፍራ በድንጋይ ክምር ሥር ተኝታ ይሆናል።

አንድ ምሽት ላይ ምሕረት ሕመም ስለ ተሰማት ለመተኛት ጋደም አለች። ጊዜው ገና ማለዳ ነበር፤ ተክሌ ከአጠገብዋ ሆኖ ያጉ ረመርም ነበር፤ ምክንያቱም ለመጫወት ወደ ውጭ እንድትወስደው ይፈልግ ነበር። ነገር ግን እርሷ ልብ አላለችውም፣ ምክንያቱም ሆድዋ ጭብጥ አድርጎ ይዟታል፣ ደግሞም በጣም ብርድ ይሰማት ነበር። የካህኑ ሚስት ተነሥታ ራት እንድታዘጋጅ ነገሯት፤ ነገር ግን፣ እርሳቸውም እንደዚሁ ልብ አላሏቸውም። በጐንዋ ተገላበጠች፣ እንዲሁም ጉልበቶችዋን አኮራመተቻቸው። ከዚህ ወዲያ ማንም የሚናገራትን መስማት እስከማትችልና ግድም እስከማይላት ድረስ ሁሉም ነገር እጅግ ሩቅ የሆነ ይመስል ነበር። ከዚያም ከበላይዋ እንግዳ የሆኑ ድምፆችን ሰማች፣ ነገር ግን ቋንቋቸውን ልትረዳቸው አልቻለችም ነበር። አንድ ሰው በአጠገብዋ በጉልበት ተንበርክኮ፣ ይመረምራት ነበር።

«አዎን፣ ይህ ሌላ የኮሌራ በሽታ መከሰት ነው።» ምሕረት እየተናገረው ያለው ወጣቱ ዶክተር ፒተር እርሱ እንደ ነበ ረ አውቃለች። «ሕሙማን የሚወሰዱበትን ጋሪ አምጡ እና በተቻለ መጠን እርሷን ከዚህ አውጧት፣ ደግሞም መተኛዋን ጭምር አውጡ። እንዲሁም ያን ሕፃን ልጅ ወደ አንድ ስፍራ ውሰዱት።»

በሚወለድበት ጊዜ ተክሌ ሲያሰቅስ እንዲሁም እርሷ ሕሙማን መግፊያ ጋሪ በምትወጣበት ጊዜ መስማት ትችል ነበር። የድንኳኑን ጨለማ ካለፉ በኋላ፣ ወርቃማው የምሽት ብርሃን ልክ እንደ ስይፍ መታት፣ ነገር ግን ከዚህ በኋላ ፋይዳ ያለው ነገር አልነበረም። መላው ሰውነትዋ ከውስጥ ወደ ውጭ የወጣ ይመስል ነበር፣ ደግሞም ስለ እርሱ ምንም ልታደርግ አትችልም ነበር። ለብቻዋ እንድትሆን ተደርጋለች፣ ደግሞም ለረጅም ጊዜ በዚሁ የሚቀጥል ይመስል ነበር፣ ከዚያም ጨለማ ነበር ማለት ይቻላል ወደ አዲሱ መጠለያ እየተወለደች እንደ ሆነ አወቀች። ወዲያውም፤ ራቅ ባለ ስፍራ ላይ ወዳለው መቃብር ተሸክመው እንደሚወስዷት ደግሞም ተክሌ ብቸኛ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር አልነበረም። ነገር ግን ምንም ልታደርገው አትችልም፤ ምንም ነገር ለማድረግ በማትችልበት እጅግ ከፍተኛ ድካም ውስጥ ነበረች።

አንድ ሰው በአልጋዋ ላይ በጉልበቱ ተንበርክኮ በክንዷ ላይ መርፌ ይተክል፣ ከንፈሮችዋን ያረጥብ፣ እንክብካቤም ያደርግላት እንዲሁም ያጥባት ነበር። እርሷ ግድ አልነበራትም። የወደዱትን ሁሉ ማድረግ ይችሉ ነበር። ከዚያም አንድ ድምፅ፣ «ምሕረት፣» አለ፣ ደግሞም እርሷ ያንን ድምፅ አስታወለችው። በብዙ ጥረት፣ ዓይኖችዋን ከፈተቻቸው።

ኤማ ጭንብል እና ነጭ ባርኔጣ አድርጋ በአጠገብዋ ነበረች፣ ነገር ግን እነዚያን ቡናማ ዓይኖች የትም ስፍራ ታውቃቸው ነበር። ለተክሌ ሲባል፣ ከምንም ነገር በላይ ለመኖር ወስና ነበር።



# 16

ተስፋዬ ወረቀቶቹንና የመንጃ ፈቃዱን አግኝቶ ለቻርሊ የሙሉ ጊዜ ረዳት ሆኖአል። በተለያዩ ዝርያዎች መካከል እንዲሁም የተለያዩ ቅድመ ታሪክ (አኗኗር) ያላቸው ሰዎች በመከራ ውስጥ በሚገናኙበትና በአንድ ፕሮጀክት ላይ በጋራ በሚሳተፉበት ጊዜ፣ ዘወትር እየጐለበተ የሚሄድ ጥልቀት ያለው ጓደኝነት በመካከላቸው እየተፈጠረ መሆኑ እየተሰማቸው፣ ሁለቱም ደስተኞች ነበሩ። ተስፋዬ በዚህ የለቆቃ እና የጥፋት ዓለም ውስጥ ጥቂት ደስታ የተረፈ መሆኑን በሚያረጋግጥለት በዚህ ወጣት ሳቅ እና ደስታ ምክንያት ቻርሊን ወድዶታል። በተጨማሪም የእርሱን ተጋላጭነት ተገንዝቦ ነበር። ቻርሊ በዙሪያው ስላለ ሕይወት እና ባህል የሚያውቀው እጅግ ኢምንት ነበር፣ አንድ ስሕተት ቢፈጠር ምን ማድረግ እንዳለበትም አያውቅም ነበር። ጠረፉን መሻገር እስከሚቻል ድረስ፣ ተስፋዬ ከቻርሊ ጋር ይቆያል።

ቻርሊ ስላለው የመካኒክነት ክህሎት፣ ነገር ግን ከዚህ በበለጠ ስላለው የጠለቀ ዝግጅት፣ ተስፋዬን ያደንቀዋል፤ ያከብረዋልም። ቻርሊ አብዛኞቹን ነገሮች ወደ ቀልድ መለወጥ እና በሳቅ እንድትንከተከት የሚያደርጋትን ደብዳቤ ለሴት ጓደኛው መጻፍ ይችል ነበር። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ፣ በተለይ በምሽት ወይም ፀሐይ በምትጠልቅበት ጊዜ ቀልዶቹ በጨለማ ስፍራ ጨለማውን ለመደበቅ ችፍግ ብለው እንደ ተኰተቱ መጋረጃዎች መሆናቸውን ያውቃል። ኀላፊነት የሚጠይቅ ሥራ ይዞአል ደግሞም ነገሮች በመጥፎ ሁኔታ ይጓዙ ነበር - እነዚያ በከፊል ርሃብተኛ የሆኑ ትናንሽ ሕፃን ልጆች፣ የምግብ አቅርቦቱ ያልቃል የሚለው ሥጋት፣ ዝናቡ በሚመጣበት ጊዜ ስለ እነዚያ የበረሃ መንገዶች የሚሆን ሥጋት፣ ደግሞም ዝናቡ ካልመጣ የባሰ ስለሚሆንበት

ሁኔታ. . . ነገሮች የከፋ አድርጓቸዋል። ቻርሊ በምዕራብ ዓለም ያሉት በሚሊዮን የቈጠሩ ሰዎች ራሳቸውን አጨናንቀው ከዚያም አመጋገባቸውን በማስተካከል ክብደታቸውን ለመቀነስ የሚጨነቁበትን ሁኔታ እያሰበ ሳለ ራሱን አነቃነቀ። በዓለም ላይ ምን ዓይነት ችግር እንደ ተፈጠረ ማወቅ አልቻለም። ቀልዶች እርሱ ነገሮችን የሚያልፍባቸው መንገዶች እንደ ሆኑ ይገምታል። ነገር ግን ተስፋዬ አይስቅም ወይም አይቀልድም ነበር። ብዙ ፈገግ እንኳ አይልም፣ ምክንያቱም በአሁኑ ሰዓት በትክክለኛው ሰቆቃ ውስጥ ስላለፈ እና ከዚያም የወጣ ስለሆነ ነው። ምንም ነገር ቢከሰት፣ ተስፋዬ ሁልጊዜ ምን መደረግ እንዳለበት ያውቃል። ቻርሊ ከጎልማሳው ተስፋዬ ጋር በመሆኑ ምክንያት ከሥጋት ነፃ መሆን ይስማዋል።

ስለዚህም፣ ጭነታቸውን ካራገፉ እና ግምጃ ቤቶቹን ከቃኙ በኋላ በክፍለ አገር ወዳሉ ወደ ተለያዩ ካምፖች መኪናቸውን እየነዱ ሄደው የምግብ አቅርቦት ያደርጋሉ። ደግሞም በጠንካራ ሥራ፣ በጓደኝነት እና ጸጥ ባለ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ በሚደረግ ሹፈራ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ፣ የተስፋዬ ጥንካሬ ተመለሰ ደግሞም የዝናቡ ወቅት ፈታኝ ነገሮች እና አደጋዎችን ለመጋፈጥ ዝግጁ ነበር። በአንድነት ሆነውም ከጭቃ ውስጥ መኪናውን ያውጡታል፤ አንዳንድ ጊዜ ሳይሳካላቸው ይቀርና ጭነቱን ለማቅለል ይጥራሉ፤ ወይም በጐማዎቹ ፊት ለፊት የሚነጠፍ ነገር ያደርጋሉ፣ ይሁንና በጭቃ ተሸፍነው ሁልጊዜ ወዳሰቡት ስፍራ ይሄዳሉ፤ ነገር ግን በመልካም መንፈስ ነው የሚደርሱት። ነገር ግን በምድር ላይ ባለ መንገድ መጓዝ የማይቻልባቸው ጊዜያት እና ምንም ሥራ ሊሠራባቸው የማይችሉ ሁኔታዎች ነበሩ። ከዚያም ተስፋዬ አዲስ ኪዳኑን ይዞ ተመልሶ ይስሐቅ ወዳለበት ሄደ፣ ይኸውም ምናልባት ነፃ የምሆንበት ዕድል ካለ በሚል ተስፋ ነበር።

መጽሐፉን በቀጥታ አንብቦ ጨርሶታል፣ ነገር ግን ወደ ኋላ ደግሞ ደጋግሞ ሕይወት-ለዋጭ ወደ ሆነው ወደ ትንሣኤው ታሪክ ተመልሶ አንብቦታል። በታሪኩ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በላይኛው እዳራሽ ያደረገው ንግግር የመክፈቻ ቃላት



ልቡን ነክተውታል። «ስለ ምን ትፈራላችሁ? . . . እጆቼን እና እግሮቼን ተመልከቱ . . .» እርሱ የይስሐቅን ቃሎች አስታወሰ። እርሱ ምንድን ነበር ያሰው? ልክ እንዲህ የሚመስል ነበር፦ «ለእጆቹ የምታስረክበው ነገር ከቍስሎቹ ጋር የሚገናኝ ይሆናል። በፍቅሩ ያጥበዋል . . . ከእርሱም ውስጥ ውድ የሆነ አንድ ነገር ያወጣል።» ተስፋዬ እስከሚያውቀው ድረስ፣ ሕይወቱን፣ ልጆቹን የአሁንና የወደፊት ዘመንና ኑሮውን ሁሉ ለእነዚህ እጆች አሳልፎ ሰጥቶአል፣ ለሳምንም አግኝቶበታል። እጅግ ብዙ ነገሮችን ያጣ በመሆኑ በቀላሉ፣ «እኔ እና ያለኝ ነገር ሁሉ የአንተ ነው» ማለት ለእርሱ ከባድ አልነበረም።

ነገር ግን ሙሉ በሙሉ የሆነ መሰጠት ኀላፊነት መውሰድን፣ ታማኝነትን እና ማገልገልን እንደሚያካትት መገንዘብ ጀምሮአል፣ ደግሞም በዚህ ጉዳይ ላይ አሁንም ገና እየታገለ ነበር። «. . . ክርስቶስ ለሁላችንም ሞቶልናል» የሚለውን ጥቅስ ይስሐቅ አሳይቶታል። «እርሱ የሞተው እኛ ለእራሳችን እንዳንኖር፣ ነገር ግን ስለ እኛ ለሞተውና ለተነሣው ለእርሱ እንድንኖር ነው።» ነገር ግን ተስፋዬ ያንን ጉዳይ በዝርዝር ማጥናት እና ማወቅ ይኖርበታል። በመጠለያ ውስጥ፣ በከባድ መኪና ውስጥ፣ በጭቃ መንገድ ላይ እና ከቻርሊ ጋር ባለው በጣም የተወሰነ ንግግር ብቻ በሚያደርግበት ሁኔታ ውስጥ ከሙታን ለተነሣ ጌታው እንዴት ሊኖርለት ይችላል? የተራዘመ ኀዘን እና ረሃብ የማስታወስ ችሎታውን ያቃወሰው ይመስል ነበር፤ ደግሞም ተምሮት የነበረውን እንግሊዝኛ አብዛኛውን ረስቶት ነበር።

ይስሐቅ አንድን ቀን በየተራ እንዲኖርበት ነግሮታል። ወደፊት፣ ተመልሶ ሊሄድና መልእክቱን ለገዛ ሕዝቡ ሊነግራቸው ይችላል። በመሀሉ፣ የኢየሱስን ትእዛዛት ለመጠበቅ ይችላል፣ ደግሞም አሁን በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሰጠው መገንዘብ የቻለውን የኢየሱስን ሕይወት ለመኖር ፈለገ። ስለዚህ አዲስ ያገኘውን ፍቅር ወደ ሥራውና ወደ ከባዱ መኪናው እንክብካቤ አፈሰሰው። በታማኝነቱ፣ ራስ ወዳድነት በሌለበት ትዕግሥቱ፣ ጥብቅ በሆነ ሰዓት አክባሪነቱ ይልቁንም፣ በቀላሉ የማይታየው በቅዱስ ሰው

መካከል የሚኖር መሆኑ ቻርሊን አስደነቀው::

«መጥፎ ዕድል ነው፣» በማለት ሰንደኛው አወያየው:: «አንድ ጊዜ ከተቈጣ፣ ከጠጣ፣ ወይም አንድ ጉዳይ ወይም አንድ ነገር ካሰው ጥሩ ስሜት ይሰማኛል:: እኔን እንኳ የሚረብሸኝ ነገር ነው! በሌላ ቀን ተስፋዬ አጠገቤ እስካለ ድረስ ምንም ዓይነት የስድብ ቃላት መሰንዘር እንደማይኖርብኝ ተረድቻለሁ::»

ቀናቶቹ ወደ በጋው አጋማሽ እየገፉ ሄደዋል:: ቀደም ብለው የዘነቡ ታላላቅ ዝናቦች ለአንድ ሳምንት ያህል አካባቢ ዘንበው አልፈዋል፣ ደግሞም ፀሐይና ንፋስ መንገኛ መንገዱን እያጠነከሩት ነበር:: «በመካከለኛው ካምፕ ኮሌራ ተነሥቶአል የሚለውን አሁን ሰማን፣» አለ ቻርሊ በማለዳ:: «ፈጣን የሆነ የመድኃኒት አቅርቦት ይፈልጋሉ:: ከምሳ በኋላ ሁላችንም እንሄዳለን፣ ተስፋዬ፣ እሺ?»

«እሺ፣» አለ ተስፋዬ:: «ዕቃ በመጫን እረዳሃለሁ::»

ጊዜው ብሩህ የሆነ ከሰዓት በኋላ ነበር፣ ደግሞም ቻርሊ በፍጥነት ይነዳ ነበር:: በበረሃው መንገድ አንድ ጊዜ በዝግታ ይጓዙ ነበር፣ ምክንያቱም ለስላሳው መሬት መንዳትን አስቸጋሪ አድርጎት ነበር፣ ነገር ግን ቻርሊ ትልሙን አድበስብሶ እና በተቋጠረ ውኃ ዙሪያ መንገድ ለውጦ መጓዙን እየተደሰተበት ነበር:: ድንኳኖቹ መታየት በቻሉበት ጊዜ፣ ቻርሊ ጸጥ አለ:: ለብቻቸው ወደ ተሠራው ታላቅ መጠለያ በትኩረት ይመለከት ነበር::

«እዚያ ስፍራ ላይ ሕክምና እየሰጡዋቸው እንደ ሆነ እገምታለሁ፣» አለ «ደግሞም አንዳንዶች ሞተዋል አሉ:: ከሚያስፈልገን ጊዜ በላይ እዚህ መቆየት አይኖርብንም:: ወደ ግምጃ ቤቱ እንሂድና ዕቃውን እናራግፍ::»

በግምጃ ቤቱ ጀርባ በኩል አድርጎ አሽከረከረ፣ ደግሞም ኩርባውን ሊያደርገው ከሚገባው በላይ በሆነ ፍጥነት ታጠፈ፣ እንዲሁም በአንድ ሰከንድ ውስጥ ይህን አከናወነው:: ትንሽ ሕፃን በድንገት ከተከመሩ ካርቶኖች ውስጥ ወጥቶ ከበስተኋላ እየሮጠ ወጣና ከመኪናው ሥር ገብቶ ተሰወረ:: ቻርሊ ራሱን እና ተስፋዬን



ከመኪናው ፊት መስኮት እስኪላተሙ ድረስ፣ ባለው ኃይል ፍሬኑን ያዘ፣ አንዲት አሮጊት ሴት ከፍ ባለ ድምፅ ጮኸ:: ቻርሊ «የለም፣ አይደረግም!» እያለ የሲቃ ድምፅ አሰማና:: ጭንቅላቱ በቀጥታ ወደ መሪው ተቀረቀረ:: ቻርሊ እንደ ገና ሲቃ ባለው ድምፅ:: «ተ ስፋዬ፣ ተስፋዬ!» አለ::

ተስፋዬ የታመመ እና ራሱን የሳተ መስሎ እየተሰማው ከመኪናው ውስጥ ዘልሎ ወጣና አንሶላ መሰል ልብስ የለበሰ ሕፃን ልጅን ጐትቶ ለማውጣት ብሎ በእጆቹ እና በጉልበቱ ተንበረከከ:: ከሞተሩ በታች ብቅ አለ፤ የሚያስደነግጥ፣ አጥንቶቹ የወጡ ፊትን እንዲሁም በመሰኪያቸው ላይ የሰጠሙ ሁለት ጥቁር ዓይኖችን ተ መለከተ:: ልጁ አልተገጨም ነበር:: እርሱ በሁለቱ ጐማዎች መካከል ወድቆ ነበርና አሁን እየተንፏቀቀ ለመውጣት በሂደት ላይ ነበረ:: ወደ እርሱ የሰው ፊት ቀርቦ በተመለከተ ጊዜ ልጁ እንቅስቃሴውን አቆመና የሰውዬውን ፊት ትኩር ብሎ ማየት ጀመ ረ::

ተስፋዬም እንደዚሁ ትኩር ብሎ ልጁን ተመለከተው:: ነገሮችን ያይ ስለ ነበር፣ የግንባሩ እብጠት በመጥፎ ሁኔታ ሳይጐዳው አይቀርም:: በደንብ በአእምሮው አልነበረም:: እኛ አሮጊት ሴትዮ ሰጊዜው መጮኻቸውን ቢያቆሙ፣ ምናልባት ነገሮችን አስተካክሎ ይመለከታቸው ይሆናል:: ለቻርሊ ሁሉም ነገር ደኅና እንደ ሆነ ሊነግረው ሲገባ በጭቃ ላይ መጋደም ሞኝነት ነበር፣ ነገር ግን ይህን ማቆም አልቻለም:: ከዚህ በኋላ በጭቃ ውስጥ የተኛ ፍጹም አልመሰለም፤ በተራራዎች ላይ ወዳለው ቤቱ ተመልሶ ሄደና ትንሽ ልጅ እርሱን ለማግኘት በእነዚያው የቀድሞዎቹ ዓይኖች እያየና ፈገግ እያለ እየሮጠ መጣ::

«ተክሌ!» ሲል አንሾካሾከ እና ጎትቶ አወጣው:: በመንገዱ አጠገብ ተቀመጠና በጭቃ የተለወሰውን ደግሞም በግራሶ የተ ጨማለቀውን ትንሹን ልጅ በጭኑ ላይ አስቀመጠው:: «ተክሌ፣» አለ እንደ ገና:: «ምሕረት ያለችው የት ነው?»

«ታምማለች፣ ወደዚያ ወስደዋታል፣» አለ ተክሌ፣ ነገር ግን

በመገረም ነበር እየተናገረ ያለው። ለረጅም ጊዜ አለመስያየታቸው እውነት ነበር፣ ነገር ግን በቂ የሆነ ሩቅ ጊዜ ነበር፤ ደግሞም በዚያ ጊዜ፣ እጅግ ብዙ ነገሮች ተከሰቱ። ነገር ግን አሁን ትውስታ እየተነሣሣ ነበር . . .

ተክሌ የእርሳቸው እንደ ሆነ የሚያስቡት አሮጊት ሴትዮ ጨዋኸት ባይኖር ኖሮ ምናልባት ትኩር ባለ እይታ እየተያዩና ሙሉ በሙሉ ተቃቅፈው ለረጅም ጊዜ ይቆዩ ነበር። ከመኪናው ውስጥ ዘልሎ የወረደው ደግሞም አመድማ ፊት ያለው ቻርሊ ተክሌ የአሮጊትዋ ልጅ መስሎት ነበር።

«በእውነት እርሱ ደኅና ነው?» ሲል ጠየቀ እየተንቀጠቀጠ።

ተስፋዬ ወደ እርሱ መለስ አለ ደግሞም አሁን በእውነት ፈገግ እያለ ከጆሮው እስከ ሌላኛው ጆሮ በሚታይ ፈገግታ ነበር።

«ይህ ልጅ ነው፣ አለ» «ደግሞም በጣም ደኅና ነው።»

***

ምሕረት ከመጠለያው እንድትወጣ ከመፈቀዱ በፊት አሥራ አምስት ቀን ሙሉ አልፎ ነበር። በእርግጥም በጣም ታምማ ነበር፣ ደግሞም ትከታተላት የነበረች ነርስ ልትሞት ነው ብላ ያሰበችበት ጊዜም ነበር። አሁን የከፋው ነገር አልፏል፣ ነገር ግን እንደገና እንደ በፊቱ ለመሆንና ለመንቀሳቀስ ኃይሏ አልተመለሰላትም ነበር። ተክሌን ትወድደው ስለ ነበር፣ አሁንም በጣም ስለምትወድው ሕይወትን የሙጥኝ አለች፤ ነገር ግን በዚያን ጊዜ ለእርሱ ያላት አሳብ ራሱ በድካም እንድትሞት አስመኛት። ከዚያም፣ እንቅስቃሴ - አልባ ሆና አንድ ከሰዓት በኋላ ጋደም ብላ ሳለ፣ ኤማ መጣች፤ ዓይኖችዋ ያበራሉ ደግሞም ሙሉ በሙሉ በደስታ ተፍለቅልቀው ነበር፤ ደግሞም በአስተርጓሚ አማካይነት፣ አባትዋ ተመልሶ መምጣቱን ነገረቻት።

ምሕረት በጣም ደክማለች፣ ደግሞም የመጀመሪያ ምላሽዋ ለእናትዋ ማልቀስ ነበር፤ ነገር ግን የመጀመሪያው የኀዘን ልቅሶ እንዳለቀ፣ ቀስ በቀስ እርስዋ አባት ያላት የመሆኑ ጉዳይ ወደ



ውስጥዋ እየዘለቀ ይገባ ነበር፣ ደግሞም ዜናው በተሻለ ወቅት ሊመጣ አልቻለም ነበር። ጋደም ብላ፣ በበሩ በኩል ፀሐይዋ የሸፈነችውን ርቀት እንዲሁም ሰማያዊውን ሰማይ ትኩር ብላ ትመለከት ነበር፤ ደግሞም ለተክሌ ኃላፊነትን የመውሰድ ወይም የመጨውን ጊዜ በተመለከተ ነፃ መሆንዋን ታውቅ ነበር። ለመኖር የሚደረግ ትልቁ ግጭት አለፈ፣ ደግሞም ይህ በሚሰጠው ሰላም ዘና አለች። እየሮጠ ያለው የልቧ ምት ቀነሰ፣ ፈጣን የሆነው ትንፋሿ ዝግ እለ እና አንቀላፋች።

ትከታተላት የነበረች ነርስ ለኤማ፣ «በጣም እየተሻላት ነው። ያሰበችውንም ነገር ልታደርገው ነው» አለቻት።

ቻርሊ በሆነው ነገር ተደነቀ፣ ደግሞም ለዚህ ከአእምሮ በላይ ለሆነ መገናኘት እርዳታ እንዳደረገ የሚያስብ ይመስል ነበር። ምሕረት ከመጠለያው የምትለቀቅበትን ቀን ተረዳ፣ ደግሞም ወደ ሰሜናዊ ካምፕ የሚደረገውን ጉዞ አዘጋጀ። ወደዚያም እየሄዱ፣ ተስፋዬን በመካከለኛው ካምፕ ያወርደውና ወደ ቤት በሚመለሱበት ጊዜ ይወስደዋል። ደግሞም ተስፋዬን ሊሄድና ከሕፃናት ልጆቹ ጋር በካምፑ ውስጥ ሊኖር ይመርጥ እንደ ሆነ እንኳ ጠይቆታል፤ ደግሞም የእርሱን ምላሽ ለማግኘት በሚያጓጓ ትንፋሽ ጠብቆት ነበር። ነገር ግን፣ ተስፋዬ ቻርሊ ሕፃናት ልጆቹ ሲል ሕፃናት ልጆች ለማለት እንዳልፈለገ ወዲያው ተረድቶታል፣ ራሱን ነቀነቀ። ለልጆቹ ሲል መሥራቱን እንደሚመርጠውና ወደ ቤት የሚመለሱበትን ገንዘብ ማጠራቀም እንደሚፈልግ ተናገረ።

ደግሞም ታላቁ ቀን መጣ። ምሕረት፣ ልክ ሕይወት ያላት ዐፅም መስላ፣ ከመርዙ ነፃ በመሆን ተፈወሰች። ነገር ግን ኤማ በድጋሚ አንድ ላይ እንዲሆኑ የግል ፍላጎትዋን አሳየች፣ ደግሞም ለእርስዋ ከአሮጌ ልብሶች መካከል ሰማያዊ ልብስ እንዲሁም ከሞላ ጐደል ከእርሱ ጋር የሚመሳሰል (አብሮ የሚሄድ) ሰማያዊ የጠጕር ማሰሪያ አገኘችላት፤ ደግሞም ምሕረት በእራፊ ጨርቅ ላይ ተቀምጣ ዙሪያዋን ትመለከትና እንዲሁም በጣም ቆንጆ መሆንዋ ይሰማት ነበር። የሚያቃጥለው ሙቀት አሁን የለም፣ ደግሞም በሕመምዋ ጊዜ፣ ምድር ዝናብ አግኝታ ነበር፣ ደግሞም ከአድማስ

እስከ አድማስ ምድሪቱ አረንጓዴ ነበረች። ከዚያም ተክሌን በክንዶቹ ይዞ አባቷ ከማዕከሉ ሲወጣ ተመለከተችው ደግሞም ሰላምታ ልትሰጠው ለመነሣት ሞከረች፣ ነገር ግን ለመነሣት እጅግ ደካማ መሆንዋን ተረዳችው።

ለረጅም ጊዜ በአንድ ላይ ተቀመጡ፦ ተክሌ፣ እርሱና አባቱ ከቶ ተለያይተው እንደማያውቁ ደስተኛና እምነት የሞላበት ሆኖ ይታያል፤ ምሕረት፣ አፍራና ጥቂት ገለል ብላ ነበር፣ ምክንያቱም ይህን ሰው ከዚህ ቀደም ማንም አያውቀውም ነበርና። የሕይወት ዘመን ኀዘን ተጨምቆ በአምስት ወራት ውስጥ የተከሰተ ይመስል፣ እርሷ አድጋለች፣ እርሱ ደግሞ እያረጀ ነው። እንደገና መተዋወቅ ሊኖርባቸው ነው፣ ነገር ግን በዚያ የከሰዓት በኋላ ጊዜ ይህን መተዋወቅ ጀምረውታል።

«አባ፣» አለች ምሕረት፣ «ወደ ቤት የምንሄደው መቼ ነው?»

ቁጭ ብሎ ነገሮችን አሰላሰለ። «ይህም በዚህ ክረምት አይደለም፣ ልጄ» አለ፤ «ለመከር እጅግ ዘግይተናል ደግሞም በእግር ለመጓዝ አንቺ እጅግ ደካማ ነሽ። ተመልሰን ወደ ከተማው አንሄድም። በጊዜ ለማረስ እና የበልግ ዝናብ ከመምጣቱ በፊት ለመዝራት ወደ አያትሽ እርሻ እንሄዳለን። ብዙዎቹ፣ እጅግ ብዙ የሚሆኑ ሰዎች አብረውን እንደሚሄዱ አምናለሁ፦ ዘር እና በሬዎች ለመግዛት እየሠራሁ ገንዘብ አጠራቅማለሁ። የተበላሸውን ነገር እንደገና እንጠግናለን ደግሞም ባዶ የሆኑትን መሬቶች በአትክልት እንሸፍናለን።»

ምሕረት ፈገግ አለች። ከመጀመራቸው በፊት ያለው ሌላ ተጨማሪ የስድስት ወር ጊዜ ነበር፣ ነገር ግን እርሷ መቆየትን ተምራለች። ፍቅሬ፣ «ወደ መንደሩ እመጣና እፈልግሻለሁ» ብሏታል። ደግሞም ቃሉን እንደሚጠብቅ እርሷ ታውቅ ነበር። እርሱ አስተማሪ ይሆናል፣ ደግሞም ከእርሷ ጋር በአንድነት የተበተነውን ማኅበረሰብ ያደራጃሉ። ትልቅ የሆነውን የጦርነት፣ የረሃብ እና ተጨማሪ የድርቅ አደጋዎች ማሰብን አትፈልግም። ተስፋ ማድረጊያውና ማንኛውንም ነገር መጀመሪያው ጊዜ ይህ ነው።



በየትኛውም መልኩ፣ የእርሷ የሆኑ ኀላፊነቶች አልነበሩም፤ እርሷ አባት ያላት ነበረች።

ለረጅም ጊዜ ለመነጋገር እጅግ ደካማ ናት፣ ቻርሊ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ፣ በዙሪያቸው ያለውን ንጹሕ አየር እና አረንጓዴ ተክሎች በመመልከት ደስ እያላቸው ምቾት ባለው ጸጥታ ውስጥ ተቀመጡ። ተስፋዬ ደግሞ የወደፊቱን በተስፋ ይመለከታል። ያደገው በእርሻ ውስጥ ነው፤ የሙቀቱን የመፈራረቅ ዑደትን እና የሰብሎችን አስተዳደግ ሁኔታ ያውቃል፣ ደግሞም በመስኖ እና እርከን በመሥራት የሚደረገውን አዲሱን ሳይንስ በመጠለያ ካምፑ ውስጥ ካሉ ከገዛ ሕዝቦቹ የሚማረው ይሆናል። ነገር ግን የዘር እጥረት እንዳለ እና አንድ በሬ ብዙ ዋጋ እንደሚጠይቅም ጭምር ያውቅ ነበር።

ጦርነቱ እንዳላበቃ ደግም በተራራዎች ላይ ያሉት ሽምቅ ተዋጊዎች ተስፋ እንዳልቈረጡ ያውቃል። የጠላት አውሮፕላኖች ብዙ ጥቃትን በማድረግ መንደሮችን እያጠፉ አሁንም አሁንም ደጋግመው ይመላለሳሉ።

ምናልባት በየትኛውም ወቅት ዝናቡ እንደገና ሊጠፋ እንደሚችል ያውቃል፤ በየትኛውም ዓመት ትላትሎች እና ነፍሳቶች ሊያጠቁ እንደሚችሉ ያውቃል።

የምዕራባውያን እርዳታ /ልገሣ/ የማይተማመኑበት ወይም የማይዘልቅ የቊሳቊስ እርዳታ እንደ ሆነ ያውቃል። አንድ ጊዜ አዲስ በጉዳዩ የተሳቡ ወገኖች የተራቡ ሕፃናትን በቴሌቪዥን መስኮት ካሳዩ በኋላ፣ አብዛኛው የመስጠት ተግባር ይቋረጣል፣ ደግሞም የተራቡት ሰዎች ይረሳሉ።

ነገር ግን በሕይወት ወዳሉት ልጆቹ፣ ወደ ቤቱ መጥቷል ሰላምንም አግኝቷል። እያንዳንዷን ቀን ተራ በተራ ይኖሯታል፣ በወደፊቱ የአሳብ ሸክም መጨፍለቅ አያስፈልገውም። እርሱም ጭምር አባት ያለው ነበርና።

በፓትሪሺያ ሴንት ጆን የተጻፉ

ሌሎች አስደሳች መጻሕፍት:-

1. የአራተኛው ሻማ ምሥጢር
2. አስደናቂው የይቅርታ ቅርስ
3. የብርሃን ኮከብ